የሶሻል ሳይንስ ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል


ድህረ ምረቃ

# በአማርኛ ቋንቋ ለ7ኛ ክፍል በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ተገቢነት እና የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ


በ

እታለማሁ አድነው ደስታ



ነሐሴ 2013 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስ ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ

# በአማርኛ ቋንቋ ለ7ኛ ክፍል በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ተገቢነት እና የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ

በ

እታለማሁ አድነው ደስታ

አማካሪ

ዋና አማካሪ፣ ምህረት ሳዳም (ዶ/ር)

ረ/አማካሪ፣ ይክበር ይመስገን (MA)

ነሐሴ 2013 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስ ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ

# በአማርኛ ቋንቋ ለ7ኛ ክፍል በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ተገቢነት እና የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ

በ

እታለማሁ አድነው ደስታ

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | ፊርማ |
|---|---|
| አማካሪ | _______________ |
| ፈታኝ | _______________ |
| ፈታኝ | _______________ |

## ማረጋገጫ

በአማርኛ ቋንቋ ለ7ኛ ክፍል በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ተገቢነት እና የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራና የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን የተጠቀምኩባቸውንም ቀደምት ጥናቶች በትክክል በዋቢነት ያቀረብኳቸው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ______________________________

ቀን____________________________

ፊርማ _________________________

# ምስጋና

ከጥናቱ ረቂቅ አስከ ዋናዉ የጥናትና ምርምሩን አቅጣጫ በመጠቆምና በትዕግስት አንብቦ ተገቢዉን እርማት በመስጠት ከፍተኛ ዕገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶክተር ምህረት ሳዳም እና ይክበር ይመስገን ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለዚህ ጥናት አስተዋጽኦ ላደረጉልኝ የተቋሙ መምህራን ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ለጥናቱ የሚያስፈልገኝ ወጪ በመሸፈን ትብብር ላደረገልኝ ለጅማ ዩንቨርሲቲ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ለጥናትና ምርምር ሥራዬ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን እንዳገኝ የተለያዩ መፅሐፍትን ለዋሱኝ፣ በቃለ መጠይቅና በጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎችን እንድሰበስብና ፈቃድ በመስጠት ለተባበሩኝ መስርያ ቤቶችና ግለሰቦች ምስጋናዬ የላቀ ነዉ፡፡

ለጥናቱ መሳካት ከጎኔ ሳይለዩኝ ላበረቱኝና ለደገፉኝ ልጆቼ ፍቅሬና ምስጋናዬ ይድረስልኝ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ በ2009 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ በዋለዉ የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሓፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ተገቢነት እና የክፍል ዉስጥ አተገባበር መፈተሸ ነዉ፡፡ ጥናቱ መነሻ ያደረገዉም መማሪያ መጽሐፉ በዉስጡ ያከተታቸዉ የሰዋሰዉ ይዘቶች አደረጃጀት ምን ይመስላል? የክፍል ዉስጥ አተገባበርስ ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ነዉ፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ከተተኳሪዉ መማሪያ መጽሐፍ በሠነድ ፍተሻ፣ መማሪያ መጽሐፉን ከሚያስተምሩት የደረጃዉ ቋንቋ መምህራን በቃለ- መጠይቅ፣ ከደረጃዉ በናሙና ከተመረጡ ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ እንዲሁም ከክፍል ምልከታ አስፈላጊዉ መረጃ ተሰብስቦና ተደራጅቶ አይነታዊ የምርመር ዘዴን በመጠቀም በገላጭ የምርምር ስልት በመተንተን የዉጤት ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ ለሠነድ ፍተሸዉ ጥናቱ መሠረት አድረጎ የተነሳዉ በክለሳ ድርሳን ሥር ምሁራን የሰጡትን ንድፈ ሀሳባዊ መርሆችን ሲሆን የይዘቶቹ አደረጃጀት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከዉጤት ተኮር ወደ ሂደት ተኮር የቀረበ ነዉ፡፡ የሠነድ ፍተሻዉ እንደሚያመለክተዉ ሁሉንም ይዘቶች መጠቀሙ ጠንካራ ጎን ሲሆን በድክመት የታየዉ ለአንዱ ይዘት ብቻ ሰፊ ጊዜና ቦታ መስጠቱና ሌሎቹ ይዘቶች ዝቅተኛ መሆንና አለመመጣጠን መጠቆሙ ነዉ፡፡ ቃለ መጠይቁን፣ የጽሑፍ መጠይቁንና የክፍል ዉስጥ ምልከታዉን ለመተንተን፡- ግበአቱን ከማስገንዘብና አጠቃቀሙን ከማለማመድ፣ በምሳሌ ወይም ከማስታወሻ ወደ ጥያቄ የቀረበ፣ በገለጻ ስልት ብቻ የቀረበ፣ ከተመጣጣኝነት አንፃር የቀረበ እና ከተገቢነት አንፃር የቀረቡ የሚሉ ነጥቦችን በመጠቀም ጥያቄዎችን በመተንተን በተገኘዉ ወጤት ላይ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡በተገኘዉም ዉጤት መሰረት በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱት የሰዋሰዉ ይዘቶች የክፍል ደረጃዉን ከመመጠንና ተገቢነት አንፃር ጠንካራ ጎን ሲኖረዉ ለታላሚዉ ቋንቋ ሥርዓት የሚተነትኑ እንጂ ለመዋቅሩ ፍቺና አጠቃቀም ላይ ትኩረት አለማሳየቱ ድክመትን አሳይቷል፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና ..... i

አጠቃሎ ..... ii

የይዘት ማውጫ ..... iii

የሠንጠረዥ ማዉጫ ..... vi

ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ ..... 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..... 2

1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ..... 2

1.4 የጥናቱ ዓላማዎች ..... 3

1.5 የጥናቱ ዋና ዓላማ ..... 3

1.6 የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች ..... 3

1.7 የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 3

1.8. የጥናቱ ወሰን ..... 4

ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት ..... 5

2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች ..... 5

2.1.1 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ..... 5

2.1.2 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ..... 8

2.1.3 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ..... 8

2.2 የሰዋሰው ይዘቶች አደረጃጀት ..... 12

2.2.1 ተከታታይነት ..... 13

2.2.2 ተለጣጣቂነት ..... 13

2.2.3 የቋንቋ መርሃ ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍት ..... 13

2.3 የተዘማጅ ጥናቶች ቅኝት ..... 15

ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ዘዴና አካሄድ ..... 19

3.1 የጥናቱ ዘዴ ..... 19

3.2 የጥናቱ አካላይ ..... 19

3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ ..... 19
3.3.1 የት/ቤት ናሙና አመራረጥ ..... 19
3.3.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ..... 20
3.3.2 የተማሪ ናሙና አመራረጥ ..... 20
3.3.3. የመምህራን ናሙና አመራረጥ ..... 20
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ..... 20
3.4.1. የሰነድ ፍተሻ ..... 21
3.4.2 ምልከታ ..... 21
3.4.3 የጽሑፍ መጠይቅ ..... 21
3.4.4 ቃለ መጠይቅ ..... 21
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ ..... 22
ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ ..... 23
4.1. የመማሪያ መጽሐፉ አጠቃላይ ቅኝት ..... 23
4.2. በመማርያ መጽሀፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ..... 25
4.2.1. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ..... 25
4.2.2. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ..... 28
4.2.3. ዉጤት ተኮር አቀራረብ ..... 38
4.2.4. ሂደት ተኮር አቀራረብ ..... 51
4.3. በመማሪያ መፀሐፍ ውስጥ የተካተቱት የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ..... 54
4.3.1 ተከታታይነት ..... 54
4.3.2. ተለጣጣቂነት ..... 56
4.3.3. መማሪያ መጽሐፍ ከመረሃ ትምህርቱ ጋር ያለዉ ዝምድና ..... 59
4.4. በማማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ትኩረት የተሰጣቸዉ የሰዋስው ግብአቶች ..... 60
4.4.1. የቋንቋ  ክፍሎች ..... 60
4.4.2. በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡ የሰዋሰዉ መልመጃዎች አደረጃጀት ..... 63
4.4.3. ግብአቱን ከማስገንዘብና አጠቃቀሙን ከማላመድ አንጻር የቀረበ ..... 69
4.4.4. ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..... 78
4.4.4  የውጤት ማብራሪያ ..... 83

ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያና አስተያየት ........................................................................ 89
5.1 ማጠቃለያ ........................................................................................................ 89
5.1. አስተያየት ...................................................................................................... 93
ዋቢዎች ........................................................................................................................ 94
አባሪዎች ...................................................................................................................... 97

# የይዘት ማዉጫ

ገፅ

ርዕስ

ሠንጠረዥ 1፡-የሰባተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማርያ መጽሐፍ አጠቃላይ ቅኝት ................24
ሠንጠረዥ 2. በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ተከታታይነት ኖሮአቸው የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች........................................................................54
ሠንጠረዥ3 በደቡብ ክልል የ7ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መረሃ ትምህርት መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡትን ዝርዝር የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች። ....................................................59
ሰንጠረዥ 4"በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡትን የሰዋሰዉ መልመጃዎች ለቋንቋ ቅርፃዊ ሥርዓትና ፍቺ ተመጣጣኝ ትኩረት ሰጥተዋል ብለዉ ይስማማሉ?" ተብለዉ በቀረበ ጥያቄ የሰጡት መልስ ..........................................................................................................62
ሠንጠረዥ 5. የሰዋሰዉ መልመጃዎች ይዘቱ/ግብአቱ/ ከጥልቅ በህሪ ወደ ዝርዝር ባህሪይ ቀርቧል ብለዉ ይስማማሉ? ተብሎ ለቀረበዉ ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት መልስ፡፡.................67
ሠንጠረዡ 6. በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡትን ምሳሌዎች እንዲታወቅ የተፈለገዉን የሰዋሰዉ ጉዳይ በግልጽ ያቀርባሉ ብለዉ ይስማማሉ? ለሚለዉ ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ...........................................................................................................................71
ሠንጠረዥ 7. በመማሪያ መጽሃፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰው ጥያቄዎች በምሳሌዎቹ ብቻ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ብለዉ ይስማማሉ? ተብሎ ለቀረበዉ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ........................72
ሠንጠረዥ 8. በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ጥያቄዎች ለገለጻ ወይም ለማስተዋሻ ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት ሰጥተዋል ብለው ይስማማሉ? ለሚለዉ የሰጡት መልስ ..........................................................................................................................75
ሠንጠረዥ 9. በመማሪያመጽሐፍዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ለደረጀዉ የሚመጥንና ተገቢ መሆኑን ይስማማሉ? ተብሎ ለቀረበዉ የጽሑፍ መጠይቅ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ...........................................................................................................77
ሠንጠረዥ 10. መምህራን የሰዋሰዉ ይዘቶችን በየዕለቱ በክፍል ዉስጥ አተገባበራቸዉ ምን እንደሚመስል ለማወቅ የተደረገ የምልከታ ዉጤት ትንተና፡፡ ................................................78
ሠንጠረዥ11 የክፍለ ጊዜዉን ትምህርት መመህራን በምን መልክ እደሚያቀርቡት ለማወቅ የተደረገ ምልከታ የተገኙ ምላሾች ትንተና.......................................................................81

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ሥርዓት በሚገባ ተረድተው በትክክለኛ መንገድ ጥቅም ላይ እዲያ ውሉ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ ትምህርቱ የቋንቋውን ቅርጽ፣ ፍቺና አጠቃቀም ትስስሮሽ ፈጥሮ ማቅረብ እንደ ሚገባው (Larsenfreeman (1986) ይገልፃሉ።

በተጨማሪም እንዚህን የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ታሳቢ ያደረገ ትምህርት ለማቅረብ በመጀመሪያ የታላሚውን ቋንቋ ሥርዓት መሰረት በማድረግ ተገቢ የማተማር ስነዘዴን መምረጥ እንደሚያስፈልግና የመማር ማስተማስተማሩ ንሂደት በሚገባ ለመቆጣጠር የሚያስችል ተገቢ የይዘት አመራረጥ፣ አቀራረብና አደራጃጀት መከተል፣ እንዲሁም ከቋንቋው ጋር የሚገናኙ መልመጃዎችንና ተግባራትን በምሳሌዎችና በማብራሪያዎች አስደግፎ ማቅረብ እንደ ሚያስፈልግም ያስረዳሉ። በማህበራዊ ተራክቦ ወይም መስተጋብር የአንድን ቋንቋ ስርዓት ጠብቆ ለመግባባት መሰረታዊ የቋንቋ ክፍሎችንና የሰዋሰው ህጎችን ማወቅ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑ እውን ነው።

Ur(1988፣4-5) በአንድ ቋንቋ ሰዋሰው ችሎታ ከሌለ ወይም አጠቃቀሙን በአግባቡ ለይተን ካላወቅን የቋንቋ ችሎታችን ደካማ ወይም ጎዶሎ እንደሚሆን አያጠያይቅም ሲሉ ገልፀዋል። በተጨማሪም ባየ(1987፣8 "ከማንኛውም የክህሎት ትምህርት በስተጀርባ ማንኛውም የቋንቋ ተማሪ ሊገነዘበው የሚገባው ጥልቅ የሆነ እውቀት አለ። ይህም የቋንቋ ሥርዓት ከድምጽ እስከ ሐረግ አመሰራረት ድረስ የሚያሳይ ሳይንስ ነው" ብለዋል። ከገለፃው መረዳት እንደሚቻለው ሰዋሰው በአንድ ቋንቋ ውስጥ ሰፊ ቦታ ያለው ሲሆን ይህም በትምህርት ቤት ደረጃ በሚሰጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ ሁለተኛ ቋንቋና የውጭ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋሰውን ማስተማር ጠቀሜታ እንዳለው መጠቆሙ ነው። ከዚህ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ጌታሁን(1989፣v) "የቋንቋ ትምህርት ዓላማ በክሂሎች ላይ ብቻ ሳይሆን በሥርዓትም ላይ መሆን አለበት። ምክንያቱም ሁለቱም አንድን ቋንቋ ተማርኩ ከሚል ሰው የሚጠበቁ ችሎታዎች ናቸው። ይህ ካልሆነ ደግሞ ተምሬአለሁ የሚለው እውቀት ቁንፅል ይሆናል። "በማለት ገልጸዋል።

የዚህ ጥናት ትኩረት የሆውን የሰዋሰውን ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ስንመለከት የግምገማ ዋነኛ ትኩረት ወይም ዓላማ አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ለሚማሩ ተማሪዎች በተዘጋጀው የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ነው፡፡ በየክልሉ የሚዘጋጁት የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት የየራሳቸው  ችግር አይጠፋቸውም ተብሎ ይገመታል፡፡ ስለሆነም በየቋንቋው የሚዘጋጁት መማሪያ መጽሐፍት ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ተከታታይ ግምገማ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

ይህንኑ አስመልክተው Dubin and Olshtain(1986፣2-3) እና Cunningsworth(1984፣5) መማሪያ መጽሐፍት ተዘጋጅተው ሥራ ከዋሉ በኋላ ተከታታይ ግምገማ ሊደረግባቸው እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት በደቡብ ክልላዊ መንግስት ለሰባተኛ ክፍል የተዘጋጀውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከሰዋሰው ይዘቶች አደረጃጀት ተገቢነት እና የክፍል ውስጥ አተገባበር አንፃር ምን እንደሚመስል መርምሯል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህ ርዕስ የተመረጠበት ዋና ምክንያት አጥኚዋ በዚህ የክፍል ደረጃ ከነበራት የረጅም ጊዜ የማስተማር ልምድ አንጻር በዚህ ክፍል ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች የሰዋሰው እውቀት ዝቅተኛ ሆኖ መታየቱ፣ መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት የሰዋሰው ይዘቶች አደረጃጀት ምን ይመስላል? የክፍል ውስጥ አተገባበርስ እንዴት ነው? የሚለውን ለመፈተሸ ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

የዚህ መሪ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው

1. የሰዋሰው ይዘቶች የቀረቡበት መንገድ ምን ይመስላል?
2. የዘቶቹ አቀራረብ ጥንካሬና ድክመት ምንድነው?
3. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተመርጠው የቀረቡት የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች የተደራጁበት መንገድ ምን ይመስላል?
4. በክፍል ውስጥ የመምህራን አተገባበር ጠንካራና ደካማ ጎን ምንድ ነው?
5. የሰዋሰው ያዘቶችን አስመልክቶ በመማሪያ መጽሐፉን በመርሃ ትምህርቱ መካከል ያለው ትስስር ምን ይመስላል? የሚሉት ተፈትሸዋል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ዓላማዎች

### 1.5 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት አብይ አላማ በደቡብ ክልላዊ መንግስት ተዘጋጅቶ በ2009 ዓ.ም ሥራ ላይ በዋለው የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ተገቢነት እና የክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ነው፡፡

### 1.6 የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች

የጥናቱን ዋና አላማ መነሻ በማድረግ ለሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች መልስ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

1. የሰዋስው ይዘቶች የቀረቡበት መንገድ ምን እንደሚመስል ማብራራት
2. የይዘቶቹ አቀራረብ ጥንካሬና ድክመትን መለየት
3. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተመርጠው የቀረቡት የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች የተደራጁበት መንገድ ምን  እንደሚመስል መግለፅ
4. በክፍል ውስጥ የመምህራን አተገባበር ጠንካራና ደካማ ጎንን መለየት
5. የሰዋስው ይዘቶችን አስመልክቶ በመማሪያ መጽሐፉና በመርሃ ትምህርቱ መካከል ያለው ትስስር ምን እነደሚመስል ማብራራት

### 1.7 የጥናቱ ጠቀሜታ

በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ከሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች መካከል አንዱ የሰዋስው ትምህርት ነው፡፡ በመሆኑም በታላሚው መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ፍተሻ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

- በሰዋስው አቀራረብና አደረጃጀት አኳያ በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ የታዩት ድክመቶች የሚሻሻሉበትን አቅጣጫ ለቋንቋው መማሪያ መጽሐፍት አዘጋጆች ይጠቁማል፡፡
- በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የሰዋሰው ትምህርት የይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት በመፈትሽ ምን አይነት ገፅታ እንዳለው በመጠቆም በመስኩ ለሚደረግ ቀጣይ ጥናት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡
- የደረጃውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ለሚያዘጋጁና ለሚያሻሽሉ አካላት በዝግጅታቸውም ሆነ በማሻሻል ሥራቸው ሊገለገልባቸው የሚችሉትን ግብአቶች ይጠቁማል፡፡

- የቋንቋ መምህራን የስልጠና እድል ቢገጥማቸው የሚያስተምሩበቸው መጽሐፍት ሰዋሰዋዊ ይዘታቸውን ለመገምገም የሚያስችላቸውን መነሻ ሀሳብ ሊያገኙበት ይችላሉ፡፡
- ቀጣይ ከዚህ ርዕስ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጥናት ለሚያደረጉ አከላላት መነሻ ሀሣብ ይሰጣቸዋል፡፡

## 1.8. የጥናቱ ወሰን

ምንም እንኳን በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ የተነሱት ርዕሰ ጉዳያች ሰፊ ቢሆኑም ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በደቡብ ክልል፣ በ2009 ዓ.ም በሥራ ላይ በዋለው የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ተገቢነት እና የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ ለደረጃው የተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ጋር አያይዞ የሚመለከት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች

### 2.1.1 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች

የሰዋስው ትምህርት ትኩረት በቋንቋው ቅርፅና መዋቅር ላይ ሆኖ መምህር መር የትምህርት ሂደትን በመከተል ተማሪዎች የሚሰጣቸውን ገለፃና ማብራሪያ የቋንቋውን ህግጋት በሙሉ እንዲቆጣጠሩ ማድረግ ነበር፡፡ የተማሪዎች የቋንቋ ብቃት ተደርጎ የሚታየውም ቃላትን በተገቢው ቦታቸው በመሰካት አረፍተ ነገሮችን ማዋቀር መቻላቸው ነው፡፡ ለዚህ ሰዋሰውወ ትርጉም ዘዴን እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህን የማስተማር ሥነ ዘዴ መሰረት አድረገው በሚዘጋጁ የቋንቋ ቅርፅና ህግ ላይ ያተኮሩ ሆነው በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚተው ባዶ ቦታ መሙላትን፣ በታላሚው ቋንቋ የተፃፉ አረፍተ ነገሮችን ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መተርጎምና የቃላትን ቅደም ተከተል ማስተካከል የመሳሰሉት ይዘቶች ነበሩ (Nunan፣1991)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ለአንደኛ ቋንቋ ደግሞ የሰዋሰው ትምህርት የሚቀርቡ ሰነ ልሳናዊ ይዘቶች መሰረት የሚያደርገው የቋንቋ ማስተማር ስልት አይነት የተለያዩ ናቸው፡ ፡ውጤታማ ስልት መሰረት የሚያደርጉ ወገኖች የታላሚውን ቋንቋ ቅርፃዊ ሥርዓት ወይም ቅርፃዊ ሥርዓቱንና ፍቺውን ከስነልሳን ትንታኔዎች አንፃር መርጠውና አደራጅተው ይቀርባሉ፡፡

በአንፃሩ ሂደታዊ የቋንቋ ማስተማር ስልትን የሚከተሉ ወገኖች ደግሞ ስነልሳናዊ ግብአቶችን ወይም ይዘቶችን ሳይሆን ክንዋነዎችን ወይም አዉዶችን ከተማሪው የመማር አላማና ዳራዊ ገጠመኝ አንጻር መርጠው ያቀርባሉ፡፡ ውጤት-ወ-ሂደት የቋንቋ ማስተማር ስልትን የሚከተሉ ወገኖች ደግሞ ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ የስነ ልሳን ትንታዎችንና የተማሪውን ፍላጎት መርጠው በይዘትነት ያቀርባሉ፡፡ (Leech፣1994፣ Batstone፣1994፣Nunan፣1988)፡፡

ለአንደኛ ቋንቋ ወይም አፈ-ፈት ተማሪ የታላሚውን ቋንቋ ቅርፃዊ ሰዋሰው በይዘትነት ሊቀርብ እንደሚገባ የመስኩ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ቅርፃዊ ሰዋሰው ተብሎ በዚህ አውድ ውስጥ የቀረበው ስያሜ የተወሰደው Batstone(1994፣11)ነው፡፡ በገለፃውም መሰረት "ቅርፃዊ ሰዋሰው የቋንቋውን ቅርፃዊ ስርዓት የሚመለከት ነው፡፡ ሁኔታውን በምሳሌ ሲያብራሩ፣ ለምሳሌ"ባለቤት"የሚለውን ተለምዶአዊ አባባል ወስደን ከስሩ የዋለውን የድርጊት ፈፃሚነት ወይም የአረፍተ ነገር

ባለቤትነት ፍችውን ስናስወግድለት የሚቀረውን ገጽታ ይመለከታል" ብለዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ Harmer(1991) ቀደም ሲል የተገለጸውን ሀሳብ" የሰዋሰው ቅርጽ' 'በማለት ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ" ቅርጻዊ ሰዋሰው" የሚለው ፍችን ሳያካትት ያለውን የቋንቋውን ቅርፃዊ ስርዓት ብቻ ይመለከታል ለማለት .ያስችላል፡፡

ቅርፃዊ ሰዋሰው ከቃላት ተለይተው ብቻውን ያለ ነገር አይደለም፡፡ Batstone(1994) ገለፃ መሰረት ቅርፃዊ ሰዋሰውና ቃላት ተለያይተው ያሉ ነገሮች ሳይሆኑ እርስበርስ ተሳስረው የሚገኙ ናቸው፡፡ በመሰረቱ "ሰዋሰው" ማለት ድምፆች ተቀናጅተው ቃላትን፣ ቃላትና ሀረግን ወይም አረፍተ ነገርን የሚመሰርቱበት እስከሆነ ድረስ ቅርፃዊ ሰዋሰውና ቃላት ወይም አረፍተ ነገር ተለያይተው ያሉ ናቸው ለማለት አያስችልም Ur(፣1996)፡፡ ይህም ሁኔታ የሚጠቁመው ቅርፃዊ ሰዋሰው በቃል ዉስጥ መቅረብ ያለበት መሆኑን ነው፡፡

ቅርፃዊ ሰዋሰው በቃላት ላይ የሚገጥም ባዕድ ነገር ሳይሆን አንዱ አብይ የቋንቋ አካል እንደሆነ የመስኩ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ Celce Marcia and Hills(1988) በገለፁት መሰረት ቅርፃዊ ሰዋሰው እንዲሁ ተራ የሆነ የቋንቋ አደረጃጀት ሥርዓት ሳይሆን አንዱ አብይ የቋንቋ ተዋቃሪ አካል ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ይህ አብይ የቋንቋ አካል ለአንደኛ ቋንቋ ተማሪ በይዘትነት ሊለማመዱት እንደሚገባ የመስኩ ምሁራን የሚስማሙበት ነጥብ ነው (Batstone፣1994፣ Ur፣1996፣Leech፣1994)፡፡

ሌላው ደግሞ በዚህ ጥናት ውስጥ "ሰዋሰዋዊ ፍች" የሚለው ቅርፃዊ ሰዋሰው ስር የሚውለውን ፍች ይመለከታል፡፡ ይህን ፅነሰ ሀሳብ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ይገልፁታል፡፡ ለምሳሌ Ur(1996) "ሰዋሰው ፍች" ብለው ሲገልፁት፣ (Celce Marcia and Hills1988፣9) ደግሞ ስነ ትርጉማዊ ፍች ነው ብለው ገልጸውታል፡፡ Celce Marcia and Hills ስነትርጉማዊ ፍች በማለት ለሰየሙት ሰዋሰዋዊ ሀሳብ የሚከተለውን ማብርሪያ ሰጥተዋል፡፡---"ስነ ትርጉማዊ ፍች የተባለው ከስነ ትርጉማዊ አተያይ አንፃር የሚቀርብ፣ ብዙ ጊዜ ተፈጥሮአዊ የሆነ የቅርፃዊ ሰዋሰው ፍች ሲሆን ይህም ጊዜን፣ ቦታን፣ ሁኔታን፣ ድግግሞሽን ወዘተ የሚገልፅ ነው" (Ur፣ 1988፣11)፡፡ በበኩላቸው "ሰዋስዋዊ ፍች" የሚለው ሲያሜ ገላጭ ስነ-ልሳናዊያን የሚሰጡትን ዓይነት ፍች የሚመለከት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በዚህ የተነሳ በዚህ ጥናት ውስጥ "ሰዋሰዋዊፍች" ተብሎ የተገለፀው ስነ ትርጉማዊ ሰዋሰዋውያን ወይም ገላጭ ሰዋሰዋውያን የሚተነትኑትን የቅርፃዊ ሰዋሰው ፍችን ይመለከታል ማለት ነው፡፡

ውጤታዊ የቋንቋ ማስተማር ስልትን የሚከተሉ ወገኖች ፍችን በጥንቃቄ መርጠውና አደራጅተው በይዘትነት ለአንደኛ ቋንቋ ተማሪ ያቀርባሉ (Cunningsworth፣1995፣ Batstone፣ 1994፣ Celce and Hills፣1988፣ እና Ur፣1996)። በአንፃሩ ሂደታዊ የቋንቋ ማስተማር ስልትን የሚከተሉ ወገኖች ሰዋሰዋዊ ፍችን በይዘትነት ማቅረብን አይደግፉም። ቀደም ሲል እንደተገለፀው በእነዚህ ወገኖች እምነት የቋንቋ ትምህርት በውጤት ላይ ሳይሆን ወደ ውጤቱ በሚወስደው ሂደት ላይ ማተኮር አለበት ነው። ሂደት ብለው የሚጠሩትም በአውድ ውስጥ በቋንቋ የመግባባት ልምምድን ነው። ከዚህ እምነታቸው በመነሳት ለአንደኛ ቋንቋ ተማሪ በይዘትነት የሚቀርቡትን ስነ ልሳናዊ ግብአት ወይም ቅርፃዊ ሰዋሰውንና ፍችውን ሳይሆን አውዶችን ማለትም ሁኔታዎችን፣ ርዕሰ ጉዳዮን እንደሆነ ጥናቶቹ ይገልፃሉ። በመስኩ የተደረጉ የቅርብ ጥናቶችን መሰረት አድርገው ምሁራን እንደሚገልፁት የታላሚው ቋንቋ ስነ-ልሳናዊ ይዘት ለአንደኛ ቋንቋ አስፈላጊ ስለሆነ በጥንቃቄ ተመርጠውና ተደራጅተው መቅረብ ያለበት መሆኑን ነው። እንደ (Cook፣2001፣ እና Larsen፣ Free man፣1991) በዘመናዊ ሰዋሰው ትምህርት እሳቤ ሰዋሰዋዊ ቅርፆችንና ህግጋትን ብቻ ማስተማሩ ተቀባይነት የለውም። የሰዋሰው ትምህርት ትኩረት በቋንቋ ቅርፅ ወይምመዋቅር፣ ፍችና እና አጠቃቀም ላይ መሆን ይገባል። Palmer(1984) እንደሚሉት የሰዋሰው ትምህርት ትኩረት ተማሪዎች በቋንቋው ሰዋሰዋዊ እውቀት ላይ የተመሠረተ የተግባቦት ብቃት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው። ተማሪዎች የቋንቋውን ቅርፅ ከፍችና ከአጠቃቀም ጋር አጣምረው በመማር ተገቢ የሆኑ አረፍ ተነገሮችን አፍልቀው እንዲጽፉ ወይም እንዲናገሩ፣ አድምጠው ወይም አንብበው መልዕክትን እንዲጨብጡ የሚያስችል የትምህርት ሂደትን የሚከተል መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ።

Ellis (2000) ይህንኑ ሀሳብ ሲያጠናክሩ የሰዋሰው ትምህርት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋሰው ባህርያት በሚገባ ተረድተው በተግባቦት ሂደት ጥቅም ላይ የሚያውሉበትን ሥርዓት የሚያሳይ እንደመሆኑ ሰዋሰውና ተግባቦት ተነጣጥለው መታየት የለባቸውም ይላሉ። ምክንያቱም አንዱ የቋንቋ ቅርፅ የያዘውን ቃላዊም ሆነ ሰዋሰዋዊ ፍች መገንዘብ ለተግባቦቱ፣ የሚሰጠውን ቅልጥፍና መገመት አያዳግትም። ስለዚህ የሰዋሰው ትምህርት ለቋንቋው ቅርፅ፣ ፍችና አጠቃቀም ትኩረት መስጠት አለበት ይላሉ። በአጠቃላይ ከላይ ምሁራን ካቀረቡት ገለፃ ለመረዳት እንደሚቻለው ቅርፅ፣ፍችና አጠቃቀም በሰዋሰው ትምህርት ውስጥ ትኩረት ሊደረግባቸው እንደሚገባና ተነጣጥለው የማይታዩ መሆናቸውን ነው።ቅርፅ ካለ ፍች መኖሩ ግድ ነው። ፍችም ካለ ቅርፅ መኖሩ ግድ ነው አጠቃቀም እንዲሁ ከቅርፅና ከፍች ጋር የተሳሰረ

ነው፡፡ እነዚህ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች የተቆራኙና ለትምህርት አላማ ግብ መምታት ተመጣጣኝ ፋይዳ ያላቸው መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

### 2.1.2 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት

### 2.1.3 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

የትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ አስመልክቶ ከሚነሱ ነጥቦች መካከል በዚህ ጥናት ውስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ሂደት ተኮርና ውጤት ተኮር እንዲሁም ሰዋሰውን እንደ ክፍሎች ማቅረብ የሚሉት ተተኳሪ ይሆናሉ፡፡

#### 2.1.3.1 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ስልት ትኩረት የሚያደረገው ዝርዝር የቋንቋ ባህርያትን የሚያሳዩ ምሣሌዎችንና መልመጃዎችን ትኩረት ሰጥተው ከተገነዘቡና ከሰሩ በኋላ አጠቃላይ የቋንቋውን ስረዓት እንዲረዱ የሚያደረግ ነው፡፡ Woods (1995፣76) ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ማቅረብ ማለት በአግባቡ የተመረጡ ምሣሌዎች በማቅረብ፣ ተማሪዎች የቀረቡትን ምሣሌዎች መሰረት አድርገው የተሰጣቸውን መልመጃዎች ከሰሩ በኋላ የቋንቋውን ህግ በራሳቸው እንዲደርሱበት የሚደረግ አካሄድ የተከተለ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም የአቀራረብ ስልቱ ተማሪዎቹ ከቋንቋ ዝርዝር ይዘቶች ተነስተው አጠቃላይ ወደ ሆነው የቋንቋ ህግ እንዲሸጋገሩ የሚያስችል አካሄድን የሚከተል መሆኑን Larsen Freeman(1991) ይጠቁማሉ፡፡ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚደረግ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች ስለ ቋንቋው ህግ ሊያውቁ የሚችሉበት የትምህርት አቀራረብ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ የአቀራረብ ስልት መሰረት የቋንቋ የሰዋሰው ህጎች በቀጥታ ለተማሪዎች አይቀርቡም፡፡የዚህ አቀራረብ ጠንካራና ደካማ ጎኖች የሚባሉት፡-

ጠንካራ ጎኖች፡-

- አዕምሮአቸውን በስፋትና በጥልቀት እንዲጠቀሙበት ያግዛቸዋል፡፡
- የእርስበርስ መስተጋብርን ስለሚፈቅድ ለቋንቋ ክህሎት መዳበር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡
- ተማሪዎች ከሚቀርቡላቸው ምሣሌዎች ተነስተው ህግጋትን እንዲያውቁ ስለሚጋብዛቸው በነፃነት የመማርና በራስ የመተማመን ችሎታቸውን ያዳብራሉ፣
- የመማር ፍላጎታቸውን ያነሳሳል፣ያነቃቃል፣
- ችግር አፈታት ችሎታቸውን ያዳብራል፡፡

ደካማ ጎኖች

- ➢ በህግጋት ትንታኔ መማር የለመዱ ተማሪዎችን ግራ ሊያጋባ ይችላል፣
- ➢ ጊዜና ጉልበት ያባክናል፣
- ➢ ሰዋሰዋዊ ህግጋቱ ለተማሪዎች መጀመሪያ ስለሚቀርቡ ተማሪዎቹን ወደ ተሳሳተ ግንዛቤ እንዲመሩ ሊያደርጋቸው ይችላል የሚሉት ናቸው፡፡

### 2.1.3.2. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ

በዚህ ስልት ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለፃ ይቀርብላቸዋል፡፡ ከገለፃ በመነሳት ህግጋቱን ለመተግበር ወይም ለተግባቦት ማዋል ይሞክራሉ፡፡ ይህም መሆኑ ተማሪዎች የቋንቋውን ህግጋት በፍጥነትና በቀላሉ እንዲረዷቸው ያስችላቸዋል፡፡

ሆኖም ይህ ብቻውን በቂ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በገለፃ ብቻ በመታገዝ ህግጋቱን በጥቅም ላይ ወይም ለተግባቦት ማዋል አዳጋች ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ በበቂ ምሣሌዎች ተደግፎ መቅረብ ይገባል ይላሉ Cunnings Worth(1995).Harmer(1987) እና Larsen Freeman(1991) ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ስልትን አስመልክቶ ከላይ ከቀረበው ገለፃ ጋር ተመሳሳይ ገለፃ ተሰጥቷል፡፡ በዚህ የአቀራረብ ስልት ለተማሪዎች ስለ ታላሚው ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለፃ ይቀርብላቸዋል፡፡ ገለፃውንም መሰረት በማድረግ ህግጋቱን በዝርዝር መለማመድ ይቀጥላሉ፡፡

ጠንካ ራጎኖች፡-

- ➢ ሰዋሰዋዊ ህግጋቱን በቀጥታ የሚያቀርብ በመሆኑ ጊዜ ይቆጥባሉ፣
- ➢ ተማሪዎቹ ህግጋቱን ከተረዱ በኂላ ምሳሌ ያቀርብላቸዋል፣
- ➢ የማገናዘብ ችሎታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎችን የመማር ስልት ያጠናክራል፡፡

ደካማ ጎኖች፡-

- ➢ ህግጋትን በቀጥታ በመግለፅ የሚጀምር በመሆኑ በተለይ ለህፃናት ይከብድባቸዋል፣
- ➢ የትምህርቱ አቀራረብ በመምህሩ የሚመራ በመሆኑ የተማሪዎችን ተሳትፎና የእርስበርስ ግንኙነት ይገድባል፣
- ➢ የህግጋቱ ገለፃ በተግባቦት ላይ የተመሰረት ባለመሆኑ የመታወስ ዕድሉ ዝቅተኛነው፡፡

ከላይ በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው ሁለቱም የአቀራረብ ስልቶች የየራሳቸው ጥንካሬና ድክመት ይታይባቸዋል፡፡ በተለይም አንዱ አቀራረብ የሌለኛው ግልባጭ ከመሆኑ የተነሳ አንዱ ጥንካሬ የሌላው ድክመት ሆኖ ታይቷል፡፡ በመሆኑም እንደኛው የሌለኛውን ክፍተት የሚሞላ መሆኑን ተገንዝቦ እንደ አስፈላጊነታቸው ሁለቱንም አቀራረቦች እያፈራረቁ ጥቅም ላይ ማዋል ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የተለያዩ እንደመናቸውም መጠን የተለያዩየ ትምህርት አቀባበል ችሎታ፣ የመማር ስልት ምርጫ፣ወዘተ ያላቸው መሆናቸውም ሊስተዋል ይገባል፡፡ ይህም ብቻ ሣይሆን በተለያዩ የትምህርት ዓላማዎች፣ የተለያየ አቀራረብ ስልቶችን የሚከተሉ ከመሆናቸው የተነሳ እነዚህንና መሰል ሁኔቶችን ለማመጣጠን እንደየ ሁነቱ ሁለቱንም የአቀራረብ መርሆች በተገቢው መንገድ እያፈራረቁ መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑን (Harmer፣1991) ያስገነዝባሉ፡፡

### 2.1.3.3 ውጤት ተኮር አቀራረብ

ይህ አቀራረብ ስልት መሠረት የሚያደርገው በታላሚው ቋንቋ መዋቅር ዙርያ ላይ ባለው የቋንቋ ቅረፅ ላይ መሆኑን፣ Batstone (1994፣51) ይገልፃሉ፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርዓት ላይ በማተኮር የቃላትና የአረፍተነገር አመሰራረት እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግን ትኩረት ያደረገ የአቀራረብ ዘዴን የሚከተል ነው፡፡ በመሆኑም ስልቱ የተማሪዎች የሰዋሰው አህዶችን ነጥለው በመተንተን በቋንቋው በዝርዝር ህግ ላይ ተመስርተው ትክክለኛ አረፍተ ነገሮችን እንዲያፈልቁ የሚያስችላቸው ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአቀራረብ ስልቱ ልማዳዊ የሆነ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ መርህ የተከተለ፣ በመፅሐፍት ላይ የተመሰረተና በቋንቋው መዋቂራዊ ህግጋትና ብያኔዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን በዘዴው የሚቀርበው የሰዋሰው የትምህርት ዓላማ ተግባቦት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ተማሪዎች የቋንቋውን ቃላት በቃል ክፍላቸው እንደለዩ፣ ቃላትን፣ ህግጋትንና አረፍተ ነገሮችን በተናጥል እንዲተነትኑና እንዲመሰርቱ የሚያደርግ እንጂ እነዚህን ቅርፆች ከተግባቦት ጋር በማቀናጀት እንዲለማመዷቸው የሚያስችል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግን ለማስተማር ስራ ፈጣኑ፣ ለመምህሩ ትምህርት አሰጣጥ ቀላልና ምቹ መሆኑ ደግሞ ከጠንካራ ጎኑ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ Harmer (1991) እና Batstone (1994፣5) የአቀራረብ ስልቱን ጥንካሬና ድክመት በሚከተለው መልክ አስፍረውታል፡፡

በጠንካራ ጎን የሚጠቀሱት፡-

- ግብአቶችን መርጦና አደራጅቶ ማቅረብ፣
- ውስን አላማ ይዞ የተማሪውን ልምምድ በተወሰነ ቅርጽ ላይ መገደቡና፣
- የፅነሰ ሀሳብ ግንዛበ ማስጨበጡ ሲሆን

በደካማ ጎን የሚጠቀሱት ደግሞ፡-

- ይዘቶችን በመምረጥና በማደራጀት ሂደት የተማሪውን ፍላጎት መሰረት ያለማድረጉ፣
- ለቅርፅ እንጂ ለፍች ትኩረት ያለመስጠቱና
- ድርግታዊ የማስተማር ስልትን ያለመጠቀሙ ናቸው፡፡

#### 2.1.3.4 ሂደት ተኮር የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ስልት የውጤት ተኮር ግልባጭ ነው፡፡ አላማው ሰዋሰውን ለተግባቦታዊ አገልግሎት ማዋልን የሚመለከት ነው፡፡ Batstone(1994፣51) ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት ተማሪዎች በቋንቋው ይበልጥ እንዲጎለብቱ ወይም በአውድ ውስጥ ትርጉም ሰጪ የሀሳብ ልውውጥ እንዲያደርጉ በማድረግ የቋንቋውን ቅርፆች ይበልጥ እንዲጠቀሙባቸው የሚያስችል አቀራረብ መሆኑንም ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ የምንረዳው ስልቱ ተማሪዎቹ በራሳቸው አውዶች ወይም ከራሳቸው ገጠመኝ፣ ዳራዊ እውቀት በመነሳት ሰዋሰዋዊ ህግጋትን በራሳቸው ጥረት እንዲገነዘቡአቸው የሚያደርግ አካሄድን የሚከተል መሆኑን ነው፡፡

ይህ ስልት እንደሌሎች ሁሉ የራሱ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት፡፡ ከጠንካራ ጎኖች መካከል በጉልህነት የሚጠቀሱት ተማሪዎቹ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ፍችና አጠቃቀም ተገንዝበው በቋንቋው መገልገል እንዲችሉ ማድረጉ ሲሆን፣ ከደካማ ጎኖች መካከልም፡-

- ለፍችው ብቻ እንጂ ለቅርጽ ትኩረት ያለመስጠቱ፣
- ሰዋሰዋዊ ስርዓቶችን ለተማሪዎች መርጦና አደራጅቶ ያለማቅረቡ፣
- ውስን አላማ ይዞ የተማሪዎችን ልምምድ በተወሰነ የቋንቋ ክፍል ላይ አለመገደቡና፣
- የፅነሰ ሀሳብ ግንዛቤ ሳያስጨብጥ ተማሪውን በጭፍን ወደ ተግባቦት ልምምድ ውስጥ ማስገባቱ፣ ተጠቃሽ መሆናቸውን Batstone (1994) ያስገነዝባሉ፡፡

በውጤት ተኮርና በሂደት ተኮር የሰዋሰው ትምህርት አቀራረቦች መካከል መሰረታዊ የሆኑ ልዩነቶች መኖራቸውን ከገለፃው መረዳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የመጀመሪያው በቅርፅ ላይ ሲያተኩር የሁለተኛው ደግሞ በአጠቃቀም ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ቀጥሎ ደግሞ የትምህርቱ አቀራረብም በቅርፅ ከሚደረግ የጽንሰ ሃሳብ ማስጨበጥ ልምምድ ተነስቶ በተገቢው ሁኔታ ወደ አውዳዊ የተግባቦት ልምምድ ሊሸጋገር እንደሚገባውና የተማሪዎች ምልምምድ በተወሰነ የቋንቋ ክፍል ወይም ቅርጽ መገደብ እንደሌለበት ይገልፃሉ፡፡

## 2.2 የሰዋሰው ይዘቶች አደረጃጀት

በመማሪያ መጽሐፍ የቀረቡ ይዘቶች ግብ መቿ መሆን የሚችሉት አንዱ ሌላውን እያጠናከረ በሥርዓት ሲደራጅ ነው፡፡ በሥርዓት የተደራጁ የሰዋሰው ትምህርት ልምምድ ቀዳሚው ለተከታዩ መሰረት በሚሆን መልኩ ሊዋቀር ስለሚችል ውጤታማ ትምህርት ለማግኘት ከማገዙም በተጨማሪ ቀድሞ ያልተገነዘበውን እንዲገነዘብ፣ በመጀመሪያ ያገኘውን ትምህርት ተከትሎ የሚመጣውን ትምህርት ለማዳበር እንዲያግዘው ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርት ልምምዶች ሲደራጁ ደግሞ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ እያደገ እንዲዋቀሩ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Tyler(1949፣84) የትምህርት ይዘትን ለማደራጀት በምንነሳበት ጊዜ በትምህርቶቹ መካከል የሚኖረውን የጊዜና የቦታ ግንኙነት መመልከት እንዳለብን ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ አንፃር የትምህርት ይዘቶቹ ደረጃ በሁለት አይነት ሊታይ ይችላል ማለት ነው፡፡ ይህም ከአንደኛው በአንዱ የትምህርት ዓይነት ውስጥ የሚኖረውን ግንኙት የሚመለከት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በአንዱ ደረጃ በተለያዩ ትምህርት አይነቶች መካከል የሚኖረውን ዝምድና የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚህ ግንኙነቶች ተዋረዳዊ (ቀጥተኛ) እና ጎናዊ ግንኙነቶች ወይም የአደረጃጀት ስልቶች በመባል የሚታወቁ ናቸው፡፡

የዚህም ጥራት ትኩረት በአንድ የትምህርት አይነት የሚቀርብ ይዘት የሚመለከት በመሆኑ ጎናዊ አደረጃጀትን አይመለከትም፡፡ ምክንያቱም ውህደት ቀደም ሲል እንደተገለፀው በአንድ የክፍል ደረጃ ውስጥ በሚሰጡ የተለያዩ የትምህርት አይነቶች መካከል ያለውን ተዛምዶ ስለሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑትን ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ያለውን አደረጃጀት ስልቶችን ለማየት ጥረት አድርጓል፡፡

### 2.2.1 ተከታታይነት

እንደ Tyler(1994፣84) ገለፃ ተከታታይነት በአንድ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች በሚቀጥለው ምዕራፎች እየተከታተሉ መምጣታቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ በይዘቶች መካከል ያለውን ድግግሞሽ ተማሪዎቹ የተማሩትን ትምህርት የበለጠ እያጠናከሩት እንዲሄዱ ይረዳቸዋል፡፡ ትምህርት ረጅም ጊዜና የማያቋርጥ ክትትል የሚያሳይ ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን በውስን የትምህርት ይዘት የተፈለገው ትምህርት አላማ ግቡን ይመታል ተብሎ ስለሚታሰብ ተማሪዎች የተፈለገውን ለውጥ ያመጡ ዘንድ ተደጋጋሚነት ያላቸው የትምህርት ልምምዶች እየተደጋገመ ደረጃ በደረጃ መቅረብ ይኖርባቸዋል በማለት ያስቀምጣሉ፡፡

### 2.2.2 ተለጣጣቂነት

እንደ Laresen (1991) እና Tyler (1949) ገለፃ ተለጣጣቂነት ተዋረዳዊ የትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትን የሚመለከት ነው፡፡ በተከታታይ ክፍል ደረጃዎች በሚዘጋጁ የመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች ያላቸው ተዋረዳዊ ዝምድናና ተደጋጋፊነት የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ይዘቶች እርስ በራሳቸው ተሳስረው በመሄድ የተማሪው ቋንቋ ደረጃ እያደገ በሄደ ቁጥር በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ ያሉ ይዘቶችም ስፋትና ጥልቀት እያገኙ እንዲሄድ የሚያደርግበት አደረጃጀት ነው ይላሉ፡፡

### 2.2.3 የቋንቋ መርሃ ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍት

#### 2.2.3.1 የቋንቋ መርሃ ትምህርት

ይህ ጥናት ትኩረት በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ያደረገ ቢሆንም ለመማሪያ መጽሐፉ መነሻው መርሃ ትምህርቱ በመሆኑና ያላቸውንም ተያያዥነት ለመመልከት ይረዳ ዘንድ ስለመርሃ ትምህርት ምንነት በመጠኑም ቢሆን መመልከት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

መርሃ ትምህርት ከስርዓተ ትምህርት የሚነሳና ጠበብ ባለ መልኩ በአንድ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች በአንድ የትምህርት አይነት ምን መማር እንዳለባቸው የሚያመለክት ሰነድ ነው፡፡ በመሆኑም በውስጡ የትምህርቱን አላማ ግብ መምታት፣ ይዘት እና የይዘቱን አቀራረብ፣ የትምህርቱን ጊዜና አላማ የሚሸፈንበትን ግምገማ የያዘ ሰነድ ነው፡፡ Cunnigsworth(1995) እና Dubin and Olshtain (1986) መርሃ ትምህርት የህብረተሰቡንና የትምህርት ይዘቶችን መርጦ ለማደራጀት የሚያስችልና በአጠቃላይ በክፍል ውስጥ የሚደረጉ መማር ማስተማር ሂደትና ክንውኑችን ለመምራት የሚያስችል ሰነድ ነው፡፡ Ur (1996)፡፡

የቋንቋ መርሃ ትምህርት ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ የትኛውን እውቀት፣ ክህሎት እና እሴቶች መማር እንዳለባቸው፣ የታቀደውን ትምህርት ውጤት ለማምጣትምን ልምዶች ወይም ይዘቶች ሊታቀፉ እንደሚገባ የመማር ማስተማር ተግባር እንዴት እንደሚተገበር እና እንደሚገመገም የሚያመላክት ሰነድ ነው፡፡ Ur(1996)፡፡ አያይዘውም የቋንቋ መርሃ ትምህርት የትምህርቱን አቅጣጫ ከመምራቱም ባሻገር በታላሚው ቋንቋ በራስ የመተማመን ብቃት የሌላቸው መምህራንን የማበረታታት ድርሻ (ሚና) እንዳለው ይገልፃሉ፡፡

### 2.2.3.2 የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት

ሰዋሰው ተኮር የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳቦችን መነሻ አድርገው የሚዘጋጁ በመሆናቸው አላማቸው ቋንቋ ማስተማር ሆኖ አቀራረባቸው ግን የተለየ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ አንዳንዶች በሰዋሰው አንዳንዶች ደግሞ በተግባቦት ላይ ትኩረት የሚሰጡ ሆነው ይታያሉ፡፡ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት አይነቶችን አስመልክቶ ምሁራን የተለያዩ ስያሜዎችን ሲጠቀሙ ይስተዋላሉ፡፡ Grant(1987) የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሰዋሰው ተኮርና ተግባቦት ተኮር በማለት በሁለት ይከፍላቸዋል፡፡ በሌላ በኩል Dawsol (1984) የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትን መዋቂራዊ፣ ሁኔታዊና ግልጋሎታዊ ብለው በሦስት ይከፍላቸዋል፡፡ እነዚህ በምሁራን የተሰጡ ስያሜዎች የተለያዩ ይሁኑ እንጂ ይዘው ከተነሱት አላማ አንጻር በተመሳሳይ ፅንሰ ሀሳብ ዙሪያ የሚያውጠነጥኑ በመሆናቸው ያላቸውን የባህሪይ አንድነት በመመርኮዝ እንደ ሚከተለው አካቶ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### 2.2.3.3 የሰዋሰው ተኮር የመማሪያ መጽሐፍ

ሰዋሰው ተኮር የመማሪያ መጽሐፍት የመዋቅራዊ ስነ ልሳን ንድፈ ሀሳባዊ መሰረትነት ያለው ነው፡፡ በዚህ መማሪያ መጻህፍት አዘገጃጀት የቋንቋ ትምህርት ትኩረት የሚሰጠው ለቋንቋ ሰዋሰዋዊ ሥርዓት ነው፡፡ በቋንቋ ሰዋሰዋዊ ትክክለኛነት ላይ ተመስርቶ ታላሚውን ቋንቋ ለማስተማር በሚያስችል መንገድ የሚዘጋጅ ነው፡፡ የመጽሐፍት አዘገጃጀት ከተግባቦት ይልቅ ስርዓት ላይ ያነጣጠረ እንደመሆኑ የትምህርቱን አላማ ለማስፈፀም የሚመረጡ ይዘቶች ከቋንቋ ሰዋሰዋዊ ባህሪይ አንጻር በቅደም ተከተል የሚቀርብበት ነው፡፡

### 2.2.3.4 የተግባቦት ተኮር መማሪያ መጽሐፍ

ተግባቦት ተኮር የመማሪያ መጽሐፍ የማህበራዊ ስነ ልሳን ንድፈ ሀሳባዊ መሰረትነት ያለው ነው፡፡ ይህ የመማሪያ መጽሐፍት ቋንቋው ለተግባቦት ትምህርት በሰዋሰው ላይ ከማተኮር ሂደት ተከትሎ መዘጋጀት እንዳለበት የሚያምን ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ አቀራረብ በክፍል ውስጥ

የሚተገበሩት መስተጋብር አማካኝነት የተግባቦት ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ስለሆነም ከፍ ሲል በተጠቀሰው የፅነሰ ሀሳብ ዝምድና አንጻር በተግባቦት ተኮር የመማሪያ መጻህፍት ስር የሚመደቡ ናቸው፡፡

እንደ cook (2001) እና Larsoen free man (1991) በዘመናዊ የሰዋሰው ትምህርት እሳቤ ሰዋሰዋዊ ቅርፆችንና ህግጋትን ብቻ ማስተማተሩ ተቀባይነት የለውም፡፡ የሰዋሰው ትምህርት ትኩረት በቋንቋ ቅርፅ ወይም መዋቅር፣ፍቺና አጠቃቀም ላይ መሆን ይገባል፡፡

Palmer (1984) እንደሚሉት የሰዋሰው ትምህርት ትኩረት ተማሪዎች በቋንቋው ሰዋሰዋዊ እውቀት ላይ የተመሰረተ የተግባቦት ብቃት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡ ተማሪዎች የቋንቋውን ቅርፅ ከፍቺና ከአጠቃቀም ጋር አጣምረው በመማር ተገቢ የሆኑ አረፍተ ነገሮችን አፍልቀው እንዲፅፉ ወይም እንዲናገሩ፣ አድምጠው ወይም አንብበው መልዕክትን እንዲጨብጡ የሚያስችል የትምህርት ሂደትን የሚከተል መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡

ከላይ በምሁራን በተሰጠው ንድፈ ሀሳቦች መሠረት የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀትና አቀራረብ አስመልክቶ ከሚነሱ ነጥቦች መካከል በዚህ ጥናት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ከውጤት ተኮር ወደ ሂደት ተኮር እንዲሁም ሰዋሰውን እንደ ክፍሎች ማቅረብ የሚሉት ተተኳሪ ሆነዋል፡፡

## 2.3 የተዘማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ካላቸው የጥናት ስራዎች መካከል፡-

ሰሚራ አሊ (2010) በደቡብ ክልል በ2009ዓ.ም ሥራ ላይ ባዋለው "የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ "በሚል ለድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የቀረበ ጥናት ነው፡፡ አላማውም በደቡብ ክልል በ2009 ዓ.ም ሥራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የሰዋሰው ትምህርት ይዘች አቀራረብ እና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡

የጥናቱ ዘዴ አይነታዊውን የምርምር ዘዴ በመጠቀም በሰነድ ፍተሻ መረጃዎችን መፈተሽ የሚል ሲሆን፣ በጥናቱም የተገኘው ውጤት የይዘቶች አቀራረብ በተመለከተ ከአጠቃላይ ወደ

ዝርዝር ይልቅ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አብላጫውን ሽፋን እንደሚይዙ ጥናቱ ለመመልከት ችሏል፡፡

ተስፋዬ በቀለ (1993) "በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለ8ኛ ክፍል አማርኛ ኢ-አፈ-ፈት ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡

የጥናቱ አላማ አንደኛ በመልመጃዎች ውስጥ ትኩረት ለተሰጠው ለእያንዳንዱ ቅርፃዊ ስርዓቱና ፍቺው መቅረቡን መፈተሽ፣ ሁለተኛ ትኩረት የተሰጣቸው የሰዋሰው ግብአቶች አደረጃጀት ምን እንደሚመስል እና የሰዋሰው ከቅርፃዊ ስርዓታቸው ወደ ፍቻቸው ተደራጀው መቅረባቸውን መፈተሽና መገምገም ነው፡፡

የጥናት ዘዴውም አይነታዊ የምርምር ዘዴ አካል የሆነውን የገለፃ ዘዴ በመጠቀም ነው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያውም በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋሰው ይዘቶች አቀራረብ ላይ ሆኖ በዋናነት ጥናቱ መሰረት ያደረገው ምንባብ ላይ ነው፡፡ አጋዥ መረጃዎችን ለመሰብሰብ መምህራንና ተማሪዎችን ተጠቅሞ በጽሑፍ መጠይቆች አማካኝነት መረጃለ መሰብሰብ ችሏል፡፡

በመሆኑም የመረጃ አተናተን ዘዴው ደግሞ ከምንባቡ በወጡት መልመጃዎች፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች በገለጻ ትንተና ተሰጥቶባቸው፣ ከትንተና ውጤት ጋር ተያይዘው ተገልፀዋል፡፡ ውጤቱም የሰዋሰው መረጃዎች ለታላሚው ቋንቋ ቅርፃዊ ስርዓትና ለፍቺው ሚዛናዊ ትኩረት እንዳልሰጡ፣ ከዚህ አንፃር የተሰበሰቡት መረጃዎች አሳይተዋል፡፡ አንጻራዊ በሆነ አነጋገር ለቋንቋ ቅርጻዊ ስርዓት የሰጡት ትኩረት ከፍተኛ ሲሆን፣ ለፍቺው የሰጡት ትኩረት ግን በጣም አነስተኛ መሆኑን ከመረጃው ተሰብስበው ከተተነተኑት መረጃዎች ውጤት ለማየት ተችሏል፡፡

ከላይ የቀረቡት የጥናት ስራዎች ከአጥኚዋ ስራ ጋር ከርዕስ አንፃር ከተመረጠው የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተከተቱት የሰዋሰው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ላይ ተተኳሪ መሆን ሲያመሳስላቸው፣ እነዚህ የሰዋሰው ይዘቶች ከክፍል ውስጥ አተገባበር መሆንይለያያቸዋል፡፡

የሁለቱም ጥናት ስራዎች ዓላማ ትኩረት የሚደርገው በስራ ላይ በዋለው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት እና አቀራረብን መገምገም በሰነድ

ፍተሻ፣ በጽሑፍ መጠይቅ በመሆኑ መመሳሰል ቢታይም፣ ይኸው የሰዋሰው ይዘቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ምልከታ መሆኑ ይለያቸዋል፡፡

እንዲሁም የጥናት ዘዴው አይነታዊ የጥናት ዘዴ መሆን፣ ጥናቱን ሲያመሳስለው በሌላ በኩል ደግሞ የቀደሙት ጥናቶች ትኩረት በሰነድ ፍተሻ መሆን፣ የሁለተኛው ጥናት ደግሞ በጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን ሲጠቀም የአጥኚዋ ደግሞ በክፍል ምልከታና በቃለመጠይቅ መረጃ መሰብሰብ ይለያያቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት የጥናት ስራዎች ሰዋሰው ላይ ትኩረት ከማድረጋቸው አኳያ ሲታይ ከአጠኚዋ ስራ ጋር የሚያመሳስላቸው ዝምድና ቢኖርም ከመጽሐፉ አዲስ መሆን፣ ከክፍል ደረጃ፣ ከቦታና ከጥናቱ አካሄድ አንጻር ፍጹም ተመሳሳይ ወይም ተዛማጅ አይደሉም፡፡

እስሌማን አባይ(2003) በ1998 ዓ.ም ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ተሻሽሎ በተዘጋጀዉ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋሰዉ ትምህርትን  አደረጃጀትና አቀራረብ ከስነ መርሆች አንጻር መፈተሽ በሚል ርዕስ የቀረበ ነዉ፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ በ1998 ዓ.ም ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ተሻሽሎ በተዘጋጀዉ የአማርኛ መማረያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋሰዉ ይዘቶችን አደረጃጀትና አቀራረብ ከስነ ትምህርታዊ ሰዋሰዉ መርሆችን አንጻር መፈተሽ ሲሆን የግምገማ መስፈርቶች መሰረት በማድረግ በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ምን ያህል ስነ ትምህርታዊ ነዉ? የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ለቋንቋዉ ቅርጽ፣ ፍቺና አጠቃቀም የሰጡት ትኩረት ምን ያህል ስነ ትምህርታዊ ነዉ፣ የስነ ትምህርታዊ የሰዋሰዉ ይዞቶች ማደራጃና ማቅረቢያ መርሆች አንፃር የመማሪያ መጽሐፍ ሰዋሰዋዊ ይዘቶች ምን ጠንካራና ምንስ መሻሻል የሚኖርቡት ገጽታ አለ? የሚሉ 3ቁልፍ ጥያቄዎችን ይዞ የተነሳ ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር በመፍትሄ ሀሳቡ ላይ እንደሰፈረዉ ሰዋሰዋዊ ይዘቶቹ የታለሚዉን ቋንቋ ስነ ድምፅ፣ ስነ ምዕላድ፣ ስነ አገባብና ስነ ፍቻዊ ክፍሎችን የያዙ መልመጃዎችን በተለየዩ ክፍሎች በተደጋጋሚ ከማቀረብ አንጻር ጥሩ ገጽታ እንዳለዉ ግልጸዋል፡፡ በመቀጠልም የተተኳረዉ መጽሐፍ ከደረጃዉ መረሀ ትምህርት ጋር ያልተዛመደ ስለሆነ ለወደፊት የሚዘጋጁና ተሻሽለዉ የሚቀርቡ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት መረሃ ትምህርቱን መሠረት ያደረጉ ቢሆኑ፤

የታላሚዉን ቋንቋ ትክክለኛ ሰዋሰዋዊ ቅርጽ ማወቅና ቅርጹን ጠብቆ ተግባቡት ላይ ለማዋል የሚሉትን የወቅቱን የሰዋሰዉ ትምህርት አለማዎች ከማሳካት አንጻር የመማሪያ መጽሐፍ

የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች የቋንቋዉን ቅርጽ ከማስተማር አንጻር እንጂ ትምህርቱን ተግባቦት ላይ ለማዋል ደካማ ሆነዉ ተገኝተዋል በማለት አስፍሯል፡፡

የእስሌማን ጥናት ተተኳሪ ከደረገዉ ርዕስ ጉዳይ አንፃር ጥናቱ ጋር ይመሳሰላል፡- ነገር ግን ጥናቱ ትኩረት ያደረገዉ በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱት የሰዋሰዉ ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ተገቢነት እና የክፍል ዉስጥ አተገባበር ፍተሸ የሚል ሲሆን የእስሌማን ከስነትምህርታዊ መርሆች አንፃር መሆኑ ይለያየዋል፡፡ በተጨማሪም የእስሌማን የጥናት ተተኳሪ መማሪያ መጽሐፍ የ12ኛ ሲሆን የዚህ ጥናት ደግሞ "የ7ኛ" ክፍል መማሪያ መጽሐፍ መሆን በክፍል ደረጃ ይለያያሉ፡፡ በመረጃ አሰባሰብ አንፃርም ሠነድ ፍተሻ፣ ቃለ መጠይቅና የጽሁፍ መጠይቅ ከመሆን አንፃር ይመሳሰላሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት ደግሞ የክፍል ዉስጥ አተገባበርን ተመልክቷል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት ከቀደምት ጥናቶች የሚለይበት ዋና ዋና ውጤቶች

- የተተኳሪው መጽሐፍ የሰዋሰው ይዘቶች አደረጃጀት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ከውጤት ተኮር ወደ ሂደት ተኮር የተደራጀ መሆን፣ጥንካሬውን ሲያመለክት
- አደረጃጀቱ ለአራቱም አቀራረብ እኩል መጠን አለመስጠቱና የውጤት ተኮር በልጦ መገኘት እና በይዘቶች መካከል መበላለጥ መኖሩ አቀራረቡ ላይ ድክመት እንዳለ ማሳየቱ
- የይዘቶች መደጋገም አልፎ አልፎ መሆንና ተከታተይነቱን ጠብቆ ከከባድ ወደ ቀላል አለመጓዝ
- ከይዘቶች አደረጃጀት አንፃር ለሰዋሰው የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆን የዚህ ጥናት ሁለተኛ ትኩረት ከሆነው የክፍል ውስጥ ምልከታ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት በጣም ከፍተኛ 12 ተግባራት፣ከፍተኛ 20 ተግባራት፣መካከለኛ ነጥብ 26 ተግባራት እና ዝቅተኛ 17 ተግባራት በድግግሞሽ በተደረገው ምልከታ መምህራን የሰዋስው ይዘቶችን እንዴት እንደሚተገብሩ የሚያመለክት ውጤት መገኘቱን ጥናቱ በግልፅ ያሳያል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት
# የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

## 3.1 የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የሚከተል ሲሆን አቀራረቡም ገላጭ የምርምር ንድፍን መሰረት ያደረገ ነው፡፡

## 3.2 የጥናቱ አካላይ

በደቡብ ክልላዊ መንግስት በአማርኛ ቋንቋ ለ7ኛ ክፍል እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ተገቢነት እና የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ፣ በሸካ ዞን በማሻ ከተማ አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ7ኛ ክፍል ተማሪዎችና የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ተተኳሪነት ነው፡፡

## 3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

"አንድ ተመራማሪ ጥናት ለማካሄድ በሚያስብበት ወቅት ከችግሩ ባልተለየ ሁኔታ ሊያውቀው የሚገባው ዋና ጉዳይ ጥናቱ በማን ላይ ይካሄዳል? የሚለው ነገር ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፍዎች ተለይተውና ተወስነው ካልታወቁ የችግሩ መፍትሄ ለመለየትም ሆነ ራሱን ምርምሩን ለማካሄድ አስቸጋሪ ነው፡፡" በማለት ያለው እንዳወቅ (2009፣123) ያስረዳሉ፡፡ ይህንን መሰረተ ሀሳብ መነሻ በማድረግ አጥኚዋ ለጥናትዋ ወካይ የሚሆኑ ናሙናዎችን እንደሚከተለው ታቀርባለች፡፡

### 3.3.1 የት/ቤት ናሙና አመራረጥ

በደቡብ ክልል ከሚገኙ ዞኖች መካከል አንዱ የሸካ ዞን ሲሆን፣በዚሁ ዞን ከሚገኙት ከተሞች ውስጥ ማሻ ከተማ በአመቺ ናሙና ተመርጧል፡፡ ከተማዉ የተመረጠበት ምክንያት የዚሁ ጥናት አቅራቢ የምትኖርበት ከተማ በመሆኑና አስፈላጊ መረጃዎችን በቅርበት ለመሰብሰብ ስለሚያመች ነዉ፡፡ በናሙናነት በተመረጠው ከተማ ውስጥ አራት መለስተኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሲሆን፣ አራቱም ባጠቅላይ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑና ሁሉንም በማሳተፍ በቂ መረጃ ለማግኘት ታስቦ ነው፡፡

### 3.3.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በደቡብ ክልላዊ መንግስት ለአንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ሣይክል (ከ5-8) አማርኛን እንደ አፊ-ፊት ለሚማሩ ተማሪዎች ተዘጋጅተው ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ በዋለው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ከመርሃ ትምህርቱ አንፃር ያለውን ተገቢነት እና የክፍል ውስጥ አተገባበር ለመፈተሽ የ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በአላማ ተኮር ናሙና ተመርጧል፡፡ ምክንያቱም ከጥናቱ ዓላማ አንፃር ተተኳሪው መፅሀፍ ተመርጧል፡፡ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካትና አስፈላጊውን መረጃ ላገኝበት እችላለሁ በማለት አጥኚዋ የደረጋውን መፅሀፍ በዓላማ ተኮረ ናሙና ዘዴ መርጣለች፡፡

የቀሩት (5ኛ፣6ኛእና 8ኛ) ክፍሎች መማሪያ መጽሐፍት በዚህ ጥናት ውስጥ አልተካተቱም፡፡ ምክንያቱም ለጥናቱ ከተመደበው ጊዜና የገንዘብ ውስንነት አንጻር ነው፡፡

### 3.3.2 የተማሪ ናሙና አመራረጥ

በማሻ ከተማ ውስጥ ከሚገኙት አራት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ አማርኛ ቋንቋን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ እየተማሩ ያሉት የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ወንድ 218 ሴት 92 በድምሩ 400 ሲሆኑ ከእነዚህም ውስ ወንድ 60 ሴት 40 በድምሩ 100 ተማሪዎች በጥናቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተመርጠዋል፡፡ ናሙና ተማሪዎችን ለመምረጥ ተራ የዕጣ ናሙና ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

### 3.3.3. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በደቡብ ክልል በሸካ ዞን በማሻ ከተማ ውስጥ ካሉት አራት አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ የሚያስተምሩ ወንድ 1 ሴት 3 ድምር 4 መምህራን ሲሆኑ፣አራቱም ባጠቅላይ ናሙና ተመርጠዋል፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በጥቅም ላይ የዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ የሆነው ዋነኛው የሰነድ ፍተሻ እና የክፍል ምልከታ ሲሆኑ የጽሑፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ አጋዥ መረጃ መሰብሰቢያዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በቅደም ተከተላቸው መሰረት ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

### 3.4.1. የሰነድ ፍተሻ

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አቢይ የመረጃ መሰብቢያ መሳሪያ የሆነው የሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት የሚያገለግለው በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ በ2007 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በ2009 ዓ.ም በስራ ላይ የዋለው የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ናቸው፡፡

መማሪያ መጽሐፉ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያለው ዝምድና ተፈትሾ የተገኘው መረጃ በሰንጠረዡ ውስጥ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

### 3.4.2 ምልከታ

ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎች መካከል አንዱ ምልከታ ሲሆን የ7ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ይዘቶች በክፍል ውስጥ አተገባበራቸው ምን እንደሚመስል ወይም በምን ዐይነት ስልት እና ሁኔታ እንደሚተገበሩ ዝርዝር አጀንዳ (Chek list) በመታገዝ በአጥኚዋ አማካይነት የሰዋሰው ትምህርት የሚሰጥበትን በመለየት አራቱም መምህራን በሚያስተማሩበት ትምህርት ቤት በመገኘት በአራቱም ክፍል ሁለት ሁለት ዙር በአጠቃላይ ለ8 ተከታታይ ጊዜ የክፍል ምልከታ ተደርጓል፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት የሰዋሰው ትምህርቱን መምህራን በክፍል ውስጥ እንዴት እንደሚተገብሩ በመመልከትና ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ሲባል ነው፡፡

### 3.4.3 የጽሑፍ መጠይቅ

“ የጽሁፍ መጠይቅ ከሌሎቹ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሚለየው ተመራማሪው ለማጥናት በሚፈልገው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ጥያቄዎችን በጽሁፍ አዘጋጅቶና አንደ አስፈላጊነቱም የጥናቱን አላማ ገልጸ ለተጠኚዎች በመስጠት መረጃውን መሰብሰብ መቻሉ ነው፡፡” ያለው እንዳወቅ (2011፣148) በማለት ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሐፉ እየተገለገሉ ከሚገኙት ወንድ 218 ሴት 92 ድምር 400 የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች መካከል 25%ቱን በመውሰድ ወንድ 60 ሴት 40 ድምር 100 ተማሪዎች በተራ ዕጣ ናሙና ዘዴ በመምረጥ የጽሁፍ መጠይቅ ተካሂዷል፡፡

### 3.4.4 ቃለ መጠይቅ

ከላይ ከተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎች በተጨማሪ ቃለ መጠይቅ ነው በጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍል ደረጃ በክፍል ውስጥ የሰዋሰው ይዘቶችን የሚተገብሩትን

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከፊል ነፃ በሆነ ቃለ መጠይቅ አማካይነት ለጥናቱ አጋዥ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ በመጠቀም በሰነድ ፍተሻና በክፍል ውስጥ ምልከታ ተፈትሸው የተገኙት መረጃዎች እንደ አስፈላጊነቱ በቂ ማባራሪያና ገለፃ ተሰጥቶባቸው በሰንጠረዥ ውስጥ በገላጭ ስልት ቀርበዋል፡፡ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ይዘቶች በክለሳ ድርሳን የቀረቡ ንድፈ ሀሳቦችን መሠረት በማድረግ የሰዋሰው ትምህርት ይዘት አደረጃጀትና አቀራረብ ምን እንደሚመስል፣ የመልመጃዎች አቀራረብ ተፈትሾና ተተንትኖ በገላጭ መልክ ቀርቧል፡፡ በሠነድ ፍተሻው መሠረት በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያለው ዝምድናና ትስስሮች ተፈትሾ በሰንጠረዥ ውስጥ ቀርቧል፡፡ የይዘቶችን አተገባበር በተመለከተ በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታ አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ ውጤት በተገቢ ሁኔታ ተተንትኖ በሠንጠረዥ መልክ ቀርቧል፡፡

በፅሁፍ መጠይቅ ከተማሪዎች የተሰበሰበ መረጃ ጥያቄውና የተገኘው ምላሽ በሠንጠረዥ ውስጥ በገለፃ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ከዚሁ ጋር ተዛማጅነት አላቸው ተብለው የሚገመቱ ነጥቦች 7ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ለሚያስተምሩ መምህራን በቃለ መጠይቅ ቀርቦ የተሰበሰበው መረጃ ገለፃና ማብራሪያ ተሰጥቶበት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ከሰነድ ፍተሻና ከክፍል ውስጥ ምልከታ የተሰበሰቡት መረጃዎች የጥናቱ አብይ መረጃዎች ሲሆኑ ከመምህራንና ከተማሪዎች ማለትም ከቃለ መጠይቅና ከጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች አጋዥ ናቸው፡፡ በዚህ ሁኔታ ከሁሉም የተገኙት የመረጃ አይነቶች ተደጋጋፊነት ሊኖራቸው በሚችሉበት መልክ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1. የመማሪያ መጽሐፉ አጠቃላይ ቅኝት

የ7ኛ ክፍል የአማርኛ መማርያ መጽሀፍ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ለክልሉ እንዲስማማ ተደርጎ በ2007 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በ2009 ዓ.ም ስራ ላይ የዋለዉ ሲሆን መጽሀፉ 237 የገጽ ብዛት አለዉ የመማርያ መጽሀፍ የተዘጋጀበት አላማ የደረጃዉ ተማሪዎች በታላሚዉ ቋንቋ በብቃት ማንበብ፣ መጻፍ፣ ማዳመጥና መናገር እንዲችሉ ለማድረግ እንደሆነ በመግቢያዉ ላይ ተጠቅሷል፡፡

ተተኳሪዉ መማሪያ መጽሐፍ አስር ምዕራፎች ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ምዕራፍ የራሱ የምንባብ ይዘት ያለዉና አንዱ ምዕራፍ በሶስት ሳምንታት እና በዘጠኝ ቀናት ተከፋፍሎ እያንዳንዱ ምዕራፍ ስምንት የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች አቅፎ ይዟል ወይም ቀርቧል፡፡

እነዚህ የመጽሀፍ ይዘቶች አደረጃጀት የቃላት ጥናት፣አንብቦ መረዳት፣ቃላት፣ መጻፍ፣ አቀላጥፎ ማንበብ፣ ቃላዊ ክህሎች(ማዳመጥና መናገር)፣ ሰዋሰዉ በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ተደራጅቶ ቀርቧል፡፡ እያንዳንዱም የምንባብ ይዘት ሶስት ርዕሰ ጉዳዮችና አራት ምንባቦች አሉት፡፡ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮቹ ተማሪዎች በቋንቋቸዉ እንዲናገሩ፣ እንዲያዳምጡ፣ እንዲያነቡና አንዲጽፉ እንደ መነሻ ያገለግላቸዋል፡፡

በአጠቃላይ በደቡብ ክልል የ7ኛ ክፍል የአማርኛ መማርያ መጽሀፍ ዉስጥ የተካተቱ የተለያየ ይዘት ካላቸዉ 361(ሦስት መቶ ሰላሳ አንድ) መልመጃዎች ወይም ተግባራት መካከል ሰዋሰዉ ላይ የተመሰረቱ ይዘቶች 32(ሠላሳ ሁለት ናቸዉ)፡፡

መጽሀፉ ከተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች የሚያወሱ በዝርዉና በግጥም አስር ዋና ርዕሶችን መሰረት ያደረጉ 30 ምንባቦችና 20 አጫጭር ገለጻዎች (ማብራሪያዎች) አሉት፡፡ የሰዋሰዉ ትምህርት ላይ ትኩረታቸዉን አድርገዉ የተጻፉ ገለጻዎች 11 (አስራ አንድ) ናቸዉ፡፡ ይህንን ሁኔታ በሚከተለዉ ሰንጠረዥ መመልከት ይችላል፡፡

## ሰንጠረዥ 1፦የሰባተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማርያ መጽሐፍ አጠቃላይ ቅኝት

| ምዕራፍ | የምዕራፍ ዋና ርዕሶች | የምንባቦች ርዕሶች | የምንባቡ አይነት | የቀረበዉ መልመጃ ብዛት | የቀረበዉ የሰዋሰዉ መልመጃ ብዛት | የቀረበዉ ገለጻ ብዛት | የቀረበዉ የሰዋሰዉ ገለጻብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተፈጥሮን ማድነቅ | መስዕቦቻችን | ኢልቦለድ | 13 | 1 | 3 | 1 |
| | | ጉዞ ወደ ጊቤ ሸሎቆ ብሔራዊ ፓርክ | | 9 | 1 | - | - |
| | | የአፈር እንክብካቤ | | 12 | 1 | - | - |
| 2 | የቤተሰብ ምጣኔ | የቤተሰብ ምጣኔ ምንነት | ኢልቦለድ | 12 | 1 | 1 | 1 |
| | | ስለቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ አመለካከቶች | | 11 | 1 | - | - |
| | | የሕፃናት አንክብካቤ | | 12 | 1 | - | - |
| 3 | ኤች.አይ.ቪ. ኤድስና ማህበራዊ ቀዉስ | ኤች.አይ. ቪ. | ኢልቦለድ | 14 | 1 | 2 | 1 |
| | | ወይ አለማወቅ | | 10 | 1 | 3 | 1 |
| | | የኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ተጽዕኖ | | 13 | 1 | 1 | - |
| 4 | ታዋቂ የኪነ ጥበብ ሰዎች | የኢትዮጲያ ፋና ወጊ የሙዚቃ አቀናባሪ | ኢልቦለድ | 9 | 1 | 2 | 1 |
| | | የዉሎ ማስታወሻ | | 10 | 1 | 1 | 1 |
| | | እጅግ የተከበሩ የአለም ሎሬት | | 10 | 1 | - | - |
| 5 | ዉሃና ጥቅሙ | ፋጡማና የዉሃ አጠቃቀም | ኢልቦለድ | 14 | 1 | 1 | 1 |
| | | ዉሃና ህይወት | | 11 | 1 | 2 | 1 |
| | | የዉሃ አጠቃቀም | | 12 | 1 | - | - |
| 6 | ማህበራዊ ግንኙነት | ከሞት ጋር ዉድድር | ኢልቦለድ | 14 | 1 | 2 | 1 |
| | | በላ ልበልህ | | 8 | 1 | - | - |
| | | እርስ በእርስ መረዳዳት | | 13 | 1 | -- | - |
| 7 | ሱስ | ጫት መቃምና መዘዙ | ኢልቦለድ | 14 | 1 | 1 | 1 |
| | | የሱሰኝነት ተጽዕኖ | | 11 | 1 | -- | - |
| | | ከሱሰኝነት ነጻ መዉጣት | | 13 | 1 | -- | - |
| 8 | አርበኝነት | እቴጌ ጣይቱ ብጡል | ኢልቦለድ | 13 | 1 | - | - |
| | | የሀገር ፍቅር | | 10 | 1 | - | - |
| | | ማህበረሰብን ማገልገል | | 14 | 2 | - | - |
| 9 | ተላላፊ በሽታዎች | ተላላፊ በሽታዎች | ኢልቦለድ | 16 | 1 | 1 | 1 |
| | | የቲቢ በሽታ | | 12 | 2 | - | - |
| | | ተላላፊ በሽታዎችን መከላከለ | | 14 | 1 | - | - |
| 10 | ቃላዊ ግጥም | የተጻፈና ያልተጻፈ ግጥም | | 15 | 1 | - | - |
| | | ቃላዊ ግጥሞች(የቃላዊ ግጥም አይነቶች) | ግጥም | 11 | 1 | - | - |
| | | ስነ ቃልን ማድነቅ (ቃላዊ ግጥሞች) | | 11 | 1 | - | - |
| | | | | 361 | 30 | 20 | 11 |

## 4.2. በመማርያ መጽሀፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

### 4.2.1. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ

የሰዋሰዉ ትምህርት ዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ስልት ተማሪዎች በመማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የቀረቡትን የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች በምሳሌዎች እየታገዙ መልመጃዎችንና ተግባራትን ከሰሩ በኃላ በሂደት የቋንቋን ሰዋሰዋዊ ሥረዓት በራሳቸዉ ጥረት እንዲደርሱበትና አቅም እንዲፈጥሩ የሚያደርግ አቀራረብ መሆኑን በክለሳ ድርሳን ላይ ተጠቁሟል፡፡

በመማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ምሳሌ ጠቅሰዉ የቀረቡ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች በርካታ ናቸዉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ቀጥሎ የቀረቡት ይገኙበታል፡፡

"ቀጥለዉ የቀረቡትን በክፍት ቦታዉ በማስገባት ዓረፍተ ነገሮችን አሟሉ" ከሚል ትዕዛዝ ሥር የሚከተለዉ ምሳሌ ይገኛል፡፡

ምሳሌ፤-1.ፋጡማ ጎበዝ ናት፣ ነገር ግን ፈተናዉን አላለፈችም፡፡

2.ዳዊት ንቁ ዓምሮ አለዉ፣ ስለዚህነገሮችን ቶሎ ይገነዘባል፡፡

(ገጽ ፣ 32-33)

ከላይ የቀረበዉ ይዘት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረበ ነዉ፡፡ በመሆኑም በምሳሌዉ እንደተገነዘብነዉ የተሰመረበትና በክፈት ቦታ የገባዉ በአያያዥ ቃልነት ነዉ፡፡ በአረፈተ ነገር ዉስጥ የገባዉ ዳግም በሁለቱም ምሳሌዎች እንደሚታየዉ ምሳሌ 1 ሁለት የተለያየ ሀሳብ ያላቸዉን አረፍተ ነገር ለማያያዝ ነዉ፡፡ በምሳሌ 2 የገባዉ ቃል ወይም አያያዥ የገባዉ ሁለት ተደጋጋፊ ሀሳብ ያላቸዉን አረፍተ ነገሮች ለማያያዝና የተሟላ ሀሳብ ለመስጠት ነዉ፡፡ ስለዚህ በቀረበዉ ምሳሌ በመደገፍ ተማሪዎች የቋቋዉን ሰዋሰዋዊ ስረዓት እንዲያዉቁ መደረጉና ይዘቱ ደግሞ መረሃ ትምህርቱ ላይ ተመስርቶ መቅረቡ ጥንካሬዉን ያሳያል፡፡ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ከቀረቡት ይዘቶች መካከል በምዕራፍ ስድስት ስለ ዉስብስብ አረፍተ ነገር የቀረበዉ ይጠቀሳል፡፡ በመረሀ ትምህርቱ ላይ እንደተጠቆመዉ በቅድሚያ ተማሪዎች አያያዦችን የሚሳዩ ቃላትን እንዲለዩና ቀጥሎም እንዲጠቀሙ ያደርጋል፡፡ በዚሁ መሰረት፡- ቀጥሎ የቀረቡትን አያያዦች በመጠቀም በምሳሌዉ መሰረት አምስት ዉስብስብ አረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እና | ደግሞ | ግን | ነገርግን | እንጂ | ይሁን እንጂ |

ገፅ 127

ምሳሌ፡- በጠዋት ወደ ስራ ገባሁ፡፡

እስካሁን የሰራሁት የለም፡፡

በጠዋት ወደ ስራ ልግባ እንጂ እስካሁን የሰራሁት ስራ የለም፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ ስለ አያያዥ ለማስተማር የቀረበዉ ይዘት ትዕዛዝ ላይ ደግሞ አያያዥን በመጠቀም አምስት ዉስብስብ አረፍተ ነገሮች መስርቱ(ጻፉ) ይላል፡፡ በምሳሌዉ ላይ እንደምንረዳዉ አያያዥን በመጠቀም ሁለት ተራ ዓረፍተ ነገሮችን በአንድ ላይ አያይዞታል፡፡ ስለሆነም አያያዥን በመጠቀም ዉስብስብ አረፍተ ነገሮችን ተማሪዎች ሲሰሩ ከቀረበላቸዉ ጥያቄ በመነሳት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ እንደሚጓዙ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመረሃ ትምህርቱ እንደተጠቆመዉ ተማሪዎች አያያዦችን ከለዩ በኃላ በጽሁፉ ዉስጥ ይጠቀማሉ፡፡

በሌላ በኩል በገጽ 230 በተሰጠዉ ተግባር *ሥራ* ስር ማን፣ ምን፣መቼ፣ እንዴት፣ ወይ የሚሉትን ቃላት በመጠቀም አምስት አረፍተ ነገሮችን እዲመሰርቱ ያዛል፡፡እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን መጠይቃዊ ቃላት ለይቶ በመገንዘብ ማለትም ስለእያንዳዳቸዉ ምንነትና አይነት ለማወቅ ገለጻ ሳያስፈልጋቸዉ አንዳቸዉን ከሌላቸዉ መለየት ከተማሪዎች የሚጠበቅ ተግባር ነዉ፡፡ በመለየቱ ሂደትም ምንነታቸዉንና አገልግሎታቸዉን አየለዩ የመሄድ አጋጣሚ ይኖራቸዋል፡፡ በገጽ (147) ላይ በቀረበዉ መልመጃ መሰረት የሚከተለዉ ይገኝበታል፡፡

የሚከተሉትን ጥገኛ አረፍተ ነገሮችን በምሳሌዉ መሰረት አሟልታቹ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- ሑሰኝነት ሰዎችን ስለሚጎዳ.....

ሑሰኝነት ሰዎችን ስለሚጎዳ ከሑስ ነጻ እንሁን፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ ስለ ጥገኛ አረፍተ ነገር ማስተማር በቀረበዉ ይዘት ትዕዛዝ ስር ጥገኛ አረፈተ ነገሮችን በምሳሌዉ መሰረት አሟልታችሁ ጻፉ የሚል ይገኝበታል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን ምሳሌዉ በቂ ባይሆንም ተማሪዎች መተግበር እንደሚችሉ ቢገመትም ይዘቱ ከመረሃ ትምህርቱ ያላፈነገጠ መሆኑን ማወቅ ተችሏል፡፡

በገጽ (13) ድርብ አረፍት ነገሮችን መነጠል በሚል ተግባር ስር አያያዦችን በመጠቀም ድርብ አረፍተ ነገሮችን ተመስርተዋል፡፡ እነዚህ ድርብ አረፍተ ነገሮች በመነጣጠል የተለያዩ ነጠላ አረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡ ይልና ለምሳሌ

"የሀዋሳ ከተማ ሞቃት የአየር ጠባይ አላት፣ ነገር ግን ከሰዓት በኃላ ነፋሻ አየር ይነፍስበታል" የሚለዉ አረፍተ ነገር "ሀዋሳ ከተማ ከሞቃት የአየር ጠባይ አላት" እና ሀዋሳ ከተማ ከሰዓት በኃላ ነፋሻ አየር ይነፍስባታል" የሚሉ ሁለት ነጠላ አረፍተ ነገሮችን ይዟል፡፡ በዚሁ መሰረት ተማሪዎች የተቀሩትን እንዲሠሩ ተደርጓል፡፡

ሀ. ዳዉሮ ዞን ወጣ ገባ የመሬት አቀማመጥ አለት፣ይሁን እንጂ የአየር ጠባዩ ለኑሮ ተስማሚ ነዉ፡

ለ.ልጁ ልብሱን አጥቧል፣ ነገር ግን ልብሱ በሚገባ አልጸዳለትም፡፡

ሐ.አፈርና ዉሃ ለኑሮአችን አስፈላጊዎች ናቸዉ፣ ስለዚህ ለአፈርና ዉሃ አስፈላጊዉን እንክብካቤ እናድርግላቸዉ፡፡

መ.የአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ ሰፊ ነዉ፣ እንዲሁም አስደሳች ነዉ፡፡

ሠ.አባትየዉ ልጁን ወደ ሸርሸር ቦታ ወሰደው፣ ልጁ ደግሞ የጎበነኘዉን አደነቀ፡፡ የሚሉት ናቸዉ፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ድርብ አረፍተ ነገሮች አሉታዊና አዎንታዊ የሆኑ አያያዦችን በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን ነጣጥለዉ የየራሳቸዉን ነጠላ ትርጉም እንዲሰጡ አድርጎ መስራት ከተማሪዎች የሚጠበቅ ተግባር ነዉ፡፡ በዚህ ሂደትም የአያያዦችን አገልግሎትና ተገቢ ቦታቸዉን ለይተዉ እንዲጠቀሙ የሚረዳቸዉ መልመጃ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በተደረገዉ የሰነድ ፈተሸ በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ለናሙናነት ከተተቀሱት ሌላ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረቡ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያየ ዘርፍ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ የቀረቡላቸዉን ምሳሌዎች ተከትለዉ በመስራት ብቻ የቋንቋዉን ሰዋሰዋዊ ስርዓት በቀላሉ ይረዱታል ማለት አይደለም፡፡ በመማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋሰዉ መልመጃዎችን ከዝርዘር ወደ አጠቃላይ ስልት ተከትለዉ የቀረቡ ይሁኑ እንጂ ምሳሌዎችን ብቻ መሰረት አድርገዉ የሚሰሩት መልመጃዎች ሁሉም ተማሪዎች በተመጣጣኝ

ሁኔታ ትክክለኛ የሆነዉን የቋንቋ ህግ በራሳቸዉ ለማወቅ ሊከብዳቸዉ ይችላል፡፡ ይህም የተባለበት ምክንያት አንድ ትዕዛዝ ነጠላ ጉዳዮች ላይ ብቻ የሚያተኩር አይደለም፡፡ ይህም ሲባል ዉስን ጉዳዮቹ ብቻ ይጠየቅ ወይም ትኩረት ይደረግበት ለማለት አይደለም፡፡ በአንድ ይዘት ዉስጥ ከአንድ በላይ ጉዳዮች መቅረባቸዉ የይዘቶቹን ተያያዥነት ተማሪዎች እያወቁ እንዲሄዱ ማስቻሉ ጥሩ ጎን አለዉ፡፡ ነገር ግን እንደ ይዘቱ፣ አደረጃጀቱና እንደ አቀራረቡ ይለያያል፡፡ በመረሀ ትምህርቱ የተጠቀሙ ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ መኖራቸዉ ከጠንካራ ጎን እንዲጠቀስ ያደርጋል፡፡

### 4.2.2. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ

በዚህ አቀራረብ ስልት በመጀመርያ የቀረበዉን የሰዋሰዉ ይዘት አስመልክቶ የቋንቋዉ ሥርዓት የሚፈቅደዉን ወይም የሚከተለዉን ህግ መነሻ ያደረገ ማብራሪያና ትንታኔ በመስጠት ተማሪዎች ህጉን መነሻ በማድረግ የሚቀርቡላቸዉን መልመጃዎች እንዲሰሩ የሚያስችል አቀራረብ ነዉ፡፡

በ7ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጽሀፍ ላይ በተደረገዉ የሰነድ ፍተሸ መሰረት 10(አስር) የሚሆኑት የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ማብራሪያ የተሰጠባቸዉ ሲሆን በመጽሐፍ ዉስጥ ገለጻ የተሰጠባቸዉ የሰዋሰዉ ትምህርት የዘቶች ስለአያያዥ በገጽ (8) ፣ መስተዋድድ ገጽ (27) ፣ጠቋሚ መስተዓምርና፣ የመሆን ግስ ገጽ (54-55) ፣ ተዉሳከ ግስ ፣ ገጽ(70) ፣ መደብ ገጽ(76-77) ፣አዉንታዊና አሉታዉ አረፍተ ነገሮች ገጽ(94-95) ፣ መጠይቃዊ ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች ገፅ(102) ፣ ዉስብስብ ዓረፍተ ነገርን መመስረት ገፅ(119-120) እና ጥገኛ ዓረፍተ ነገር ገፅ(141) ላይ አጫጭር ማብራሪያዎች ቀርበዋል፡፡

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ከጥቅል ሰዋሰዋዊ በህሪያቸዉ ወደ ዝርዝር በህሪያቸዉ መቅረባቸዉን ያሳያል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ ገለፃ የተሰጠባቸዉን የሰዋሰዉ ትምህረት ይዘቶች በሚመለከት፡-

| |
|---|
| አያያዦች በሁለት ነጠላ ዓረፍተ ነገሮች መካከል እየገቡ አረፍተነገሮችን ወደ ድርብ ዓረፍተ ነገር መለወጥ የሚያስችሉ ናቸዉ፡፡ እነርሱም፡- እና፣ ግን፣ ነገር ግን፣ እንጂ ወዘተ ናቸዉ፡፡ |

ቀጥሎ በተሰጡት ድርብ ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ያሉትን አያያዦች አስምሩባቸዉ

ሀ. ደመናዉ ዳመነ እንጂ፣ዝናቡ አልዘነበም፡፡

ለ. ከድጃ ትምህርት ቤት መጣች፣ ግን ክፍል ዉስጥ አልገባችም፡፡

ሐ. ብርክታዊት ሀኪም ናት እንጂ፣ ፖሊሲ አይደለችም፡፡

መ. ጅብሪል ድርሰት ጻፈና ለህትመት አበቃ፡፡

ሠ. የአባይ ግድብ ሰዉ ሰራሽ ነዉ እንጂ፣ ተፈጥሮአዊ አይደለም፡፡

ረ. ከድር የተፈጥሮ አከባቢን ማድነቅ ይወዳል፣ ሔደን ግን ልቦለድ ፅሁፎችን ማንበብ ትወዳለች፡፡

ገፅ/8/

ከላይ ስለአያያዦች የቀረበዉ አጭር ገለፃ መሰረት አድርገዉ የተሰጠዉን ተግባር ወይም መልመጃ እንዲሰሩ የቀረበዉ ማብራሪያ ተማሪዎች ግንዛቤ ኖሯቸዉ ወደ ተግባር እንዲገቡ ያግዛቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የተሰጠዉ ገለፃ በምሳሌ ቢደገፍ ተጽፎ ቢቀርብ ኖሮ የበለጠ እገዛ ያደርግ ነበር፡፡

በመማሪያ መጽሐፍ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ገለፃና ምሣሌዎች ተሰጥቶባቸዉ ቀርበዋል፡፡ ገለፃ ከተሰጠባቸዉ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል መስተዋድድ ይገኝበታል፡፡ እንደሚከተለዉ እንመለከታለን፡፡

| |
|---|
| መስተዋድድ አንድን አረፍተ ነገር እንዲያስር አድርጎ ከሌላ አረፍተ ነገር ጋር እንዲጠጋ የሚያደርግ ነዉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ስለ-፣እንደ-፣ከ-፣ለ-፣ወደ- እና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ |

በጥንድ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች በመስተዋድድ በማያያዝ ዉስብስብ አረፍተ ነገሮች መስርቱ፡፡

**<u>ምሳሌ</u>፡-** አህመድ ቶሎ መጣ፡፡

አህመድ ደብተሩን አገኘ፡፡

አህመድ ቶሎ ስለመጣ ደብተሩን አገኘ፡፡

ሀ. ጋሻዉ በሰዓቱ ሥራዉን አጠናቀቀ፡፡

ጋሻዉ በጊዜ ወደ ቤቱ አመራ፡፡

ለ. ፋጡማ ከጓደኞቿ ጋር ተባበረች፡፡

ፋጡማ ስራዋን በጥሩ ሁኔታ ታከናዉናለች፡፡

ሐ. አቶ አለማየሁ የቀበሌያችን እናቶችና ህፃናት ጤና ባለሙያ ሆነ፡፡

አቶ አለማየሁን ስለቤተሰብ ምጣኔ እጠይቀዋለሁ፡፡

ገፅ/27/

ከላይ ስለመስተዋድ የቀረበዉ ማብራሪያ ወይም ገላፃ ለተማሪዉ ግልፅ በሆነ መንገድ አልቀረበም ምክንያቱም "አንድን አረፍተ ነገር ግስ እዳያስር አድርጎ ከሌላ አረፍተነገር ጋር እንዲጠጋ" ተብሎ የቀረበዉ ገለፃ እንዲጠጋ ብሎ ከማለት ሁለት አረፍተ ነገሮች እንዲገናኙ ያደርጋል ተብሎ ቢቀርብ የተሸለ ይሆን ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መስተዋድድ ተብለዉ ከተዘረዘሩት ዉስጥ በመልመጃ ዉስጥ ግሱን ጥገኛ እንዲሆን ወይም እንዳያስር ሊያደርግ የሚችለዉ "ስለ" ብቻ ነዉ፡፡ ስለዚህ የቀረበዉ መልመጃ ሁሉንም መነካካት መቻል አለበት፡፡

በገለፃና በምሳሌ ተደግፎ ከቀረበዉ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች አንዱ ጠቋሚ መስተአምርና የመሆን ግስ ነዉ፡፡ ይህንንም እንደሚከተለዉ ማየት ይቻላል፡፡

**<u>ምሳሌ</u>**፡- "እነዚያ ዋልያዎች ናቸዉ" በሚለዉ አረፍተ ነገር ዉስጥ "ናቸዉ" የሚለዉ የመሆን ግስ ሲሆን፣ "ዋልያዎች" የሚለዉ ስም ደግሞ ለመሆን ግሱ መሙያ ነዉ፡፡ "እነዚያ" የሚለዉ መስተዓምር ስሙን ይጠቁማል፡፡

ቀጥሎ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች የጠቋሚ መስተአምሩንና የመሆን ግሱን ቦታበ መጠበቅ አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡

**ሀ.** እነዚያ ናቸው በጎች፡፡ **ለ.** ግመል ነው ይህ፡፡ **ሐ.** ተራራ ያ ነው፡፡ **መ.** ተያቢ ናት ይቺ፡፡

**ሠ.** ሀውልቶች ናቸው እነዚያ፡፡

ገጽ /54-55/

ከላይ ከቀረበው ገለፃ እና ምሳሌ እንደምንመለከተው የመሆን ግሶች መሆንን ወይም ሁነትን የሚገልፁ ግሶች ሲሆኑ ስምን በመሙያነት እንደሚወስዱ፣የመሆን ግሶችን የሚባሉት ደግሞ "ሆነ"፣ነው፣ናት፣ናቸው" የሚሉትና ጠቋሚ መስተ አዕምሮች ደግሞ በመሙያነት ከሚገባው ስም ቀድመው በመምጣት ጠቋሚውን ስም ከሚገኝበት ቦታ አንፃር የመጠቆም ተግባር እንደሚያከናውኑ በተመጠነ መንገድ ተካቶ ቀርቧል፡፡ በዚህ ስር ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ከቀረበው ጠቋሚ መስታአምር እና የመሆን ግስ ገለፃ እና ምሳሌ ተማሪው መረዳት በሚችልበት መንገድ በአጭሩ ያቀረበ ያቀራረብ ስልት ነው፡፡ በአቀራረቡም ጠንካራ ጎን የታየበት ስልት ሆኖ ታይቷል፡፡

ገለፃ ከተሰጣቸዉ የሰዋሰዉ ይዘቶች ሌላዉ ደግሞ ተዉሳከ ግስን የሚመለከት ሲሆን ይህ ገለፃ በምሳሌ ተደግፎ በጥሩ ሁኔታ ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ በመሆኑም አንደሚከተለዉ እንመለከታለን፡፡

> ተዉሳከ ግስ ማለት የግስ ጭማሪ ወይም ግስን የሚገልፅ ማለት ነዉ፡፡ መደበኛ ተዉሳከ ግሶች በቁጥር ጥቂት ሲሆኑ አገባባቸዉም ከግስ በፊት ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ ከግስ በፊት ገብቶ ግስን የገለፀ ቃል ሁሉ ተዉሳከ ግስ ላይሆን ይችላል፡፡ ተዉሳከ ግሶች ግሱን የሚገልፁት ከጊዜ፣ ከቦታ፣ ከሁኔታ ወዘተ አንፃር፡፡

**ምሳሌ፡-** ኃይሉ እዚህ ነበር፡፡ /ቦታን/

ፅጌረዳ ነገ ትመጣለች፡፡/ጊዜን/

ቀጥሎ በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ዉስጥ ባሉት ክፍት ቦታዎች ተገቢዉን ተዉሳከ ግስ በመጻፍ አገልግሎቱን ግለጹ፡፡

ሀ. ሁለቱ ልጆች---------------መጥተዋል፡፡

ለ. አበራ ዛሬ---------------ነበር፡፡

ሐ. ከድጃ ሰፊ ቦታ----------ገዛች፡፡

መ. አሊ--------------------ሄደ፡፡

ሠ. ልጆቹ-------------------ናቸዉ፡፡

ገጽ/70/

ከላይ በቀረበዉ ገለፃ ተዉሳከ ግስ ማለት የግስ ጭማሪ ወይም ግስን የሚገልፅ እንደ ሆነ፣ መደበኛ ተዉሳከ ግሶች በቁጥር ጥቂት መሆናቸዉንና ከግስ በፊት ገብተዉ ግሱን ከቦታ፣ከጊዜ ከሁኔታና ወዘተ. አንፃር መግለፅ እንደሚችል ተጠቁሟል፡፡

በሌላ በኩል የቀረበዉን ገለፃ መሰረት አድርገዉ ተማሪዎች ህጉን እየተከተሉ በተገቢዉ መንገድ በመልመጃዎችና ምሳሌዎች በመታገዝ ሥርዓቱን ተገንዝበዉ እንዲተገብሩ የሚያደርጉ አቀራረቦች ስለሆኑ ተማሪዉ በራሱ ጥረት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር እንዲሄድና በሂደትም በራሱ እንዲተማመን የሚያደርግ ስልት በመሆኑ ጠንካራ ጎን ታይቶበታል፡፡

ገለፃና ምሳሌ ከተሰጡባቸዉ በረካታ የሰዋሰዉ ይዘቶች ዉስጥ አንዱ ስለመደብ የቀረበ ገለፃ ነዉ፡፡ ገለፃዉ ምንም እንኳን በምሣሌዉ አስፋፍቶ ቢያስቀምጠዉም ገለፃዉ ሁለት መስመር በማይሞላ መጠን ቀርቦ ይገኛል፡፡ ምሳሌዉን ተከትለዉ የቀረቡ መልመጃዎች በርካታ ቢሆንም በቀላሉ ለመረዳትና ለተግባቦት ለማዋል ሊያስቸግር ይችለል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ዉስጥ መደብ በሶስት ይከፍላል፡፡ እነዚህ መደቦች የሚገለፅባቸዉ ተዉላጠ ስሞች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

| **መደብ** | | **ተዉላጠ ስሞች በቁጥር** | |
|---|---|---|---|
| | | **ነጠላ** | **ብዙ** |
| 1ኛ | | እኔ | እኛ |
| 2ኛ | ተባዕት | አንተ | እናንተ |
| | አንስታይ | አንቺ | እናንተ |
| 3ኛ | ተባዕት | እሱ | እነሱ |
| | አነስታይ | እሷ | እነሱ |

በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ዉስጥ ተዉላጠ ስሞች፣ ፆታን፣ መደብንና ቁጥርን ለይታችሁ በተሰጠዉ ሠንጠረዥ አመልክቱ

<u>**ምሳሌ፡-**</u>

| **አረፍተ ነገር** | **ተዉላጠ ስም** | **መደብ** | **ፆታ** | **ቁጥር** |
|---|---|---|---|---|
| እኔ ነገ መፅሐፍ አነባለሁ | እኔ | 1ኛ | (አይለይም) | ነጠላ |

| **አረፍተ ነገር** | **ተዉላጠ** | **መደብ** | **ቁጥር** |
|---|---|---|---|
| ሀ.እናንተ ዛሬ እዚህ ተጫወቱ፡፡ | | | |
| ለ.እነሱ እዚያ ይሰበሰባሉ፡፡ | | | |
| ሐ.እሱ እዚያ መጽሐፍ አነበበ | | | |
| መ.እሷ ትናንት እዚያ ልብሷን አጠበች፡፡ | | | |
| ሠ.እኔ ቅድም እዚያ ነበርኩ፡፡ | | | |

ገፅ/76-77/

ከላይ የቀረበዉ ይዘት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረበ ቢሆንም ስለመደብና ስለተዉላጠ ስሞች በቂ በሆነ መጠን መብራራትና መግለፅ ይኖርበታል፡፡ አለበለዚያ ግን በምሳሌዎች ብቻ በመታገዝ የቋንቋዉን ሰዋሰዋዊ ሥርዓት ማወቅና መረዳት ለተማሪዎች ቀላል አይሆንም፡፡ በገለፃዉ መሰረት መደብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተዉላጠ ስሞችን እንደዚሁ ተብራርቶ መቅረብ ባይችልም የአቀራረብ ስልት ከከባድ ወደ ቀላል ወይም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልት የቀረበ ነዉ፡፡ የቋንቋ ይዘት ወይም ገለፃዉ በአማርኛ ቋንቋ መደብ በሦስት እንደሚከፈልና መደቦቹ የሚገለፁባቸዉ ተዉላጠ ስሞች ተካተዉ ቀርቧል፡፡ መደብ ተብሎ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበዉ 1ኛ መደብ በተዉላጠ ስም ሲገለፅ እኔ፣ በቁጥር ነጠላ፣ እኛ በቁጥር ብዙ በማለት ቀርቦ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ፆታን አይለይም፡፡ 2ኛ መደብ በፆታ ተለይቶ ተባዕታይ በማለት የቀረበ ሲሆን በተውላጠ ስም አንተ በቁጥር ነጠላ፣ በተዉላጠ ስም እናንተ በቁጥር ብዙ በተዉላጠ ስም አንቺ በቁጥር ነጠላ፣ እናንተ ቁጥር ብዙ በማለት ቀርቧል፡፡ 3ኛ መደብ ልክ እንደ 2ኛ መደብ ላይ እንደተመለከተዉ ተባዕታይ እና አንስታይ ተብሎ በፆታ የተከፈለና በተዉላጠ ስም እሱ በቁጥር ነጠላ፣ እነሱ በቁጥር ብዙ በተባዕታይ ፆታ ሲቀርብ በአንሰታይ ፆታ

ደግም በተዉላጠ ስም እሷ በቁጥር ነጠላ፣ እነሱ በቁጥር ብዙ በማለት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልት መደብንና ተዉላጠ ስሞችን አካቶ ለማቅረብ ችሏል፡፡

ገለፃ የተሰጡባቸዉ የሰዋሰዉ ይዘቶች ዉስጥ ሌላዉ ደግሞ አዎንታዊና አሉታዊ አረፍተ ነገሮች ናቸዉ፡፡ በዚህ ገለፃ ወይም ማብራሪያ ምንም አይነት ምሳሌ ሳይሰጥ ተማሪዉ ከጠቅላላ እዉቀት ወይም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ባለዉ አቀራረብ ማስታወሻዉን ወይም ገለፃዉን ብቻ በመረዳት በራሳቸዉ ጥረት ወደ ተግባር እንዲገቡ የሚያደርግ የአቀራረብ ስልት ነዉ፡፡ በመሆኑም ይህንን አቀራረብ ስልት እንደሚከተለዉ እንመለከታለን፡፡

> *አወንታዊ አርፍተ ነገር ማለት በአረፍተ ነገሩ ማሠሪያ አንቀፅ የተጠቆመዉን ድርጊት ሳያፈርስ መናገርን የሚመለከት ነዉ፡፡ አሉታዊ አረፍተ ነገር ደግሞ መጀመሪያ የታወቀዉን ወይም የተነገረዉን ሀሳብ የሚያፈርስ አገላለፅ ነዉ፡፡ አዎንታዊ አረፍተ ነገር አዎንታዊነቱን የሚያሳይ ቅጥያ የለዉም፡፡ አሉታዊ አረፍተ ነገር ላይ ግን ግሱ ላይ አል- (-ም) የሚሉ ቅጥያዎችን ይወስዳል፡፡*

ከዚህ በታች የተሰጡትን አረፍተ ነገሮች አዎንታዊና አሉታዊ በማለት ለዩ፡፡

*ሀ*. የወይን ሐረግ የተሰራዉን *ሥራ* አላየችዉም፡፡
**ለ**. በስብሰባዉ ላይ ብዙ ሰዉ አልተገኘም፡፡
**ሐ**. ለቃለ መጠይቅ ያለፉ ተማሪዎች ዛሬ ይፈተናሉ፡፡
***መ***. ወደ በታቸዉ የሄዱ ልጆች እንደገና መጡ፡፡
***ሠ***. ራን ከኤች.አይቪ. መጠበቅ ብልህነት ነዉ፡፡
**ረ**. ጠንክሮ መስራት ለሀገር ልማት ይበጃል፡፡
**ሰ**. አቶ ወርቁ ወደ አዲስ አበባ አልሄደም፡፡
**ሸ**. ትምህርት ቤታችን በመስከረም ወር *ሥራ*ዉን ጀመረ፡፡
**ቀ**. በሕይወት ለመኖር ዉሃ በጣም አስፈላጊ ነዉ፡፡
**በ**. ልጁ ጎበዝ ተማሪ መሆኑን አላወቅሁም፡፡
የሚሉት ጥያቄዎች ይገኙበታል፡፡

ገፅ/94-95/

ይህ ከላይ የቀረበዉ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀርበ የአቀራረብ ስልት ሲሆን አዎንታዊና አሉታዊ አረፍተ ነገሮችን ለይቶ ማወቅና ወደ ተግባር መቀየርን ወይም መተግበርን አካቶ የቀረበ ስልት ነዉ፡፡ በገለፃዉ መሰረት ተማሪዉ ሊረዳዉ በሚችልበት መንገድ የተብራራና ምንም እንኳን አጋዥ የሆነ ምሳሌ ባይቀርብም ከገለፃዉ በመነሳት ተማሪዎች ቀሪዉን ተግባር እንዲሰሩ የሚቻል መሆኑን የሚያሳይ አቀራረብ ስልት ነዉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ገለፃ ያተኮረበት ነጥብ አዎንታዊ አረፍተ ነገር ማለት በአረፍተ ነገር የሚለየዉና አዎንታዊነቱን የሚያሳይ ቅጥያ ያለመኖሩን ነዉ፡፡ በሌላ መንገድ ደግሞ አሉታዊ አረፍተ ነገር ግን በግሱ ላይ አል-(-ም) የሚሉ ቅጥያዎች መኖሩን አመጣጥኖ ማቅረብ መቻሉ ጠንካራ ጎኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡

ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ከቀረበዉ የሰዋሰዉ ይዘቶች ዉስጥ ገለፃ የተሰጠዉ በመጠይቃዊ ቃላትና አረፍተ ነገሮች ነዉ፡፡ ይህ አቀራረብ ከጥቅል የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ህግ ወደ ዝርዝር ጉዳይ የሚያመለክት አቀራረብ ስልት ሲሆን ይህንኑ በሚከተለዉ መልክ እንመለከታለን፡፡

መጠይቃዊ አረፍተ ነገሮች ምላሽ የሚሹ አረፍተ ነገሮች ናቸዉ፡፡ እነዚህ አረፍተ ነገሮች አብዛኛዉን ጊዜ በመጠይቃዊ ቃላት አማካይነት ይመሰረታሉ፡፡ መጠይቃዊ ቃላት የሚባሉት ማን? ምን? ለምን? እንዴት? መቼ? የት? የሚሉት ናቸዉ፡፡

ወደ ተግባር ስንገባ ደግሞ፡- ማን? ምን? ለምን? እንዴት? መቼ? የት?የሚሉት መጠይቃዊ ቃላት በመጠቀም አምስት መጠይቃዊ አረፍ ነገሮች መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- በትምህርት ቤታችን የተሰራዉን ቧንቧ ማን ሰበረዉ?

ንፁህ የመጠጥ ዉሃ እንዴት ሊገኝ ይችላል?

ገፅ/102/

ከላይ በቀረበዉ የአቀራረብ ስልት መሰረት ስለመጠይቃዊ አረፍተ ነገር ምንነት ያብራራና የመጠይቃዊ ቃላትን በዝርዝር ማለትም ማን? ምን? ለምን? እንዴት? መቼ? የት? የሚሉትንና ይህንኑ በምሳሌ ያቀረበ የአቀራረብ ስልት መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ ተማሪዉ ከተሰጠዉ ገለፃና ምሳሌ በመነሳት የቀረቡትን ቃላት በመጠቀም በራስ ተነሳሽነት መጠይቃዊ አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ የሚያደርግ ነዉ፡፡ ለተማሪዉም መረዳት በሚችልበት አቀራረብ የቀረበ ነዉ ማለት ይቻላል፡፡

በመማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ከቀረቡት የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ ዉስብስብ አረፍተ ነገርን መመስረት ይገኝበታል፡፡

ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ነጠላ(ተራ) አረፍተ ነገሮችን በአያያዦች አማካይነት በማጣመር ሌሎች ዉስብስብ አረፍተ ነገሮችን መመስረት ይቻላል፡፡

ምሳሌ፡- የሂሳብ ትምህርት አወዳለሁ፡፡ ነጠላ/ተራ/ አረፍተ ነገር)

ጥሩ ዉጤት አላመጣሁም፡፡ ነጠላ /ተራ)አረፍተ ነገር)

የሂሳብ ትምህርት እወዳለሁ፣ይሁን እንጂ ጥሩ ዉጤት አላመጣሁም፡፡

በምሣሌዉ መሰረት"ይሁን እንጂ" የሚለዉን አያያዥ ሁለቱን ነጠላ(ተራ) አረፍተ ነገሮችን በማያያዝ ሌላ ዉስብስብ አረፍተ ነገር ለመመስረት አስችሏል፡፡

ቀጥሎ በሰንጠረዥ ግራና ቀኝ የቀረቡትን ነጠላ/ተራ/ አረፍተ ነገሮች ከተሰጡት አያያዦች መካከል ተገቢዉን በመጠቀም ዉስብስብ አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

| ተ.ቁ | ነጠላ(ተራ) አረፍተ ነገር | አያያዥ | ነጠላ(ተራ)አረፍተ ነገር |
|---|---|---|---|
| 1 | ቦርሳዬን አስቀመጥኩ፡፡ | ይሁን እንጂ | ሀ. ብዙ ማዳመጥ እችላለሁ |
| 2 | ቁርስ አልበላሁም፡፡ | እና | ለ. እኔን አታገኘኝም |
| 3 | ሩቅ ቦታ ሄጃለሁ፡፡ | ስለዚህ | ሐ. እሱ አይወደኝም |
| 4 | ብዙ መናገር አልወድም፡፡ | ነገር ግን | መ. የረሀብ ስሜት አልተሰማኝም |
| 5 | በስራ ቦታ አልነበርኩም፡፡ | እንጂ | ሠ. ምን እንደሰራህ ሪፖርቱ ደርሶኛል፡፡ |
| 6 | ታታሪነቴን አልጠላዉም፡፡ | ግን | ረ. እንደ ሥራዬ ዉታጤማ አይደለሁም፡፡ |
| 7 | ወንድሜን እወደዋለሁ፡፡ | | ሰ. ኳስ መጫወት ጀመርኩ፡፡ |
| 8 | የክፍል ጓደኞቼን አወዳቸዋለሁ፡፡ | | ሸ. በየቀኑ ባያቸዉ ደስ ይለኛል፡፡ |

ገፅ/119-120/

ከላይ የቀረበዉ ይዘት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረበ ሲሆን ዋና አላማዉም አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ነጠላ/ተራ/ አረፍተ ነገሮችን በማጠመር ዉስብስብ አረፍተ ነገሮችን መመስረት እንደሚቻል ነዉ፡፡ ገለፃዉ በሁለት መስመር የተጠናቀቀ ቢሆንም ምሳሌ ሰፋ ባለ ሁኔታ ለማቅረብ ጥረት ያደርገ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ የአቀራረብ ስልት

ከአጭር ገለፃና በምሳሌዉ በመመራት ተማሪዎች የተሰጠዉን መልመጃ እንዲሰሩ ወይም በራሳቸዉ እንዲተገብሩ የሚያደርግ ነዉ። በዚህ አቀራረብ ስልት መሰረት ስለአያያዥ ቀደም ብለዉ መማራቸዉ ለቀጣዩ ስራ ያግዛችዋል የሚል እሳቤ ያሳድራል ወይም ትምህርቱን ያቀለዋል ተብሎ ይገመታል።

ከአጠቃላ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ከቀረቡት የሰዋሰዉ ይዘቶች መካከል የመጨረሻ የሆነዉ ገለፃ ጥገኛ አረፍተ ነገር የሚለዉ ሲሆን ይህንኑ አቀራረብ እንደሚከተለዉ እናያለን።

መስተዋድዶች በነጠላ አረፍተ ነገር ማሰሪያ አንቀጽ ላይ በሚያርፉበት ጊዜ ማሰሪያ አንቀጹን እንዳያስር በማድርግ ነጠላ አረፍተ ነገሩን ወደ ጥገኛ አረፍተ ነገር ይለዉጡታል። ጥገኛ አረፍተ ነገሩንም በሌላ አረፍተ ነገር ላይ ተጠግቶ እንዲነገር ያደርጉታል። ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹ በ- ከ- ለ- ስለ- እንደ ናቸዉ።

ምሳሌ፡- ጫት ጤናን ያዉካል።

ጫት ጤናን ስለሚያወክ.....

ቀጥሎ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች ስለ - እንደ -ከ- በ - ለ -የሚሉትን መስተዋድዶች በመጠቀም ወደ ጥገኛ አረፍተ ነገሮች ለውጧቸው።

ሀ. ጎበዟ ልጅ አጠናች።

ለ. ረጅሙ ልጅ ሮጠ።

ሐ. ሁሉም ሰው አገሩን ወደደ።

መ. በርካታ ሰዎችን ከሱስ ነፃ ሆኑ

ሠ. የአካባቢ ሰዎች ማህበራዊ ግንኙነታቸውን አጠናከሩ

ረ. መጥፎ ሽታ ሸተተኝ ።

ሰ. እህቱ ሄደችበት ።

ሸ. መምህሯ ክፍል ውስጥ ገባች።

ገፅ/141//

ከላይ የቀረቡት መልመጃዎች ትኩረት በቋንቋው ሰዋሰዋዊ ህግ ላይ በማተኮር ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብን የተከተሉ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም የቀረበው መልመጃ በገለፃና በምሳሌው መሰረት ተማሪዎች መስተዋድዶችን በመጠቀም ነጠላ አረፍተ ነገሮች ወደ ጥገኛ አረፍተ ነገሮች እንዲለውጧቸው የሚያደርግ ነው፡፡ የመስተዋድዶች ተግባርም በነጠላ አረፍተ ነገሮች ማሠሪያ አንቀጽ ላይ በማረፍ ማሰሪያ አንቀፁን እንዳያስር ወይም እንዳይቋጭ በማድረግ ነጠላ አረፍተ ነገሩን ወደ ጥገኛ አረፍተ ነገር መለወጥ ነዉ፡፡ ጥገኛ አረፍተ ነገሩንም በሌላ አረፍተ ነገር ተጠግቶ እንዲነገር ያደርጉታል፡፡ ከመስተዋደዶችም መካከል ጥቂቶቹ በ- ከ- ለ- ስለ- እንደ ናቸዉ፡፡ ተብለዉ በመጽሐፉ ዉስጥ ተዘርዝረዉ ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ በተደረገዉ የሰነድ ፍተሻ በተተኳሪዉ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች በተለያየ መንገድ ለናሙናነት ቀርበዋል፡፡ ይህ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ከሌሎች አቀራረቦች የበለጠ በስፋትና በብዛት ገለፃዎችንና ምሳሌዎችን በማቀረብ ብሎም በማብራረት በተገቢ መልኩ ቀርቦ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ከጠቅላላ ዕዉቀት ወደ ዝርዝር ወይም ከከባድ ወደ ቀላል በሚሄድ አቀራረብ የራሳቸዉን ጥረት አክለዉና በምሳሌዉም ተደግፈዉ ወደ ተግባር እንዲሄዱ ያደርጋቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ መጽሐፉ በመረሃትምህርቱ ላይ ተመስርቶ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የይዘት አቀራረብ ቢያቀርብም ተማሪዎች በተመጣጣኝ ሁኔታ ትክክለኛ የሆነዉን ቋንቋ በራሰቸዉ ለማወቅ ሊከብዳቸዉ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ አቀራረብ በርካታ ርዕሰ ጉዳዮችን በተለያየ መንገድ አካቶ ማቅረቡ የይዘቶችን ተያያዥነት ተማሪዎች እያዉቁ እንዲሄዱ ማድረጉ ዳግም መልካም ጎን እንዲኖረዉ አድረጓል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በመርሃ ትምህርቱ የተጠቆሙ ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ መኖራቸዉ ከጠንካራ ጎን እዲጠቀስ ያደርጋል፡፡

### 4.2.3. ዉጤት ተኮር አቀራረብ

ዉጤት ተኮር አቀራረብ በቋንቋዉ ቅርፅ እንዲሁም በቋንቋዉ መዋቅራዊ ህግጋትና ብያኔዎች ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ በክለሣ ድርሳት ተጠቀሷል፡፡ በዚሁ መሰረት ዉጤት ተኮር በሆነ ስልት የቀረቡ የሰዋሰዉ ይዘቶችን እናያለን፡፡

በገፅ /20/ ላይ ድርብ አረፍተ ነገሮችን መመስረት፣ በገፅ/39/ ላይ አያያዦችን በመጠቀም፣ በገፅ/62/ ላይ ጠቋሚ መስተአምር ከመሙያ ጋር፣ በገፅ/85/ ላይ ተዉሳከ ግስ፣ ስምና መደብ፣ በገፅ/108/ ላይ አዎንታዊ፣ አሉታዊና መጠይቃዊ አረፍተ ነገሮች፣ በገፅ/133/ ላይ ዉሰብስብ አረፍተ ነገር መመስረት፣ በገፅ/154-155/ ላይ ዉስብስብ አረፍተ ነገር መመስረት በገፅ /164/

ላይ ጠቋሚ መስተአምሮች፣ በገፅ/172/ ስሞች እንደመሙያ ሲገቡ፣ በገፅ /179-180/ ላይ ጠቋሚ መስተአምርና መሙያ፣ በገፅ/197-በ 198/ የጊዜና የቦታ ተዉሳከ ግስ፣ በገፅ /106-107/ ላይ ተዉሳከ ግስ፣ መደብና ጊዜ አመልካች፣ በገፅ/216- 217/ ላይ አዎንታዊና አሉታዊ አረፍተ ነገሮች እና በገፅ /224- 225/ ለይ መጠይቃዊ አረፍተ ነገሮች የሚሉት የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ይገኙበታል፡፡

በዉጤት ተኮር የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ስልት መሰረት የቀረበ ርዕሰ ጉዳይ ድርብ አረፍተ ነገሮችን መመስረት በሚል የቀረበ ነዉ፡፡ ይህም የአቀራረብ ስልት እንደሚከተለዉ እንመለከታለን፡፡

ቀጣዮቹን አያያዦች በትክክል በመጠቀም ጥንድ ጥንድ ሆነዉ የቀረቡትን ነጠላ አረፍተ ነገሮች ወደ ድርብ አረፍተ ነገሮች ለዉጡ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| እና | ይሁን እንጂ | ነገር ግን | ስለዚህ | እንጂ |

ሀ. አፈር ሕይወት የለዉም፡፡

አፈር ሕይወትን ያለመልማል፡፡

ለ. አስቴር ራሷን አሟታል፡፡

አስቴር ሐኪም ቤት ትሂድ፡፡

ሐ. መማር ይጠቅማል፡፡

መማር አይጎዳም፡፡

መ.ሀዋ ደብተሯን አዘጋጀች፡፡

ሀዋ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች፡፡

ሠ.ሀሊማ በጥሩ ሁኔታ አጠናች፡፡

ሀሊማ ፈተናዉን አላለፈችም፡፡

የሚሉትን ይዘቶች በገፅ /20 ላይ ቀርቦ ይገኛል፡፡

ውጤት ተኮር የቋንቋ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ስልት ተማሪዎቹ በቋንቋዉ ህግ ላይ ተመስርተዉ ትክክለኛ የሆነ መልስ እንዲሰጡ ይሻል፡፡ ለዚህም ነዉ ከላይ በትዕዘዙ እንደተጠቀሰዉ በትክክል አያያዦችን ተጠቅመዉት በጥንድ የቀረበዉን ነጠላ አረፍተ ነገር ወደ ድርብ አረፍተ ነገር እንዲለወጡ የተጠየቀዉ፡፡ በዚህ ዓይነት ተማሪዎች የአረፍተ ነገር አመሰራረት እዉቀት እንዲኖራቸዉ ለማድረግ እና አያያዥ ቃላትን እንዴት በተገቢዉ ቦታቸዉ መጠቀምና ነጠላ አረፍተ ነገርን ወደ ድርብ አረፍተ ነገር ለዉጠዉ እንዲያሳዩ የሚያሰችል የአቀራረብ ስልት መሆኑን ከቀረበዉ አስረጂ ለማየት ተችሏል፡፡

በገፅ /39/ ላይ ስለ አያያዦችን መጠቀም የቀረበ ትዕዛዝ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

አያያዦችን በመጠቀም አምስት ድርብ አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

በዉጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት ከቀረቡት የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል አንዱ አያያዦችን መጠቀም የሚል ነዉ፡፡ በዚህ የአቀራረብ ስልት ተማሪዉ ምንም አይነት ማብራሪያ ወይም ምሳሌ ሳይሰጠዉ በነበረዉ ቅደመ እዉቀት በመጠቀም በራስ ጥረት ወደ ዉጤት እንዲመጣ የሚያደርግ አቀራረብ ነዉ፡፡ ለዚህም ነዉ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ሥር በቀጥታ የተሰጠዉ ትዕዛዝ አያያዦችን በመጠቀም አምስት ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን መሥርቱ ብሎ ያስቀመጠዉ፡፡ ከዚህ አንፃር ተማሪዎች የነጠላና ድርብ ዓረፍተ ነገሮች አመሠራረትን በተመለከተ በተቀመጠዉ ህግ ወይም ትዕዛዝ መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄ መልስ እንዲሰጡ ይጠበቃል፡፡

ገፅ/39/

በገፅ/62/ ላይም ጠቋሚ መስተአምር ከመሙያዉ ጋር የሚለዉን በተመለከተ የቀረበዉን ትዕዛዝ እንደሚከተለዉ ማየት ይቻላል፡፡

"ጠቋሚ መስተአምርንና ስምን እንደ መሙያ የያዙ ስድስት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡"

ገፅ/62/

በገፅ/85/ ላይ የቀረበዉ የዉጤት ተኮር የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል አንዱ "ተዉሳከ ግስ፣ ተዉላጠ ስሞችና መድብ" የሚል ሲሆን እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

ቀጥሎ የቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ያሉትን ቃላት በተገቢ ቦታቸዉ መድቡ፡፡

| | ዓረፍተ ነገር | በአረፍተነገሩዉስጥያለዉ የተዉሳከ ግስ ዓይነት | | | በአረፍተ ነገሩ ዉስጥ ያለዉ ተዉላጠ ስም | መደብ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | እሱ ትናንት እዚህ አልነበረም፡፡ | የጊዜ | የቦታ | የሁኔታ | | |
| ለ | እኔ ይህንን ጉዳይ በቀላሉ አላየዉም፡፡ | | | | | |
| ሐ | አንቺ ነገ ወደ ወላጆችሽ ትሄጃለሽ፡፡ | | | | | |
| መ | አንተ ቅድም እዚህ አልመጣህም | | | | | |
| ሠ | እነርሱ ጎበዞች ናቸዉ፡፡ | | | | | |

/ገፅ፣85/

ከላይ በዉጤት ተኮር አቀራቀረብ የቀረበዉ ይዘት በቋንቋዉ መዋቅራዊ ህግጋት መሠረት እንዲሰሩ ትዕዛዝ ተሰቶበታል፡፡ በዚሁ መሰረት የቋንቋዉን ሰዋሰዋዊ ሥረዓት በተከተለ መልኩ ተዉሳከ ግስን፣ ተዉላጠ ስምንና መደብን ከአረፍተ ነገሮች ዉስጥ ለይቶ በማወጣት በተገቢ ቦታዎች መመደቡ ከተማሪዎች የሚጠበቅ ተግባር ነዉ፡፡ በዚህ የአቀራረብ ስልት የሚቀርበዉ የተለያዩ የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ይዘቶችን በተናጥል ተማሪዎች እንዲተነትኑ መደረጉ አቅም ስለሚሆናቸዉና የበለጠ እንዲነሳሱ ስለሚያደርጋቸዉ አቀራረቡ ተወዳጅና ጠንካራ ጎን እንዲኖረዉ አድርጎታል፡፡ ምክንያቱም በርዕሰ ጉዳዩ ወይም በአንድ አረፍተ ነገር በዉስጡ ብዙ ዘርፎችን መያዙና ተማሪዉ ደግሞ እያንዳንዱን የሰዋሰዉ ይዘቶች(ክፍሎች) በቀላሉ እንዲረዳ ማስቻሉ ነዉ፡፡

በገፅ/108/ ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ"አዎንታዊ፣ አሉታዊና መጠይቃዊ አረፍተ ነገሮች" በሚል የቀረቡ የዉጤት ተኮር ይዘት ትዕዛዙ ወይም ተግባር እነደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

ቀጥሎ በሰንጠረዥ የቀረቡት አረፍተ ነገሮች አዎንታዊ፣ አሉታዊና መጠይቃዊ አረፍተ ነገሮች መሆናቸዉን ይህን(√) ምልክት በመጠቀም ለዩ።

| አረፍተ ነገር | | ዓይነት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አዎንታዊ | አሉታዊ | መጠይቃዊ |
| ሀ | በጌጣጌጥ ንግድ ለምን ያህል ጊዜ ሠራችሁ? | | | |
| ለ | ሥራችንን በአግባቡ ለመስራት በዕቅድ መመራት አለብን። | | | |
| ሐ | በአንዳንድ ቤተሰብ ሕፃናትን መንከባከብ አልተለመደም። | | | |
| መ | ወጣቶች ቅርሶችን የመንከባከብና የመጠበቅ ሀላፊነት አለባቸዉ። | | | |
| ሠ | ሰፊ ይዘት ያለዉን እንደ ፅሁፍ አሳጥሮ ለመፃፍ የሚቻለዉ እንዴት ነዉ? | | | |
| ረ | በሀገራችን የሰንደቅ አላማ ቀን በብሔራዊ ደረጃ ይከበራል። | | | |
| ሰ | በቃል ዉስጥ የፊደሎች ላልቶና ጠብቆ መነበብ የፊቺ ለዉጥ የሚያመጣዉ ለምንድነዉ? | | | |
| ሸ | ሁለት የተለያዩ ፊቺ ያላቸዉ ቃለት በአንድ ላይ አጣምሬ አንድ ትርጉም ያለዉ ቃል አልመሰርትም። | | | |
| ቀ | በትኩረት በማነብበት ጊዜ ሲያወሩኝ አልወድም | | | |
| በ | በምታነብበት ጊዜ መንቀሳቀስ የሚገባዉ የትኛዉ አካል ከፍላችን ነዉ። | | | |

/ገፅ፣ 108/

ከላይ በዉጤት ተኮር የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ስልት የቀረበዉ መልመጃ አዎንታዊ፣ አሉታዊና መጠይቃዊ አረፍተ ነገሮችን በቋንቋ መዋቅራዊ ህግ መሰረት እያንዳንዱን በመለየት በተሰጠዉ ሰንጠረዥ ዉስጥ(√) ይህንን ምልክት በመጠቀም ማመልከትና ለይቶ ማሳየት ከተማሪዎች የሚጠበቅ ተግባር ይሆናል። በዚህ ሂደትም ተማሪዎች የአረፍተ

ነገር አይነቶችን ለይተዉ እንዲያዉቁ የሚረዳቸዉ የአቀራረብ ስልት መሆኑ ጠንካራ ጎኑን ያመለክታል፡፡

በገፅ/133/ ላይ"ዉስብስብ አረፍተ ነገር መመስረት" በሚል በዉጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት የቀረበዉን መልመጃ ትዕዛዝ እንደሚከተለዉ ማየት ይቻላል፡፡

"የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም ስድስት ዉስብስብ አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡"

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| እና | ግን | እንጂ | ነገር ግን | ስለዚህ | ይሁን እንጂ |

/ገፅ፣ 133/

ከላይ በቀረበዉ በዉጤት ተኮር አቀራረብ ተማሪዉ የቋንቋዉን ሰዋሰዋዊ መዋቅር ተከትሎ የተሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረት አድርገዉ እነዚህን(እና፣ ግን፣ እንጂ፣ነገር ግን፣ ስለዚህ፣ ይሁን እንጂ) የሚሉትን አያያዦች በመጠቀም ስድስት ዉስብስብ አረፍተ ነገሮችን እንደሚሰሩ ወይም እንዲመሰርቱ ይጠበቃል፡፡ከዚህ አንፃር በተለያየ መንገድ ቃላትን በመጠቀምና መዋቅሩን በመከተል ወደ ተግባር እንዲገቡና ዉጤት እንዲያስመዘግቡ ማበረታቻ ሊሆናቸዉ የሚችል የአቀራረብ ስልት እንደሆነ ይገመታል፡፡ ነገር ግን ይህ አቀራረብ ሁሉንም ተማሪዎች ማመጣጠን ይችላል ማለት አይደለም፡፡

በገፅ/154-155/ ላይ በቀረበዉ መልመጃ እንደሚያመለክተዉ "ዉስብስብ አረፍተ ነገር መመስረት" የሚል ሲሆን ትዕዛዙም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

"መስተዋድዶችን በመጠቀም ዉስብስብ አረፍተ ነገሮችን መስርቱ"

ምሳሌ፡- ሱሰኝነት የምጣኔ ሀብት ችግር ያመጣል፡፡

ማህበረሰቡ ግንዛቤ አለዉ፡፡

ሱሰኝነት የምጣኔ ሀብት ችግር እንደሚያመጣ ማህበረሰቡ ግንዛቤ አለዉ፡፡

ሀ. ረጅሙ ልጅ ቦርሳዉን ወሰደ

የልጁ አባት ተቆጣ

ለ. ሰዉየዉ ሆስፒታል ሄደ

ሰዉየዉ ህክምናዉን አላገኘም

ሐ. እሱ ከመጠጥ ሱስ ተላቀቀ

እሱ የአልኮል መጠጥ አይጠጣም፡፡

መ. የተላከለትን ደብዳቤ ተቀበለ፡፡

የደብዳቤዉን መልስ ጻፈ፡፡

ሠ. ሰንጋዉ ዛሬ ጠዋት ታረደ፡፡

አንድ መደብ ሥጋ ገዛሁ

ረ. ሴትየዋ ሌባዉን ያዘችዉ፡፡

ሴትየዋ ሌባዉን በአንድ ቡጢ ጣለችዉ፡፡

ገፅ/154-155/

ዉስብስብ ዓረፍተ ነገር አመሰራረትን በተመለከተ በተሰጠዉ የቋንቋ ሰዋሰዉ ህግ መሰረት በማድረግ ለቀረበዉ ጥያቄ ተማሪዎች ተገቢዉን መልስ እንዲሰጡ ይጠበቃል፡፡ በዚህ ዉጤት ተኮር አቀራረብ መሰረት ስለ መስተዋድዶች በነበራቸዉ እዉቀትና ግንዛቤ ተማሪዎች መስተዋድዶችን በመጠቀም ዉስብስብ አረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ያደርጋል በዉጤት ተኮሩ አቀራረብ ስልቱ በቀጥታ ወደ ዉጤት የሚያመራ ቢሆንም በዚህ ርዕሰ ገዳይ ሥር በምሳሌ ተደግፎ መቅረቡ የተሻለ አቀራረብና አቅጣጫ አመልካች መሆኑን ያሳያል፡፡

በገፅ /164/ ላይ ጠቋሚ መስተአምሮች በሚል የቀረበ ሲሆን ይህንኑ ትዕዛዝ በሚከተለዉ መልክ ቀርቧል፡፡

"የሚከተሉት መስተዓምሮች የአረፍተ ነገሩን ባለቤት እንዲጠቁሙ አድርጋችሁ አስገቧቸዉ፡፡"

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| እነዚያ | እነሱ | ያ | እሱ | ያቺ | ይህ | እሷ | ይቺ |

ምሳሌ፡- ያ መጽሐፍ ጠቃሚ ነዉ፡፡

ሀ. የተክሌ መማሪያ መጽሐፍ አዲስ ነዉ፡፡

ለ. ልጆች ደስ የሚሉ አበቦች ገዙ፡፡

ሐ. ሴትየዋ የሳዲያ እናት ትመስለኛለች፡፡

መ. አግዳሚ ወንበር ብዙ ሰዎችን ያስቀምጣል፡፡

ሠ. ሰዎች ልብስ ከገዙ ቆይተዋል፡፡

ረ. ልጅ እናቷን በሥራ ታግዛለች፡፡

/ገፅ፤164/

ከላይ የቀረበዉን የዉጤት ተኮር አቀራረብ በተሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረት የቋንቋዉን ሰዋሰዋዊ መዋቅር ተከትለዉ ተማሪዎች ለቀረቡላቸዉ ጥያቄ ተገቢዉን መልስ እንዲሰጡ ይፈለጋል፡፡ በዚህ በተተኳሪ መፅሐፍ ዉስጥ ተካቶ የቀረበዉ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ትኩረት በዝርዝር የቀረቡ ጠቋሚ መስተአምሮች የአረፍተ ነገሩን ባለቤት እንዲጠቁሙ አድርገዉ እንዲሠሩና እንዲተገብሩ በዉጤት ተኮር አቀራረብ ስልት መሰረት የቀረበ ነዉ፡፡ በገፅ/172/ ላይ" ስሞች እንደመሙያ ሲገቡ"በሚል የቀረበ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት መልመጃዉ እንዴት መተግበር እንዳለበት የሚያመለክት ትዕዛዝ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

"የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በደብተራችሁ በመፃፍ እንደመሙያ የገቡትን ስሞች አስምሩባቸዉ፡፡"

ምሳሌ፡- እነዚያ ወጣቶች ነርሶች ናቸዉ፡፡

ሀ. እኔ መምህር ነኝ፡፡

ለ. ያ ፎቅ ነዉ፡፡

ሐ. ይሄ ሐይቅ ነዉ፡፡

መ. እሷ ነጋዴ ነች፡፡

ሠ. እነዚያተማሪዎች ናቸዉ፡፡

ረ. ያቺ ልጅ ተመራማሪ ሆነች፡፡

/ገፅ፣ 172/

ይህ ከላይ የቀረበዉ የዉጤት ተኮር አቀራረብ ስልት መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም በገፅ /164/ ላይ መስተአምሮች የአረፍተ ነገሩን ባለቤት እንዲጠቁሙ ተደርጎ የቀረበ አቀራረብ ከዚህ ርዕስ ጋር ተያያዥነት ከመኖሩ የተነሳ ለተማሪዉ ግለፅ የሆነ አቀራረብ ነዉ ለማለት ይቻላል፡፡ ምንም እንኳን በርዕሰ ጉዳዩ ቢለያዩም አንዱ ለቀጣዩ መሰረት አየሆነ እየተደጋገፈ ግንዛቤ ያስጨብጣል ማለት ነዉ፡፡

በገፅ/ 179- 180/ ላይ እንደሚታየዉ"ጠቋሚ መስተአምርና መሙያ" በሚል የቀረበ ነዉ፡፡ ትዕዛዙም እንደሚከተለዉ ይሆናል፡፡

ተግባር1 የሚከተሉትን መስተአምሮችን በክፍት ቦታ ላይ በማስገባት አንቀጹን የተሟላ አድርጉ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| እነዚያ | ያ | ይህ | ይቺ | ያቺ |

ያን ጊዜ------ተማሪ አላጠፋም ነበር፡፡ ሆኖም አጥፍቷል በማለት ---ሲቀጣዉ ፈለገ፡፡ ስለሁኔታዉ ትንሽ ከተነጋገሩ በኋላ -----ልጆች ስለ ልጁ ለመምህሩ የተናገሩት ስህተት እንደነበር ታወቀ፡፡ --------ትናንት ያገኛትን ልጅም የልጁን ትክክለኛነት በሚገባአዉቃ ስለነበር -------የተናገሩት ስህተት እንደሆነ ደግማ ለመምህሯ ገለፅች፡፡ መምህሩም------ዓይነት ነገር ለእናንተ ጥሩ አይደለም በማለት መከራቸዉ፡፡

ተግባር2. "ቀጥሎ ከቀረበዉ ሠንጠረዥ ዉስጥ የቀረቡትን ቃለትና ሐረጋት በትክክል በማደራጀትና ስሞችን እንደ መሙያ በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮች መሥርቱ፡፡"

| | | |
|---|---|---|
| ይህ | ናቸዉ | ወጣት መምህር |
| ያ | ነዉ | ወንዝ |
| እነዚያ | ነች | ተማሪዎች |
| ያቺ | | መጽሐፍት |
| ይቺ | | |

በዚህ የዉጤት ተኮር የሰዋሰዉ ትምህርት አቀራረብ ስልት መሠረት በተግባር ቁጥር1 እንደ ተመለከተዉ በዝርዝር የቀረቡትን ጠቋሚ መስተዓምሮችን በተሰጠዉ ክፍት ቦታ በማስገባት አንቀጹን የተሟላ እንዲያደርጉ የቀረበ ሲሆን፣ በተግባር ቁጥር2 ደግሞ በሠንጠረዥ ዉስጥ የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት በትክክል በማደራጀትና ስሞችን እንደመሙያ በመጠቀም ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ የቀረበ መልመጃ ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ አቀራረቡ ለተማሪዉ አቅም የሚፈጥርለትና በራስ የመተማመን እድል የሚከፍትለት ቢሆንም ከተማሪዉ ደረጃ አንጻር ሲታይ የሚከብድ መስሎ ይታያል፡፡

በገፅ/197-198/ ላይ በቀረበዉ የትምህርት ይዘት አቀራረብ ስልት መሠረት"የጊዜና የቦታ ተዉሳከ ግስ" በሚል የቀረበ ሲሆን ትዕዛዙም እንደሚከተለዉ ይሆናል፡፡

ተግባር1. ቀጥሎ የቀረቡትን ተዉሳከ ግሶች በመጠቀም ዐረፍተ ነገሮችን አሟልታችሁ ጻፉ፣(ለአንድ አረፍተ ነገር ከአንድ በላይ ተዉሳከ ግስ ሊኖር ይችላል፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ዘወትር | ነገ | እዚያ | ወዲህ | ዛሬ | ትናንት |
| ዉጪ | ቅድም | በፊት | ቶሎ | ማታ | |

ሀ. የናፈቅናት እህታችን---------መጣች፡፡

ለ. ጎበዙ ተማሪ ከመምህሩ------------መጣ፡፡

ሐ. ታላቅ መንድሙ-------------------አለ፡፡

መ. ረዥሙ ልጅ----------------------ጫማ ገዛ፡፡

ሠ. እሱ አሁን የለም፣------------------ነበር

ረ. አስቴር ከክፍሉ--------------------ተቀመጠች፡፡

ሰ. አለሙ አከባቢዉን ለቆ--------------ወደ ሌላ ቦታ ሄደ፡፡

ሸ. ብዙ ጊዜ ሳይሳካለት ኖሮ-----------ተሳካለት፡፡

ቀ. አባትየዉ ሰሚ ቢያጣም-------------ይናገራል፡፡

በ. በቀለ-------------------------------------ወደ አዲስ አበባ ይሄዳል፡፡

ተግባር 2. ከዚህ በታች የቀረቡትን ተዉሳከ ግሶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መሥርቱ፡፡

ሀ.ትናንት

ለ. ወዲያዉ

ሐ. ዉስጥ

መ.እዚህ

/ገፅ፣ 197-198/

ከላይ በተግባር ቁጥር1 ላይ የቀረበዉ የዉጤት ተኮር ትምህርት ይዘት ተዉሳከ ግሶችን በመዘርዝር ካስቀመጠ በኋላ ተዉሳከ ግሶችን በመጠቀም ያልተሟሉ ዓረፍተ ነገሮችን አሟልተዉ እንድጽፉ የሚያደርግ ሲሆን፣ በተግባር ቁጥር2 ላይ ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ ተዉሳከ ግሶችን በዝርዝር በማስቀመጥ እነዚህን ተዉሳከ ግሶች በመጠቀም አረፍተ ነገር ተማሪዎቹ እንዲመሰርቱ የሚያደርግ አቀራረብ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ለቀረቡላቸዉ ጥያቄዎች ትክክለኛና ተገቢ መልስ ይሰጣሉ፡፡

በገፅ/206-207/ ላይ ስለተዉሳከ ግስ፣መደብና ጊዜ አመላካች የቀረበዉ የትምህርት ይዘት ዉጤት ተኮር አቀራረብን የተከተለ ነዉ፡፡

"በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ያሉትን መደብ፣ተዉሳከ ግስና ጊዜ አመልካቾችን በመለየት በሚወክላቸዉ ቦታ ይህን ምልክት(√) አድርጉ፡፡

| ዓረፍተ ነገር | | መደብ | | | ተዉሳከ ግስ | | | የጊዜ(የግስ ባህሪ) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | የጊዜ | የቦታ | የመጠን | የአሁን | የሀላፊ | የትንቢት |
| ሀ | ትናንት የማጠቃለያ ፈተና ተፈተንኩ | | | | | | | | | |
| ለ | ሞሚና ዛሬ ከሰዐት በኃላ የቀለም ትምህርት ዉድድር ታደርጋለች | | | | | | | | | |
| ሐ | አሰቴር አሁን | | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከትምህርት ቤት ትመጣለች፡፡ | | | | | | | | | |
| መ | አንቺ ነገ እዚህ ግጥሞችሽን ታቀርቢያለሽ፡፡ | | | | | | | | | |
| ሠ | አስካለ ትናንት የሀበሻ ልብስ ገዛች | | | | | | | | | |
| ረ | አለማየሁ አሁን ትልቅ ዓሣ ይገዛል፡፡ | | | | | | | | | |
| ሰ | አንተ አሁን የጭስ አባይ ፋፋቴን ትጎበኛለህ | | | | | | | | | |

/ገፅ፣206-207/

ከላይ የቀረበዉ መልመጃ የሚያመለክተዉ ዉጤት ተኮር ይዘት መሆኑን ነዉ፡፡ በዚህ አቀራረብ መሠረት ቀደም ሲል በተለያየ መንገድ የተማሩትን ተዉሳከ ግስ፣ መደብና ጊዜ አመልካቾችን በመለየት በሚወክሏቸዉ ቦታ ላይ ከአረፍተ ነገሮች ዉስጥ ለይተዉ በማዉጣት እንዲያመለክቱ የሚያደርግ አቀራረቡ ነዉ፡፡ አቀራረቡም በድግግሞሽና ግልጽ በሆነ መንገድ መቀረቡ ተማሪዉ በቀላሉ እዲገነዘበዉ የሚያደርግ መሆኑን ያሳያል፡፡

በገፅ/216-217/ ላይ ስለ "አዎንታዊና አሉታዊ አረፍተ ነገሮች" የዉጤት ተኮር ይዘት አቀራረብ ሲሆን ትዕዛዙም እንደሚከተለዉ ይቀርባል፡፡

ከዚህ በታች የቀረቡትን አዎንታዊ አረፍተ ነገሮች ወደ አሉታዊ ቀይራችሁ ጻፏቸዉ፡፡

ሀ. አቶ አለሙ ቤት ሰሩ፡፡

ለ. ቃላዊ ግጥሞችን ማዳመጥ ያስደስተኛል፡፡

ሐ. እሱ ክፉ ሰዉ ነዉ፡፡

መ. ልጁ እቤት አለ፡፡

ሠ.ቀጭኗ ልጅ ጎበዝ ተማሪ ናት፡፡

ረ. ሰዉየዉ ኀበዝ ተናጋሪ ነዉ።

ሰ. ሕፃኑ መጫወቻቸዉን ሰበረ።

ሸ. የፉከራና የቀረርቶ ግጥሞች ቃላዊ ናቸዉ።

ቀ. ሙዚቃ የሰዎችን መንፈስ ያድሳል።

በ.አዛዉንቱ የሄደበት ቦታ ታዉቋል።

/ገፅ፣216-217/

ከላይ በቀረበዉ አቀራረብ መሠረት የተሰጡትን አዎንታዊ አረፍተ ነገሮች ወደ አሉታዊ ቀይሮ መጻፍ ከተማሪዎች የሚጠበቅ ተግባር ይሆናል። ከዚህ አንፃር ተማሪዎች ጠቅላላ እዉቀታቸዉን በመጠቀም አዎንታዊዉን ወደ አሉታዊ አረፍተ ነገር ቀይረዉ እንዲጽፉ የሚያደርግ አቀራረብ ነዉ።

በገፅ /224-225/ ላይ ስለ መጠይቃዊ አረፍተ ነገር የቀረበ የዉጤት ተኮር የመጨረሻ ይዘት ሲሆን አቀራረቡን እንደሚከተለዉ ማየት ይቻላል።

የሚከተሉትን መጠይቃዊ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| እንዴ! | ለምን? | ማን? | መቼ? | የት? | ምን? | ወይ? |

ሀ. የዚህ ግጥም ደራሲ----------------ነዉ?

ለ. የእርሻ ግጥም---------------------ይከናወናል?

ሐ. ገነት ሻንጣ ገዛች--------------------?

መ. ስለ ስነቃል---------------------ታዉቂያለሽ?

ሠ. የቀረርቶና የፉከራ ግጥም-------------ይጠቅማ?

ረ. ልብስህን አጠብክ----------------------?

ሰ. ዳዊት--------------------------ሄደ?

/ገፅ--224-225/

ከላይ የቀረበዉ የዉጤት ተኮር አቀራረብ ስልት የቀረቡ መልመጃዎች 14 ሲሆኑ አንዱና የመጨረሻ የሆነዉ ይህ መልመጃ ትኩረቱ በተሰጡት መጠይቃዊ ቃላት በመጠቀም በቋንቋዉ ሰዋሰዋዊ መዋቅር መሠረት ለቀረበዉ ጥያቄ ተማሪዎች ተገቢ የሆነ መልስ እንዲሰጡ የሚያሳይ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል መጠይቃዊ ቃላት ምን ምን እንደሆነ ቀደም ሲል በተማሩት እዉቀት መሰረት የቀረቡትን መጠይቃዊ ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገሮችን አሟልተዉ እንድጽፉ ትኩረቱን ያሳደረ አቀራረብ ነዉ፡፡

በአጠቃላይ በዉጤት ተኮር ትምህርት ይዘቶች ድርብ አረፍተ ነገሮችን መመሥረት፣ አያያዦችን መጠቀም፣ ጠቋሚ መስተአምር ከመሙያ ጋር፣ ተዉሳከ ግስ፣ ተዉላጠ ስምና መደብ፣ አዎንታዊ፣አሉታዊና መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገሮች፣ ዉስብስብ ዐረፍተ ነገሮችን መመስረት፣ መስተዋድዶችን በመጠቀም ዉስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን መመሥረት፣ ጠቋሚ መስተዓምሮች ስሞች እንደ መሙያ ሲገቡ፣ ጠቋሚ መስተዓምርን መሙያ፣ የጊዜና የቦታ ተዉሳከ ግስ፣መደብና ጊዜ አመልካች፣ አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች፣ እና መጠይቃዊ ቃላት የሚሉት ትምህርቶች ከሌሎች አቀራረቦች የበለጠ ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡ እነዚህም የቋንቋዉን ሰዋሰዋዊ ሥርዓት ጠብቀዉ በትክክል ሰዋሰዋዊ ህጉን መተግበር ላይ ትኩረት ያደረጉ በመሆናቸዉ በዉጤት ላይ አነጣጥረዉ የቀረቡ ለማለት ያስደፍራል፡፡ መረሃ ትምህርቱ በዉጤት ተኮር የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች በጥንቃቄ የሚተገበሩ መሆናቸዉን አሳስቧል፡፡

### 4.2.4. ሂደት ተኮር አቀራረብ

ሂደት ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆነ ስልት የቋንቋዉን ቅርጾች በሚገባ እንዲጠቀሙባቸዉ የሚያስችል አቀራረብ ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ በ7ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱት የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች መካከል አንዱ ሂደት ተኮር በሆነ ስልት የቀረቡ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶቸ ከሌሎች አንፃር ሲታዩ እጅግ በጣም ጥቂት ናቸዉ፡፡ ይህንንም እንደሚከተለዉ ለማየት እንሞክራለን፡፡

በገፅ/188-189/ ስለ ጊዜ የቀረበዉ የትምህርት ይዘት ሂደት ተኮር አቀራረብን የተከተለ ነዉ፡፡

ጊዜ አንድ ድርጊት እንደተፈጸመ ወይም መቼ እንደሚፈፀም የሚገልፅ የግስ ባህሪ ነዉ፡፡ ጊዜ በሦስት ይከፈላል፡፡ ክፍሎቹም የአሁን፣ የኃላፊና የትንቢት ጊዜ ይባላሉ፡፡

የአሁን ጊዜ የሚባለዉ ዓረፍተ ነገሩ በሚነገርበት ጊዜ የሚፈፀም ድርጊትን ይገልፃል፡፡

ምሳሌ፡- ኤደን አሁን ደብዳቤ ትጽፋለች፡፡

የኃላፊ ጊዜ አንድ ድርጊት ተፈፅሞ ያለቀ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ምሳሌ፡- አብደላ ትናንት መኪና ጠገነ፡፡

የትንቢት ጊዜ አንድ ድርጊት ገና ያልተፈፀመና ወደ ፊት የሚፈፀም መሆኑን ይገልፃል፡፡

ምሳሌ፡- ህሊና ነገ አዲስ አበባ ትሄዳለች፡፡

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች የአሁን ጊዜ፣የኃላፊ ጊዜና የትንቢት ጊዜ በማለት ለዩ፡፡

ሀ. ትናንትና በሰራዉ መጥፎ ሥራ እጅግ አዘነ፡፡

ለ. እነሱ ነገ ወደ ሀገራቸዉ ይሄዳሉ፡፡

ሐ. አስቴር ትናንትና እዚያ ነበረች፡፡

መ. ነቢያት አሁን መጽሐፍ ታነባለች፡፡

ሠ. አያሌዉ ዛሬ ጧት መረብ ኳስ ተጫወተ፡፡

ረ. እኔ በኃላ እዚያ ተራራ ላይ እወጣለሁ፡፡

ሰ. ዘምዘም አሁን ገና ዜና ታዳምጣለች፡፡

ሸ. ሙስጠፋ ከነገ ወዲያ የትምህርት መሣሪያዎችን ይገዛል፡፡

ቀ. ሄኖክ አሁን ጫማ ይሰፋል፡፡

በ. ያዕቆብ ትናንት ብዙ በራሪ ወረቀቶችን አነበበ፡፡

/ገፅ፣188-189/

ከላይ የቀረበዉ የሂደት ተኮር የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘት አቀራረብ ትኩረቱ በጊዜ ላይ ሲሆን ይህንኑ ጊዜ መቼ እንደተፈፀመ ወይም መቼ እንደሚፈፀም የሚገልፅ የግስ ባህሪ ነው፡፡ በማለት ጊዜን በሦስት ክፍሎ አቅርቧል፡፡የአሁን ጊዜ፣የኃላፊ ጊዜ እና የትንቢት ጊዜ ብሎ በገለፃው ላይ

ከፍሎ አስቀምጧል፡፡ ከሂደት ተኮር የቋንቋው ሥርዓት አንፃር በማብራራትና በምሳሌ እስደግፎ ያቀረበ ስልት ነው፡፡

በተተኳሪው የአማረኛቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ በሂደት ተኮር አቀራረብ የቀረቡት ይዘቶች አቀራራባቸው መልካም ቢሆንም በዚህ ስልት የቀረቡት ይዘቶች ግን እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በመረሃ ትምህርቱም የተካተቱት ተመጣጣኝ የሆኑ ይዘቶች ናቸው፡፡የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶችን በተናጠል እንዲተነትኑ እና የቋንቋውን ቅርጾች እንዲለማመዷቸው የሚያደረገው ውጤት ተኮር አቀራረብ የበለጠውን ቦታ ወይም አብላጫውን ድርሻ የያዘ መሆኑን ከተደረገው ጥናት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ነገር ግን በሂደት ተኮር ላይም ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆነ መንገድ ሰዋሰውን እንዲማሩ ቢደረግ ተመራጭ ነው፡፡

በአጠቃላይ በደቡብ ክል በተዘጋጀው የ7ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ የሰዋሰው ትምህርት ይዘትን ስንመለከት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ይልቅ ከአጠቃላይ ወደ ዝረዝር ለማቅረብ የተሞከረው የሰዋሰው ትምህርት ይዘት የሚያመዝን ሲሆን፣ከውጤት ተኮርና ከሂደት ተኮር አቀራረብ ዘዴ አንፃር ደግሞ ከሂደት ተኮር ይልቅ ውጤት ተኮር በሆነ ስልት የቀረቡ የሰዋሰው ትምህረት ይዘቶች በስፋት ቀርበዋል፡፡

ከላይ በንፅፅር የቀረቡትን የሰዋሰው አቀራረብ ስልቶች በያዙት ይዘቶች ልክ በቁጥር አስቀምጠን ብንመለከት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአቀራረብ ስልት በውስጡ ያሉት ይዘቶች ወይም ገላፃዎች በቁጥር 5፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ የሰዋሰው ይዘቶች በቁጥር 10፣ ውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት የቀረቡ የሰዋሰው ይዘቶች በቁጥር 14 ሲሆኑ በሂደት ተኮር አቀራረብ ስልት ደግሞ በቁጥር 1 ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 4.3. በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

### 4.3.1 ተከታታይነት

በክለሳ ድርሳን ላይ እንደተገለፃወ በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች በዚያው ክፍል ደረጃ በተለያየ ምዕራፍ ወይም በሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ እየተደጋገመ መምጣት ማለት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆነው መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ምን ያህል የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች በተለያየ መጠን ተደጋግመው እንደቀረቡ ቀጥሎ ከቀረበው ሠንጠረዥ ማየት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 2. **በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ተከታታይነት ኖሮአቸው የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች**

| የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች በአብይ ክፍል ደረጃ | የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች በንዑስ ክፍል ደረጃ | የሚገኙበት ገፅ | የድግግሞሽ መጠን | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ስነ አገባብ | ድርብ ዓረፍተ ነገሮች መነጠል | 13፣20 | 2 | 3% |
| | አያያዦችን መጠቀም | 32-33፣8.39 | 3 | 5% |
| | ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መመሥረት | 127፣119-120፣133፣154-155፣27 | 4 | 7% |
| | ጥገኛ ዓረፍተ ነገር አሟልቶ መፃፍ | 147፣141 | 2 | 3% |
| | መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር መመሥረት | 230፣202፣224-225 | 3 | 5% |
| | አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተ ነገርን መለየት | 94-95፣216-217 | 2 | 3% |
| | አዎንታዊ፣አሉታዊና መጠይቃዊ ዓ.ነገር | 108 | 1 | 2% |
| | ስሞች እንደ መሙያ ሲገቡ | 172 | 1 | 2% |
| ስነ ምዕላድ | መስተዋድድ(ውስብስብ ዐ.ነገር መመሥረት) | 27 | 1 | 2% |
| | ጠቋሚ መስተአምር | 48፣164 | 2 | 3% |
| | ጠቋሚ መስተአምርና የመሆን ግስ | 54 | 1 | 2% |
| | ተውስከ ግስ | 70 | 1 | 2% |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | መደብና ተውላጠ ስሞች | 76፣77 | 1 | 2% |
| | ጠቋሚ መስተአምር ከመሙያ ጋር | 62፣179-180 | 2 | 3% |
| | ተውሳከ ግስ፣ተውላጠ ስምና መደብ | 85 | 1 | 2% |
| | የጊዜና የቦታ ተውሳከ ግስ | 197-198 | 1 | 2% |
| | ተውሳከ ግስ፣መደብና ጊዜ አመልካች | 206 | 1 | 2% |
| | ጊዜ(አሁን፣የኃላፊና የትንቢያ | 188-189 | 1 | 2% |
| | ድምር | | 30 | 52% |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተመለከተው በተለያዩ ምዕራፎች ከቀረቡት 30(ሠላሳ) የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች መካከል ሃያ (20) የሚሆኑት በተለያየ መጠን ከሁለት እስከ አራት ተደጋገመ የቀረቡ ሲሆን ምንም ሳይደጋገሙ አንድ ጊዜ ብቻየቀረቡ ደግም 10 የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ናቸው።

በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ወስጥ ከቀረቡ የሰዋሰው አረፍተ ነገር ይዘቶች መካከል ካሉት በከፍተኛ ደረጃ ተደጋግሞ የቀረበው"ውስብስብ አረፍተ ነገር መመሥረት" የሚል ነው። ይዘቱ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አራት ጊዜ ተደጋግሞ ቀርቧል።

ይህም በሁለት ምዕራፎች (በምዕራፍ ሁለት ሥር እና በምዕራፍ ስድስት ሥር) በተለያዩ ገጾች ላይ የሚገኝ ሲሆን፣መደጋገሙ ደግሞ ትምህርቱን በተጠናከረ ሁኔታ ተማሪዎች እንዲገነዘቡ ከፍተኛ አስተዋጾኦ እንደሚኖረው ይገመታል። በመቶኛ ያለው ድርሻም ከጠቅላላው 7% ሻፍኗል።

በሁለተኛ ደረጃ ተደጋግሞ የቀረበው "አያያዦችን መጠቀምና መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር መመስረት"የሚሉ አረፍተ ነገሮች በተለያየ መንገድ ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶቸ ናቸው። በመቶኛ ያላቸው ድርሻም 5% ነው

ቀጥለው ሁለት ሁለት ጊዜ ብቻ የተደጋገሙ አምስት ይዘቶች ውስጥ ሦስቱ እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ጊዜ ተደጋግመው ቀርበዋል።እነዚህም"ድርብ አረፍተ ነገሮችን መነጠል፣ጥገኛ አረፍተ ነገር አሟልቶ መጻፍ እና አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች መለየት ሲሆን ቀሪዎቹ ሁለቱ ደግሞ ከስነ ምዕላድ አንፃር የቀረቡ ናቸው። እነዚህ ጠቋሚ መስተአምርና ጠቋሚ

መስተአምር ሁለት ሁለት ጊዜ ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዳቸው በመቶኛ ያላቸው ድርሻ 3% ነው፡፡  በሌላ በኩል ደግሞ ሳይደጋገሙ አንድ ጊዜ ብቻ የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አስር ሲሆኑ በመቶኛ ያላቸው ድርሻ 2% ሆንዋል፡፡ ሳይደጋገሙ አንደ ጊዜ ብቻ የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ከመቶ 20% ይደርሳሉ፡፡

በአጠቃላይ የይዘቶች ተከታታይነት  ከመርሃ ትምህርቱ ጋር የተስማማ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን በዚህ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ይዘቶች ተከታታይነት መልካም ሆኖ የድግግሞሽ መጠን ዝቅተኛ ሆኖ ታይቷል፡፡ ስልዚህ ይህ አቀራረብ ደካማ ስለሆነ ቢሻሻል፡፡

### 4.3.2. ተለጣጣቂነት

ተለጣጣቂነት  በአንድ ክፍል ደረጃ ወይም በተከታታይ የክፍል ደረጃ የሚቀርብ የትምህርት ይዘት መጀመሪያ ከቀረበው የትምህርት ይዘት ተነስቶ ነገር ግን ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ መምጣትን የሚመለከት እንደሆነ በክለሣ ድርሳናት ክፍል ተጠቁሟል፡፡

በደቡብ ክልል የ7ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሐፍ ውስጥ 52% የሚሆኑት የሰዋሰው ይዘቶች በተለያ መጠን ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡ እነዚህ በመማሪያ መጻሐፍ ውስጥ የተደጋገሙት የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ምን ያህል ተለጣጣቂነት እንዳላቸው እናያለን፡፡

በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ተደጋግመዉ ከመጡት ይዘቶች መካከል"ዉስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን መመሥረት" በምዕራፍ ስድስት ዉስብስብ ዓረፍተ ነገር መሥረታ በተመለከተ የተካተቱት የትምህርት ይዘቶች ሦስት ተደጋግመዉ ቀርበዋል፡፡

ሰዋሰዉን በተመለከተ የቀረበዉ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘት በሁለት ምዕራፍ ማለትም በምዕራፍ ስድስት እና በምዕራብ ሦስት ቀርቦ የሚገኝ ሲሆን መልመጃዎቹ የቀረቡበትም ገፅ በሠንጠረዥ2 ላይ ተጠቁሟል፡፡ ይህ አራት ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበ ይዘት ምን ያህል ተለጣጠቂነትን ጠብቆ እንደተደራጀ ስንመለከት ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከግልፅ ወደ ዉስብስብ እንደገና ስፋና ጥልቀት እየጨመረ መሄዱን በግልፅ ያሳያል፡፡

በገፅ/27/ በመእራፍ ሁለት ስለ ዉስብስብ ዓረፍተ ነገር የቀረበበት መጀመሪያ ክፍል ሲሆን ይዘቱ በገለፃና በምሳሌ ተደግፎ የቀረበ ሲሆን ተማሪዎች በጥንድ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በመስተዋድድ በማያያዝ ዉስብስብ ዓረፍተ ነገር ይመሠርታሉ፡፡

በቀጣይ የሰዋሰዉ ትምህርት በገፅ/119-120/ ላይ ዉስብስብ ዓረፍተ ነገር ለማስተማር ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ነጠላ/ተራ/ አረፈተ ነገሮችን በአያያዦች አማካኝነት በማጣመር ሌሎች ዉስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን መመሥረት እንደሚቻል በምሳሌ አስደግፎ በማብራራት ተማሪዎች እንዲተገብሩ ያደርጋል፡፡ ሌላዉ ስለዉስብስብ ዓረፍተ ነገር ገፅ/127/ ላይ ደግሞ ቀደም ሲል ስለዉስብስብ ዓረፍተ ነገር በተለያየ መንገድ እዉቀት ካስጨበጥ በኋላ የቀረቡትን አያያዦች በመጠቀም በምሳሌዉ መሰረት አምስት ዉስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ተማሪዎች እንዲሰሩ አደረገ ወይም አቀረበ፡፡ በተጨማሪ ደግሞ በገፅ/133/ ላይ ስለ "ዉስብስብ ዓረፍተ ነገር" የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም ስድስት ዉስብስብ ዓረፍተ ነገሮች መሥርቱ የሚል ጥያቄ ይገኛል፡፡ ይህም አቀራረብ ከሌሎች በተለየ መልኩ የቀረበ ስለመሆኑ በግልፅ ታይቷል፡፡ ይዘቱ ስፋትና ጥልቀቱን እየጨመረ የመጣ መሆኑንም በግልፅ ታይቷል፡፡

ቀጥሎ አያያዦችን መጠቀምን ዓረፍተ ነገር ምሥርተን በተመለከተ በገፅ/32-33፣8፣39/ በምዕራፍ ሁለትና በምዕራፍ አንድ የቀረበ ሲሆን፣ በምዕራፍ አንድ/በገፅ፣8/ አንድ ጊዜ፣ በምዕራፍ ሁለት በገፅ/32-33፣39/ ሁለት ጊዜ፣ በጥቅሉ ሦስት ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ ከቀረቡት ሦስት የዓረፍተ ነገር ምስረታ ላይ ትኩረታቸዉን ካደረጉት መልመጃዎች መካከል አንዱ አያያዦችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር አሟሉ፣/ገፅ፣33/ ላይ፣ በገፅ/8/ ላይ ደግሞ ቀጥሎ በተሰጡት ድርብ ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ያሉትን አያያዦች አስምሩባቸዉ፣በገፅ /39/ ላይ ደግሞ አያያዦችን በመጠቀም አምስት ድርብ አረፍተ ነገሮችን መስርቱ የሚል ትዕዛዝ ቀርቧል፡፡ ትዕዛዙን ተከትሎ ሁለት ግልፅ የሆነ ማስታወሻና ምሳሌ ከቀረበ በኋላ ከድርብ ዓፍተ ነገሮች ዉስጥ አያያዦችን ለይተዉ እንዲያስምሩባቸዉ፣ አያያዦችን በዝርዝር ካቀረበ በኋላ የቀረቡትን አያያዦች በክፍት ቦታ ማስገባት ዓረፍተ ነገሩን እንዲያሟሉ፣ በመጨረሻም በተለያየ መንገድ የተገነዘበትን ደግሞ አያያዦችን በመጠቀም አምስት ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ የሚያደርጉ ጥያቄዎች ይገኛሉ፡፡ ቀጥሎ ደግሞ አምስት መልመጃዎች እያንዳዳቸዉ ሁለት ሁለት ጊዜ የተደገሙ ሲሆን፣ በገፅ/13፣20/ ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን መነጠል፣ ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት በሚል በምዕረፍ አንድ በቻ ተደጋግመዉ ቀርበዋል፡፡ በገፅ/147፣141/ ላይ ስለ ጥገኛ ዓረፍተ ነገር አሟልቶ መጻፍ፣ የቀረቡትን ነጠላ አረፍተ ነገሮች መስተዋድዶችን በመጠቀም ወደ ጥገኛ አረፍተ ነገሮች ለወጧቸዉ በማለት በበቂ ገለጻና በበቂ ምሳሌ በመስደገፍ አቅርቧል፡፡

በገፅ/48፣164/ ስለ ጠቋሚ መስተአምር ለማስተማር የሚያግዝ ገለፃ ከቀረበ በኋላ በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ያሉትን ጠቋሚ መሰተአምርን ለይታችሁ ፃፉ፡፡ የሚል ጥያቄ ሲገኝ በገፅ/164/ ላይ ደግሞ መስተአምሮችን በዝርዝር ካስቀመጠ በኋላ የሚከተሉት መስተአምሮች የዓረፍተ ነገሩን ባለቤት እዲጠቁሙ አድረጋችሁ አስገቧቸዉ፡፡ በማለት የተለያየ ዘዴ በመጠቀም የቀረቡ ጥያቄዎች ይገኛሉ፡፡ በገፅ/94-95፣216-217/ ላይ ስለ አዉንታዊና አሉታዊ አረፍተ ነገሮች መለየት በሚል ትምህርቱን በገለጻ አስደግፎ ካቀረበ በኋላ ከዚህ በታች የተሰጡትን ዓረፍተ ነገሮች አዉንታዊና አሉታዊ በማለት ለዩ፡፡በገፅ/216-217/ ላይ ደግሞ ከዘህ በታች የቀረቡትን አዉንታዊ ዓረፍተ ነገሮች ወደ አሉታዊ ቀይራችሁ ጻፏቸዉ፡፡ በማለት በምዕረፍ አምስት እና በምዕራፍ አስር በሁለት ምዕረፎች ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡ የመጨረሻዉና አምስተኛዉ በገፅ/62.179-180/ ላይ ጠቋሚ መስተዓመር ከመሙያ ጋር የሚለዉን ለማስተማር ጠቋሚ መስተአመርንና ስምን እንደ መሙያ የያዙ ስድስት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ የሚል ጥያቄ ቀርቧል፡፡ በገፅ/179-180/ ላይ ደግሞ ጠቋሚመስተአምረና መሙያ የሚለዉን ለማስተማር የሚከተሉትን መስተአመሮች በክፍት ቦታ ላይ በማስገባት አንቀጹን የተሟላ አድርጉ በሚል ትዕዛዝ ጥያቄዉ ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ ሶስትና በምዕረፍ ስምንት ላይ ቀርቦ ይገኛል፡፡ ከላይ እንደተመለከትነዉ መማሪያ መጽሐፉ ለተማሪዎች ዓረፍተ ነገሮችን ከአገልግሎታቸዉና ከሰዋሰዋዊ ቅርጻቸዉ አንጻር መመስረት እንዲችሉ ለማስተማር የቀረቡተ ጥያቄዎች በቂና ተመጣጣኝ አይደሉም፡፡ ተመጣጣኝ ባለመሆናቸዉም ተለጣጣቂነት የሆነ አደረጃጀት የላቸዉም ማለት ይቻላል፡፡ በተለይም ዉስብስብ ዓረፍተ ነገርን ለማስተማር ተደጋግሞ ሶስት ጊዜ በምዕረፍ ስድስት ስር የተካተቱ ሲሆን ተለጣጣቂነት ኖሯቸዉ የተደረጁ አይደሉም ምክንያቱም በገፅ/127፣119-120፣133/ በሦስቱም ገጻች ላይ ያሉት መልመጃዎች ትኩረት ዉስብስብ ዓረፍተ ነገር መመስረት ላይ ብቻ ነዉ፡፡ ምንም እንኳን ይዘቶች በአንድ ምዕራፍ ተደጋግሞ የቀረቡ ቢሆንም ከመረሀ ትምህርቱ ጋር ተጣጥሞ መቀረባቸዉ ከአደረጃጀቱ ጠንካራ ጎኖች መካከል ተጠቃሽ ናቸዉ፡፡

### 4.3.3. መማሪያ መጽሐፍ ከመረሃ ትምህርቱ ጋር ያለዉ ዝምድና

**ሠንጠረዥ3 በደቡብ ክልል የ7ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መረሃ ትምህርት መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡትን ዝርዝር የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች፡፡**

| በመርሃ ትምህርቱና መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት ዝርዝር የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች | መርሃ ትምህርት | መማሪያ መጽሐፍ |
|---|---|---|
| ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን መነጠል | ✓ | ✓ |
| አያያዦችን መጠቀም | ✓ | ✓ |
| ዉስብስብ ዓረፍተ ነገር መመሥረት | ✓ | ✓ |
| ጥገኛ ዓረፍተ ነገር አሟልቶ መፃፍ | ✓ | ✓ |
| መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር | ✓ | ✓ |
| መስተዋድድ | ✓ | ✓ |
| ጠቋሚ መስተአምር | ✓ | ✓ |
| ጠቋሚ መስተአምርና የመሆን ግስ | ✓ | ✓ |
| መደብና ተዉላጠ ስሞች | ✓ | ✓ |
| አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች | ✓ | ✓ |
| መጠይቃዊ ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች | ✓ | ✓ |
| ዉስብስብ ዓረፍተ ነገርን መመስረት | ✓ | ✓ |
| ጥገኛ ዓረፍተ ነገር | ✓ | ✓ |
| ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት | ✓ | ✓ |
| አያያዦችን መጠቀም | ✓ | ✓ |
| ጠቋሚ መስተአምር ከመሙያ ጋር | ✓ | ✓ |
| ተዉሳከ ግስ፣ ተዉላጠ ስምና መደብ | ✓ | ✓ |
| አዎንታዊና አሉታዊ መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር | ✓ | ✓ |
| አያያዦችን በመጠቀም ዉስብስብ ዓረፍተ ነገር መመሰረት | ✓ | ✓ |
| መስተዋድዶችን በመጠቀም ዉስብስብ ዓረፍተ ነገር መመስረት | ✓ | ✓ |
| ጠቋሚ መስተአመሮች | ✓ | ✓ |
| ስሞች እንደ መሙያ ሲገቡ | ✓ | ✓ |
| የጊዜና የቦታ ተዉሳከ ግስ | ✓ | ✓ |
| አዎንታዊ አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች | ✓ | ✓ |
| መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገሮች | ✓ | ✓ |
| ጊዜ | ✓ | ✓ |

ከላይ ከቀረበዉ ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለዉ የ7ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ያካተታቸዉ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች በሙሉ ለደረጃዉ በተዘጋጀዉ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የድግግሞሽ መጠናቸዉ ቢያንስም አብዛኞቹ እየተደጋገሙ ጥቂቶችም ሳይደጋገሙ ቀርበዋል፡፡ ከዚህም አኳያ መማሪያ መፅሐፉና መርሃ ትምህርቱ ጥብቅ ትስስር እንዳላቸዉ ማየት ተችሏል፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ የተካተቱ የሰዋሰዉ የትምህርት ይዘቶች በሙሉ በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ተካተዉ ተገኝተዋል፡፡ በዚህ መሰረት የ7ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍና መርሃ ትምህርቱ ተጣጥሞሽ ያላቸዉ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 4.4. በማማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ትኩረት የተሰጣቸዉ የሰዋስው ግብአቶች

### 4.4.1. የቋንቋ ክፍሎች

እነዚህ የቋንቋ ክፍሎች በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ በሰዋሰዉ ትምህርት ክፍሎች ማለትም በስነ አገባብና በስነ ምዕላድ ሥር ተጠቃለዉ የቀረቡና በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ትኩረት የተሰጣቸዉ ግብአቶች ናቸዉ፡፡ እነዚህም በዝርዝር የቀረቡ የቋንቋ ክፍሎች አያያዥ ቃላት፣ ጠቋሚ መስተአምሮች፣ ተዉሳከ ግስ፣ ተዉላጠ ስምና መደብ፣ መስተዋድድና አረፍተ ነገር ሲሆኑ እነዚህንም በተብራራ ሁኔታ በመማሪያ መጽሐፉ አጠቃላይ ቅኝት በሠነድ ፍተሻዉ ሥር ከተገቢነታቸዉም አንፃር ሠፍሮ ይገኛል፡፡ በዚሁ ተተኳሪ መጽሐፍ ዉስጥ ትኩረት የተሰጣቸዉ የቋንቋ ወይም የሰዋሰዉ ክፍሎች ስነአገባብና ስነምዕላድ ሲሆኑ ሌሎች ማለትም ስነድምፅ፣ ያልተካተተበትና ለስነፍቺዉም በግልፅ ፊቺዉን ያለማሳየቱ ከቀረበዉ የድግግሞሽ መጠን በመነሳት ተመጣጣኝ ያለመሆኑን በሠነድ ፍተሻዉ ተመልክቷል፡፡

እንደ ምሁራኑ አገላለፅ እና አተያይ"ሰዋሰዋዊ ፍቺ" የሚለዉ ስያሜ ከቅርፃዊ ሰዋሰዉ ስር የሚወለዉን ፍች ይመለከታል፡፡ ይህን ፅንስ ሀሳብ ur(1996፣76) "ሰዋሰዋዊ ፍች ብለዉ ሲገለፁ Celce Murcia and hilles ደግሞ" ስነ ትርጉማዊ ፍች(1988፣9) ብለዉ ገልፀዉታል፡፡ ይህንኑ እንደገና ur(1988፣11) በበኩላቸዉ "ሰዋሰዋዊ ፍች" የሚለዉ ስያሜ ገላጭ ስነ-ልሳናዊያን የሚሰጡትን ዓይነት ፍቺ የሚመለከት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በዚህ የተነሳ በዚህ ጥናት ዉስጥ"ሰዋሰዋዊ ፍች" ተብሎ የተገለፀዉ ስነ- ትርጉማዊ ሰዋሰዋዊያን ወይም ገላጭ ሰዋሰዋዊያን የሚተነትኑትን የቅርፃዊ ሰዋሰዉ ፍችን ይመለከታል፡፡

በዚህ መስረት በመማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ ትኩረት ከተሰጠባቸዉ መልመጃዎች ዉስጥ አንዱ የሆነዉን የቋንቋ ክፍል/አያያዥ ቃላት/ በመጠቀም ድርብ አረፍተ ነገር እንዲሰሩ/እንዲመሠረቱ/ የቀረበዉን ለአብነት ለማንሳትና በቅርጻዊ ሰዋሰዋዊና ፍች የተሰጠዉን ትኩረት እንመለከታለን፡፡

1. **የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም ስድስት ዉስብስብ አረፍተ ነገሮች መሥርቱ፡፡**
   **እና፣ ግን፣ እንጂ፣ ስለዚህ፣ ይሁን እንጂ**

ገፅ/133/

2. **አያያዦችን በመጠቀም አምስት ድርብ አረፍተ ነገሮችን መሥርቱ፡፡**

3. **ቀጥሎ የቀረቡትን ነጠላ አረፍተ ነገሮች ስለ- ከ- በ-እንደ- ለ- የሚሉትን መስተዋድዶች በመጠቀም ወደ ጥገኛ አረፍተ ነገሮች ለዉጧቸዉ፡፡**

ገፅ/141/

ከላይ የቀረቡት መልመጃዎች ትኩረት የሚያደርጉት አያያዦችንና መስተዋድዶችን በመጠቀም አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱና በቅርፃዊ ሰዋሰዉ ሥርዓት ላይ ትኩረት ያደረገ ይመስላል እንጂ ለፍች ትኩረት የሰጠ አይመስልም፡፡ ከቀረቡት የመልመጃ ጥያቄዎች አንፃር ሲታይ የዚህ መልመጃ ትኩረቱ በቃላት ፍች ላይ ሳይሆን የአያያዥና የመስተዋድድ ቃላትን በመጠቀም ለአረፍተ ነገር ምስረታ ቅርጻዊ ሰዋሰዉ ላይ ትኩረቱን ያሳደረ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ቅርፃዊ ሰዋሰዉና ፍችዉን ለማሳየት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የቀረበ ነገር የለም፡፡ ጎልቶ የሚታየዉ ለቅርፃዊ ሰዋሰዉና ለአረፍተ ነገር ቅርፃዊ ሥርዓት ብቻ ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር ከላይ የቀረቡትን ጥያቀዎች ትዕዛዝ መሠረት ያደረገዉ ወይም ትኩረቱ የቋንቋ ቅርፃዊ ሥርዓትን በመከተል እንዲሠራ ነዉ እንጂ "የቋንቋ ቅርፃዊ ሥርዓትና ፍች" ለመግለፅ ተብራርቶ አልቀረበም፡፡

በጥቅሉ እስከ አሁን ያነሳነዉ ሀሳብ መልመጃዎቹ ትኩረት ለሰጣቸዉ የቋንቋ ክፍሎች ቅርፃዊ ሥርዓታቸዉንና ፍችያቸዉን በግልፅ በመማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ ቀርበዋል ወይ? የሚል ጥያቂ ነበር፡፡ ከመልመጃዎቹ በተገኘዉ መረጃ መሰረት ለቅርፃዊ ስርዓት የተሰጠዉ ትኩረት ከፍተኛ ሲሆን ለፍች የተሰጠዉ ትኩረት በጣም አነስተኛ መሆኑን ነዉ፡፡

ከዚህ ነጥብ ጋር ተዘማጅነት ሊኖረዉ ይችላል ተብሎ የተገመተዉን ጥያቄ ለተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቅ፣ ለመምህራን በቃል መጠይቅ የቀረበላቸዉን ጥያቄና የሰጡት ምላሽ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡ በመማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ የቀረቡትን ሰዋሰዋዊ መልመጃ ለቋንቋ ቅርፃዊ ሥርዓትና

ፍች ተማጣጣኝ ትኩረት መስጠትን አስመልክቶ ለመምህራን ለቀረቡላቸዉ ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ

*መምህር1. ተመጣጣኝ ትኩረት ሰጥቷል ብዬ አላስብም፡፡ ምክንያቱም በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት ይዘቶች ትኩረት የሚያደርጉት በሰዋሰወዊ ፍቺ ላይ ሳይሆን በቅርጻዊ ስርአት ላይ ብቻ ስለሆነ፡፡ የቃላት ፍቺ ቢኖርም በሰዋሰዉ ስር ሳይሆን ራሱን ችሎ በቃላት ጥናት ስር የቀረበ ነዉ፡፡*

*መምህር2. ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በቀረበዉ ሀሳብ እስማማለሁ፡፡ ሰዋሰዋዊ ፍቺ ላይ ባያተኩርም በአንብቦ መረዳት ዉስጥ የቃላትን ፍቺ በሰፊዉ ስለሚያስተምር*

*መምህር3. በመጽሐፍ ዉስጥ የቀረበዉ የሰዋሰዉ ይዘት አነስተኛ ነዉ፡፡ በቂ ጊዜና የተመጣጠነ ትኩረት ለሁለም ይዘቶች እኩል አልተሰጠም፡፡*

*መምህር4. ለቋንቋዉ ቅረጻዊ ስረዓትና ፍቺ ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት አልተሰጠም፡፡ ትኩረቱ በቅርጻዊ ስረአት ላይ ነዉ፡፡*

ሦስት ሴት መምህራን ለቋንቋ ቅርፃዊ ሥርዓት እንጂ ለሰዋሰዋዊ ፍቺ ምንም ዓይነት ትኩረት እንዳልሰጠ ሲያስረዱ አንድ ወንድ መምህር ብቻ በሀሳቡ መስማማታቸዉን ገልፀዋል፡፡ ከመምህራኑ በተጨማሪ በዚህ ጥናት ተተኳሪ በመሆን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ የሚማሩ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የጹሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸዋል እንደሚከተለዉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ (የፅሑፍ መጥይቅ የቀረበላቸዉ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡)

**ሰንጠረዥ 4"በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡትን የሰዋሰዉ መልመጃዎች ለቋንቋ ቅርፃዊ ሥርዓትና ፍቺ ተመጣጣኝ ትኩረት ሰጥተዋል ብለዉ ይስማማሉ?" ተብለዉ በቀረበ ጥያቄ የሰጡት መልስ**

| የጥያቄ ተ.ቁ | ተጠያቂ | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተማሪዎች | | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን ያስቸግረኛል | ፈጽሞ አልስማም | አልስማማም |
| | | በቁጥር | 19 | 23 | 10 | 12 | 36 |
| | | በመቶኛ | 19% | 23% | 10% | 12% | 36% |

ለጥያቄዉ ምላሽ ከሰጡት 100 ተማሪዎች ዉስጥ በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ ያሉት 19(19%)፣ እስማማለሁ ያለት ደግሞ 23(23%) ሲሆኑ ለመወሰን ያስቸግረኛል ያሉት ደግሞ 12(12%) ናቸዉ።

በጥቅሉ ሲታይ አዉንታዊ የሰጡት መምህረን 3 አሉታዊ ምላሽ የሰጠ መምህር 1 ብቻ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ አዎንታዊ ምላሽ የሰጡት ተማሪዎች ደግሞ 42(42%) አሉታዊ ምላሽ የሰጡት ተማሪዎች ብዛት 58(58) ናቸዉ።

የሰነድ ፍተሽ ዉጤት፣ ከመምህራነን ቃለ- መጠይቅ ምላሽና የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ የሚጠቁሙት በመማሪያ መፅሀፍ ዉስጥ የሚገኝ የቋንቋ ቅርጻዊ ሥርዓትና ፍቺ ተመጣጣኝ ትኩረት አለመሰጠቱን ያረጋግጣል። ነገር ግን መማሪያ መጽሐፍ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር እና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በፍተሻዉ ጊዜ ታይቷል። ሁለቱንም መጠቀሙ የመጽሐፉን ጠንካራ ጎን ያመለክታል።

## 4.4.2. በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡ የሰዋሰዉ መልመጃዎች አደረጃጀት

### 4.4.2.1. ከግብዓት ጥልቅ ዝርዝር ባህርይ አንጻር

በዚህ የአደረጃጀት ስልት ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለፃ ይቀርብላችዋል። ከገለጻዉም በመነሳት ህግጋቱን በተግባር ላይ ለማዋልና ለተግባቦት ይጠቀምበታል። ሆኖም ይህ ብቻ በቂ እንደማይሆን ምሁራን ያስቀምጣሉ። ምክንያቱም የተማሪዎች በገለፃ ብቻ በመታገዝ ህግጋቱን በጥቅም ላይ ወይም ለተግባቦት ማዋል አዳጋች ሊሆንባቸዉ ይችላል። ስለዚህ ገለፃዉ በበቂ ምሳሌዎች ተደግፎ ሊቀርብ ይገባል ይላሉ (cunningsworth, 1995) በተጨማሪ ይህንኑ ርዕስ በተመለከተ በክለሳ ድርሰን ላይ ለመግለፅ ተሞክሯል።

### 4.4.2.2 ከጥልቅ ወደ ዝርዝር የተደራጀ

የሰዋሰዉ መልመጃዎች ትኩረት ከተሰጠዉ የቋንቋ ክፍል ወይም ከግበዓት ጥቅል ሰዋሰዋዊ ባህርይ ወደዝርዝር ባህርያቱ መደራጀት እንዳለባቸዉ በክለሳ ድርሳን ተገልጻል።

ከዚህ አንጻር ትኩርት ከተሰጣቸዉ ጥቅል የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ባህርይ ወደ ዝርዝር ባህሪያቱ የተደራጁ የሚመስሉ መልመጃዎች አልፎ አልፎ በመማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ ቀርበዉ ይገኛሉ። እነዚህንም ለአብነት እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

4. **ቀጥሎ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች የጠቋሚ መስተአምሮችንና የመሆን ግሱን ቦታ በመጠበቅ አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡**

ጠቋሚ መስተአምርና የመሆን ግስ

ማስታወሻ

የመሆን ግሶች ከሚባሉት መካከል መሆንን ወይም ሁነትን የሚገልፁ ግሶች ስምን ለመሙያነት ይወስዳሉ፡፡ እነዚህ የመሆን ግሶች፣ ሆነ፣ ነዉ፣ ናት፣ ናቸዉ እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡ እነዚህ መስተዓምሮች ደግሞ በመሙያነት ከሚገባዉ ስም ቀድመዉ በመምጣት ጠቋሚዉን ስም ከሚገኝበት ቦታ አንፃር የመጠቆም ተግባር ያከናዉናሉ፡፡

ምሳሌ፡- "እነዚያ ዋልያዎች ናቸዉ" በሚለዉ አረፍተ ነገር ዉስጥ "ናቸዉ" የመሆን ግስ "ዋልያዎች" የሚለዉ ስም ደግሞ ለመሆን ግሱ መሙያ ነዉ፡፡ እነዚያ የሚለዉ መስተዓምር ስሙን ይጠቁማል፡፡

ሀ. እነዚያ ናቸዉ በጎች፡፡

ለ. ግመል ነዉ ይህ፡፡

ሐ. ተራራ ያ ነዉ፡፡

መ. ተያቢ ናት ይቺ፡፡

ማስታወሻ

ተዉሳከ ግስ

ተዉሳከ ግስ ማለት የግስ ተጨማሪ ወይም ግስን የሚገልፅ ማለት ነዉ፡፡ መደበኛ ተዉሳከ ግሶች በቁጥር ጥቂት ሲሆኑ አገባባቸዉም ከግስ በፊት ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ ከግሱ በፊት ገብቶ ግሱን የገለፀ ቃል ሁሉ ተዉሳከ ግስ ላይሆን ይችላል፡፡ ተዉሳከ ግሶች ግሱን የሚገልጹት ከቦታ፣ ከጊዜ፣ ከሁኔታ ወዘተ አንፃር ነዉ፡፡

ምሳሌ፡- ኃይሉ እዚህ ነበር፡፡(ቦታን)

ፅጌሬዳ ነገ ትመጣለች፡፡ (ጊዜን)

5. **ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ባሉት ክፍት ቦታዎች ተገቢዉን ተዉሳከ ግስ በመፃፍ አገልግሎቱን ግለጹ፡፡**

   *ሀ. ሁለቱ ልጆች-------መጥተዋል፡፡*

   *ለ. አበራ ዛሬ ------------ነበር፡፡የሚሉት ጥቂቶች ናቸዉ፡፡*

ከፍ ሲል ከመማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ ለአብነት ለመጥቀስ እንደተሞከረዉ በተራ ቁጥር "4" ሥር የተመለከተነዉ ንዑስ መልመጃ በመማሪያ መፅሓፍ ዉስጥ በመስተአምርና በመሆን ግስ ትኩረት አድርጎ የቀረበ ይመስላል፡፡ ለንዑስ መልመጃ የተሰጠዉ ትዕዛዝ በምሳሌዉና በማስታወሻ መሰረት ጠቋሚ መስተዓምርና የመሆን ግሱን ቦታ በመጠበቅ አስተካክሎ መፃፍን ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ትኩረቱ "ነዉ፣ናት፣ ናቸዉ.፣ ሆነ" በሚሉ የቋንቋ ቅርፆች አገባብ ላይ ነዉ፡፡

በተራ ቁጥር"5" ከቋንቋ ሰዋሰዋዊ ክፍሎች አንዱ የሆነዉን ተዉሳከ ግስ አስቀድሞ ማስታወሻ ወይም ገለፃ በመስጠት የተዉሳከ ግስ ምንነት ከሳወቀ በኋላ ቀጥሎ የተሰጠዉ ትዕዛዝ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ባሉት ክፍት ቦታዎች ተገቢዉን ተዉሳከ ግስ በመፃፍ አገልግሎቱን ግለፁ በማለት ቀርቧል፡፡ ይህ ንዑስ መልመጃ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ጉዳይ እንደሚሄድ ያሳያል፡፡

### 4.4.2.3. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አንፃር የተደራጀ

የሰዋሰዉ ትምህርት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ስልት ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡትን የሰዋሰዉ ይዘቶች በምሳሌ እየተደገፉ መልመጃዎችንና ተግባራትን ከሠሩ በኋላ በሂደት የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ሥርዓት በራሳቸዉ እንዲደርሱበት የሚያደርግ አቀራረብ መሆኑም በክለሳ ድርሳን ላይ ተጠቅሷል በተጨማሪም ይህንኑ አደረጃጀት አስመልክተዉ harmer (1987) እና Larsen Freeman(1991)፣ በበኩላቸዉ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልት ተማሪዎች ከቀረቡላቸዉ ዝርዝር ምሳሌዎች በመነሳት የቋንቋዉን ህግጋት እንዲያዉቁ የሚያነሳሳ ነዉ ብለዋል፡፡ ለዚህም ከመማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ የቀረበ ጥያቄ አስረጂ ሊሆን ይችላል፡፡

**6. ቀጥሎ የቀረቡትን አያያዦች በመጠቀም በምሳሌ መሠረት አምስት ዉስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡**

| እና፣ ደግሞ፣ግን፣ ነገር ግን፣ይሁን እንጂ |
|---|

ገፅ/147/

ምሳሌ፡- ጧት ወደ ሥራ ገባሁ፡፡

እስከ አሁን የሰራሁት የለም፡፡

ጧት ወደ ሥራ ልገባ እንጂ የሠራሁት ሥራ የለም፡፡

**7.የሚከተሉትን ጥገኛ አረፍተ ነገሮች በመሳሌዉ መሰረት አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

ምሳሌ፡- ሱሰኝነት ሰዎችን ስለሚጎዳ

ሱሰኝነት ሰዎችን ስለሚጎዳ ከሱስ ነፃ እንሁን፡፡

ገፅ/127/

በዚህ ንዑስ ርዕስ የተመለከትነዉ ከቋንቋ ክፍሎች ጥልቅና ዝርዝር ሰዋሰዉዊ በህርይ አንፃር የሰዋሰዉ መልመጃዎቹን አደረጃጀት ነበር፡፡ ከዚህም አንፃር ከይዘቱ ወይም ከግብዓቱ ጥልቅ ባህርይ ወደ ዝርዝር በህርይ የተደራጁ የተወሰኑ ሲሆኑ ብዙዎች ደግሞ በዚህ ሁኔታ አለመደራጀቱን ለማየት ሞክረናል፡፡

ከዚህ ነጥብ ጋር ተዛማጅነት ይኖረዋል ተብሎ የተገመተ ጥያቄ ለተማሪዎችና ለመምህራን በፅሁፍ መጠይቅና በቃለመጠይቅ የቀረበ ጥያቄና የተገኘ ምላሽ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡ በመማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ የሚገኙ መልመጃዎችይዘቱ/ግብአቱ/ ከጥልቅ በህርይ ወደ ዝርዝር ባህርይ መቅረቡን ምን ያህል ይስማማሉ በሚል ቃል መጠይቅ ከተደረገላቸዉ በኃላ የሰጡት ምላሽ

*መምህር1. ከጥልቅ ባህሪ ወደ ዝርዝር ባህሪ ቀርበዋል፡፡ መጠኑ ቢያንስም በማስታወሻ ተደግፎ ቀርቧል በዚህ በኩል አቀራረቡ ጥሩ ነዉ፡፡*

*መምህር2. በቀረበዉ ሀሳብ እስማማለሁ ምክንያቱም ከጥቅል ወደ ዝርዝር ባህሪ ቀርቦ ነዉ ያገኘሁት፡፡*

*መምህር3. የይዘቱ አቀራረብ ከሌላዉ ይዘት አንጻር ተመጣጣኝ ባይሆንም በጥሩ ሁኔታ ቀርቧል፡፡*

*መምህር4. የሰዋሰዉ መልመጃዎች ከጥቅል ባህሪ ወደ ዝርዝር የቀረቡ ናቸዉ፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ቦታ ላይ ማስታወሻ ብቻ ሰጥቶ ቀጥታ ወደ መልመጃ ይገባል፡፡ ይህ ለተማሪዎች ሊከብድ ይችላል በማለት ገልፀዋል፡፡*

ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸዉ አራት መምህራን ዉስጥ ሦስቱ ከጥልቅ በህሪ ወደ ዝርዝር በህሪይ መቅረቡን አስረድተዋል፡፡ አራተኛዋ መምህርት የሰዋሰዉ መልመጃዎች ከጥልቅ ባህርይ ወደ ዝርዝር ባህርይ የቀረቡ ናቸዉ ካሉ በኃላ አንዳንድ ቦታ ላይ ማስታወሻ ብቻ ሰጥቶ ቀጥታ ያለ ምንም ምሳሌ ወደ መልመጃዎች ማምራቱ አቀራረቡ ለተማሪዎች ሊከብድ ይችላል በማለት ሀሳብ ሰጥታለች፡፡

ከመምህራን በተጨማሪ የፅሁፍ መጠይቅ የቀረበላቸዉ የደረጃ ተማሪዎች ለጥያቄዉ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 5. የሰዋሰዉ መልመጃዎች ይዘቱ/ግብአቱ/ ከጥልቅ በህሪ ወደ ዝርዝር ባህሪይ ቀርቧል ብለዉ ይስማማሉ? ተብሎ ለቀረበዉ ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት መልስ፡፡**

| የጥያቄዉ ተ.ቁ | ተጠያቂ | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ተማሪዎች | | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን ያስቸግረኛል | ፈፅሞ አልስማማም | አልስማም |
| | | በቁጥር | 20 | 25 | 18 | 17 | 20 |
| | | በመቶኛ | 20% | 25% | 18% | 17% | 20% |

ከላይ የቀረበዉ ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተዉ መጠይቁን ከሞሉት ተማሪወዎች መካከል አዎንታዊ ምላሽ የሰጡት 45(45%) ሲሆን አሉታዊ ምላሽ የሰጡት ተማሪዎች ደግሞ 55(55%)ናቸዉ፡፡ ከሰነድ ፍተሸዉ የተገኘዉ ዉጤትና ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘዉ ዉጠት ተቀራራቢነት ሲኖረዉ ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኘዉ ዉጤት ተደጋጋፊ አልሆነም፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ይዘቱ ከጥልቅ ባህርይ ወደ ዝርዝር ባህርይ የመደራጀት ሁኔታ አነስተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

### 4.4.2.4. ዉጤት ተኮር አደረጃጀት

ዉጤታዊ ስልተ ትወራ የሚከተሉት ወገኖች መጀመሪያ ላይ ለተማሪዎች የሚያቀርቡት ሰዋሰዉን ነዉ፡፡ batsono(1994) እንደገለፁት እነዚህ ወገኖች ተማሪዎች በተደጋጋሚ ለሰዋሰዉ እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡ ሰዋሰዉን የሚያቀርቡት በገለጻ ነዉ፡፡ በመቀጠል በቃላዊ ምሳሌ ነዉ፡፡

ይህንንም የሚያደርጉት የሰዋሰዉን አተገባበር በቃላት ዉስጥ ለማሳየት ነዉ ይላሉ። ዉጤት ተኮር አደረጃጀት በታላሚ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ቅርጽ ያነጣጠረ ነዉ።

### 4.4.2.4.1. ከግብዓቱ ቅረፃዊ የሰዋሰዉ ፊቼ አንፃር

የታላሚዉ ቋንቋ ቅርጻዊና ሰዋሰዋዊ ፍቺ ብቻ ሳይሆን አዉድም ከተማሪዉ ገጠመኝ አንጻር ተመርጦና ተደራጅቶ በግበአትነት ሊቀርብ ይገባል። የሚሄዱትም ከጥቅል ፅንሰ ሀሳብ ወደ አዉድ ወይም ምሳሌዎች ደረጃ በደረጃ ሲዉርዱ እንደሆነ የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ።Harmer (1991), Batstone(1994)

ከዚህ ርዕስ አንጻር በመማርያ መጽሐፍት ዉስጥ በቅርፃዊ ሰዋሰዉ ላይ ያተኮሩ ይዘቶች እንጂ ለፍቺ በግልጽ የቀረበ ይዘት እንደሌለ በሠነድ ፍተሻዉ ታይቷል።

**8.ቀጣዮቹን አያያዦች በትክክል በመጠቀም ጥንድ ጥንድ ሆነዉ የቀረቡትን ነጠላ አረፍተ ነገሮች ወደ ድርብ አረፍተ ነገር ለዉጡ።**

| እና፣ይሁን እንጂ፣ ነገር ግን፣ ስለዚህ፣ እንጂ |
|---|

ሀ. አፈር ህይወት አለዉ።

ለ. አፈር ህይወትን ያለመልማል።

በገፅ/20/

ከመልመጃ 8 ላይ በተሰጠዉ ትዕዛዝ አያያዦችን በመጠቀም የቋንቋዉን ሰወሰዋዊ ፍቺ ሳይሆን በአረፍተ ነገር ቅርጽ ላይ የተመሰረተ ነዉ። በሌላ በኩል መዋቅራዊ ህግጋቱን ብቻ መሰረት ያደረገ ነዉ ለማለት ይቻላል።

### 4.4.2.5.ሂደት ተኮር አንፃር የተራጀ

በሂደት ተኮር አቀራረብ መሰረት ተማሪዉ ያካበተዉን እዉቀት በማህበራዊ ህይወቱ ወደ ተግባር ለዉጦ ለተግባቦት መጠቀም መቻል እንዳለበት ማለትም በስነ ትምህርታዊ ሰዋሰዉ ከአገባብ ደረጃ በላይ በመሄድና ተግባቦታዊ አላማዎችን ለማሳካት ፍቺና አጠቃቀምን ማካተት እንደለበት በክለሳ ድርሳን ተጠቅሷል። ይህንን ርዕስ አስመልክቶ በመማርያ መጽሐፍ የቀረበዉ መልመጃ እንደሚከተለዉ ይቀርባል።

ማስታወሻ

ጊዜ፡- አንድ ድርጊት መቼ እንደተፈጸመና ወይም መቼ እንደሚፈጸም የሚገልጽ የግስ በህርይ ነዉ፡፡ ጊዜ በአምስት ይፈከላል ክፍሎቹም ያሁን፣ የኃላና፣የትንቢት ጊዜ ይባላል፡፡

- የአሁን ጊዜ ሚባለዉ አረፍተ ነገሩ በሚነገርበት ጊዜ የሚፈጸም ድርጊትን ይጠቁማል፡፡

ምሳሌ፡- ኤደን አሁን ደብዳቤ ትጽፋለች

- የኃላፊ ጊዜ አንድ ድርጊት ተፈጽሞ ያለቀ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ምሳሌ፡- አበደላ ትናንትና መኪና ጠገነ፡፡

- የትንቢት ጊዜ አንድ ድርጊት ገና ያልተፈጸመና ወደፊት የሚፈጸም መሆኑን ያሳያል፡፡

ምሳሌ፡- ህሊና ነገ አዲስ አበባ ትሄደለች

ገፅ/188/

### 4.4.3. ግብአቱን ከማስገንዘብና አጠቃቀሙን ከማላመድ አንጻር የቀረበ

ግንዛቤ ተኮር መልመጃ "የተባለዉ ሰዋሰዋዊ ግጽታዎችን በማሳወቅ ላይ ያተኮሩ እንደ ምሳሌና መስታወሻ ያሉትን ያመለክታል" ስለሆነም ለእያንዳዱ የሰዋሰዉ ግብአት ባህሪዉን በማስገንዘብ ላይ ያተኮረ ምሳሌ ወይም ማስታወሻና አጠቃቀሙን በማለማመድ ላይ ያተኮረ ጥያቄ ልቀረብ ይገባል፡፡ አደረጃጀታቸዉም ከግንዛቤ ተኮር ወደ አጠቃቀም ተኮር መሆን አለበት፡፡ በቀረበዉ የሰዋሰዉ ግበአት ምንም ነገር ከመፈጸማቸዉ በፊት ባህሪዉን መለየት አለባቸዉ፡፡ ስለዚህም የግብአቱን ሰዋሰዋዊ በህሪ ለማሳየት ላይ ብቻ ያተኮረ ግንዛቤ ተኮር መልመጃ መጀመሪያ ላይ ለተማሪዉ ማቅረብ እንደሚገባ የመሰኩ ምሁራን ይገልጻሉ (harmer 1992,ur,1996) ፡፡

ከዚህ አንጻር በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከቀረቡት መልመጃዎች ከምሳሌዎች አንጻር የቀረቡትን ለአብነት መመልከት ጠቃሚ ይሆናል፡፤

| ማስታወሻ |
|---|
| ሁለት ወይንም ከሁለት በላይ የሆኑ ነጠላ/ተራ አረፍተ ነገሮችን በአያያዦች አማካይነት በማጣመር ሌሎች ዉስብስብ አረፍተ ነገሮችን መመስረት ይቻላል፡፡<br>ምሳሌ፡- የሂሳብ ትምህርት እወዳለሁ፡፡ ነጠላ(ተራ) አረፍተ ነገር |

| |
|---|
| ጥሩ ዉጤት አላመጣሁም።ነጠላ(ተራ) አረፍተ ነገር<br>የሂሳብ ትምህርት እወዳለሁ፣ ይሁን እንጂ ጥሩ ዉጤት አላመጣሁም።<br>በምሳሌዉ መሰረት "ይሁን እንጂ" በሚለዉ አያያዥ ሁለቱን ነጠላ አረፍተ ነገሮች በማያያዝ ሌላ ዉስብስብ አረፍተ ነገር ለመመስረት ያስችላል። ገፅ/119-120/ |

**9. ቀጥሎ በሠንጠረዡ ግራና ቀኝ የቀረቡትን ነጠላ/ተራ/ አረፍተ ነገሮች ከተሰጡት አያያዦች መካከል ተገቢዉን በመጠቀም ዉስብስብ አረፍተ ነገሮችን መስርቱ።**

በተራ ቁጥር "9" በተሰጠዉ ትእዛዝ መሰረት በምሳሌዉ ላይ በተረዱት መሰረት አያያዦችን በተገቢዉ ቦታ እንዲጠቀሙና ዉስብስብ አረፍተ ነገሮችን እዲመሰርቱ ከተማሪዎች ይጠበቃል ስለዚህ ይህ ምሳሌ የሰዋሰዉን ጉዳይ በግልፅ የሚገልጽና በትክክል እንዲመሩ መንገድ ከፋች ነዉ።

በዚህ ጽንሰ ሀሳብ መሰረት ተዛማጅነት ይኖረዋል ተብሎ የተገመተ ጥያቄ ለመምህራን በቃለ መጠይቅ፣ ከተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ የቀረበ ጥያቄና የተገኘዉ ምላሽ ቀጥሎ ቀርቧል።

**ጥያቄ3.** በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የሚገኙ ምሳሌዎች እንዲታወቁ የተፈለገዉን የሰዋሰዉ ጉዳይ በግልጽ ያቀርባሉ ብለዉ ያምናሉ? በሚል ቃለመጠይቅ ቀርቦላቸዉ ምለሽ ሲሰጡ

> *መምህር1. ምሳሌዎቹን ተከትለዉ መስራታቸዉ በዉስጡ ያለዉን የሰዋሰዉ ጉዳይ መረዳታቸዉን ያመለክታል። ስለዚህ ሊታወቅ የተፈለገዉ የሰዋሰዉ ጉዳይ ግልጽ ነዉ* በማለት ገልጸዋል።
>
> *መምህር2. ሁሉም የሚሰጡት የሰዋሰዉ መልመጃዎች ግልፅ ናቸዉ። ችግር የለባቸዉም።*
>
> መምህር3፣ በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት ምሳሌዎች ግልጽ ናቸዉ።
>
> መምህር4. *አንዳንድ ጊዜ ምሳሌዎች ብቻ የሰዋሰዉን ጉዳይ ግልጽ ላያደርገዉ ይችላል። ምሳሌና ገለጻ አንድ ላይ ካልተደጋገፉ ግልጽ ላይሆን ይችላል የሚል ሀሳብ ነዉ ያለኝ።* በማለት ገልጸዋል።

ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸዉ አራት መምህራን መካከል ከአንዷ መምህርት በስተቀር ሶስቱ መምህራን በመማሪያ መጽሐፍ ዉሰጥ የቀረቡት ምሳሌዎች ግልፅ ናቸዉ ብለዉ ሲመልሱ አንዷ መምህርት አንዳንድ ጊዜ ምሳሌ ብቻ የሰዋሰዉን ጉዳይ ግልፅ ላያድረግ ይችላል። ምሳሌና ገለፃ አንድ ላይ ካልተደጋገፉ ግልጽ ላይሆን ይችላል። የሚል ሁሳብ ነዉ ያለኝ በማለት መልስ ሰጥታለች።

ሠንጠረዥ 6. **በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡትን ምሳሌዎች እንዲታወቅ የተፈለገዉን የሰዋሰዉ ጉዳይ በግልጽ ያቀርባሉ ብለዉ ይስማማሉ? ለሚለዉ ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ**

| የጥያቄዉ ጥቁር | ተጠያቂዉ | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | ተማሪዎች | | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን ያስቸግረኛል | ፈጽሞ አልስማማም | አልስማማም |
| | | በቁጥር | 38 | 41 | 16 | 10 | 5 |
| | | በመቶኛ | 38% | 41% | 16% | 10% | 5% |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተመለከትነዉ የጽሁፉ መጠይቁን ከሞሉት 100 ተማሪዎች መካከል አዎንታዊ መልስ የሰጡት ተማሪዎች 79/79%/ ሲሆኑ አሉታዊ ምላሽ የሰጡት ደግሞ 31/31%/ ተማሪዎች ናቸዉ፡፡ ይህም ምሳሌዎቹ እንዲታወቅ የተፈለገዉን የሰዋሰዉ ጉዳይ በግልጽ መቅረቡን ያሳያል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በመማርያ መጽሃፍ ዉስጥ በቀረበዉ የሰዋሰው ይዘቶች አደረጃጀት መሠረት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ተማሪዎች በተሰጣቸዉ ምሳሌ እየተደገፉ ወደ ተግባር እንዲገቡ ለማድረግ ዋና ትኩረቱ በምሳሌ ላይ ነው፡፡

ከመማርያ መጽሃፍ ዉስጥ የቀረበዉን ምሳሌ እንመልከትና ወደ ቀጣዩ እንሻገራለን፡፡

**10. ቀጥሎ የቀረቡትን አያያዦች በመጠቀም በምሳሌዉ መሰረት አምስት ዉስብስብ አረፍተ ነገሮችን ፃፉ**

ምሳሌ፡- ሀ. በጧት ወደ ስራ ገባሁ፡፡ ለ. እስካሁን የሰራሁት ስራ የለም ፡፡

በጧት ወደ ሥራ ልግባ እንጂ እስካሁን የሰራሁት ሥራ የለም፡፡

/ገጽ 127/

ከላይ በመማሪያ መጽሃፉ የቀረበዉ መልመጃ ተማሪዎች በምሳሌዉ በመመራት በተሰጣቸዉ (በተራ ቁጥር10) ላይ ባለዉ ትዕዛዝ መሰረት እንዲሰሩ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ ሃሳብ ጋር

ተዛማጅነት ያለዉ ጥያቄ በቃለ መጠይቅ ለመምህራን ፣በጽሁፍ መጠይቅ ለተማሪዎች ቀርቦ እንደሚከተለዉ ምላሽ ተሰጥቶበታል፡፡ በቀረበዉ ቃለመጠይቅ መሰረት መምህራኑ ሲመልሱ፡-

*መምህር1. አዎን! የቀረቡት የሰዋሰዉ ጥያቄዎች በምሳሌዉ መሰረት ሊሰሩ ይችላሉ በማለት ሲገልጹ፡፡*

*መምህር2. በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ጥያቄዎች በምሳሌዎቹ ብቻ ሊሰሩ ይችላሉ ብለዉ መልሰዋል፡፡*

*መምህር3. እንደተማሪዎቹ የልምድ ሁኔታ ልዩነት ምክንያት በምሳሌዎቹ ብቻ ሊሰሩም ላይሰሩም ይችላሉ፡፡*

*መምህር4. በመማሪያ መጽሐፍ የቀረቡት ጥያቄዎች በምሳሌዉ ብቻ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ በማለት ምልስ ሰጥተዋል፡፡*

በመማሪያ መጽሃፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰው ጥያቄዎች በምሳሌዎቹ ብቻ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ብለዉ ይላሉ? ተብሎ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ አንድ መምህርት እንደ ተማሪዎች የልምድ ሁኔታ ልዩነት ምክንያት ጥያቄዎቹ በምሳሌዎቹ ብቻ ሊሰሩም ላይሰሩም ይችላሉ ሲሉ የቀሩት ሦስት መምህራን በምሳሌዎቹ መሰረት ሊሰሩ ይችላሉ በማለት መልሰዋል፡፡

ከመምራኑ በተጨማሪ የጥናቱ ተተኳሪ በሆነዉ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ የሚማሩ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ለቀረበላቸዉ የጽሁፍ መጠይቅ የሚከተለዉን መልስ ሰጥተዋል፡፡

ሠንጠረዥ 7. በመማሪያ መጽሃፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰው ጥያቄዎች በምሳሌዎቹ ብቻ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ብለዉ ይስማማሉ? ተብሎ ለቀረበዉ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ

| የጥያቄዉ ቁጥር | ተጠያቂ | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | ተማሪዎች | | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን ያስቸግረኛል | ፈጽሞ አልስማማም | አልስማማም |
| | | በቁጥር | 48 | 31 | 11 | 2 | 8 |
| | | በመቶኛ | 48% | 31% | 11% | 2% | 8% |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተመለከትነዉ መጠይቁን ሞልተዉ ከመለሱት 100 ተማሪዎች መካከል 79(79%) ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 21(21%)ተማሪዎች አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

ከሰነድ ፍተሸ ዉጤት ፣ከመመህራን ምላሽ እና ከተማሪዎች ጽሁፍ መጠይቅ የተገኘዉ ዉጤት የሚያመለክተዉ በመማሪያ መጽሃፍ ዉስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች በምሳሌዎቹ ብቻ መስራት የሚችሉ መሆናቸዉን ያረጋግጣል።

### 4.4.3.1 ከማስታወሻና ከምሳሌ ወደ ጥያቄ የቀረበ

በመማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የቀረቡ የሰዋሰዉ መልመጃዎች መካከል ከግንዛቤ ወደ ልምምድ ወይም አጠቃቀም ተኮር መልመጃዎች የተደራጁ በርካታ ናቸዉ። ይህም ማለት ገለጻና ማስታወሻ ቀርቦ ግንዛቤ ከተፈጠረ በኋላ ወደ ልምምድና አጠቃቀም መሸገር ማለት ነዉ። ከዚሁ አንጻር በመማሪያ መጽሃፉ ዉስጥ የቀረቡትን እንመለከታለን።

| |
|---|
| ***ማስታዎሽ*** |
| *አዎንታዊ ዓረፍተ ነገር ማለት በዐረፍተ ነገሩ ማሰሪያ አንቀጽ የተቀመጠዉን ድርጊት ሳያፈርስ መናገርን የሚመለከት ነው። አሉታዊ ዓረፍተ ነገር ደግሞ በመጀመሪያ የታወቀን ወይም የተነገርን ሃሳብ የሚያፈርስ አገላለጽ ነው።አዎንታዊ ዓረፍተ ነገር አዎንታዊነቱን የሚያሳይ ቅጥያ የለዉም ። አሉታዊ አረፍተ ነገረ ላይ ግን አል -(-ም) የሚሉ ቅጥያዎች ይወሰዳል።* |
| /ገጽ ፣94-95/ |

**11. ከዚህ በታች የተሰጡትን ዓረፍተ ነገሮች አዎንታዊ አሉታዊ በማለት ለዩ።**

*ሀ.የወይን ሐረግ የተሰራዉን ስራ አላየችም። ለ.በስብሰባዉ ላይ ብዙ ሰዉ አልተገኘም።*

የሚሉት ለአብነት የቀረቡ ናቸዉ።

### 4.4.3.2. ከገለጻዊ ስልት አንጻር ብቻ የተደራጁ

አንዳንድ መልመጃዎች እንዲታወቅ የተፈለገዉን የሰዋሰዉ ባህሪ ከገላጻዊ ስልት አንጻር ብቻ ቀርቦ ይገኛል።

| |
|---|
| ማስታወሻ<br>አያያዥ በሁለት ነጠላ ዓረፍት ነገሮች መካካል እየገቡ ዓረፍተ ነገሮችን ወደ ድርብ ዓርፍተ ነገር መለወጥ የሚያስችሉ ናቸዉ፡፡ እነርሱም፡- እና፣ግን፣ነገር ግን፣እንጂ ወዘተ ናቸዉ፡፡ |

**12. ቀጥሎ በተሰጡ ድርብ ዐረፍተ ነገሮች ዉስጥ ያሉትን ዓያያዦች አስምሩባቸዉ**

*ሀ. ደመናዉ ዳመነ እንጂ ፣ዝናቡ አልዘነበም፡፡ ለ. ከድጃ ትምህርት ቤት መጣች ፣ነገር ግን ክፍል ዉስጥ አልገባችም፡፡ የሚሉት ጥቂቶች ናቸዉ፡፡*

*በተራ ቁጥር 11፣12 ላይ የቀረቡት ንዑስ መልመጃዎች ትዕዛዝ በቀጥታ የተሰጠዉን ገለጻ በመገንዘብ በቀጥታ ወደ ልምምድ እንዲገቡ የሚያደርግ ነዉ፡፡ ከማስታወሻ ቀጥሎ የቀረበ አዉዳዊ ወይም ቃላዊ ምሳሌ የለም፡፡ ልምምዱም ምሳሌን የሚወክል አይደለም፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ በንዑስ መልመጃ ዉስጥ ትኩረት የተሰጠዉ የሰዋሰዉ ግብዓት እንዲታወቅ የተደረገው በገለጻዊ ስልት ብቻ ነዉ፡፡*

*የሰዋሰዉ ግብዓቶችን ለማሳወቅ ገለጻዊ ዘዴ አስፈላጊ ቢሆንም ብቻዉን በቂ አይደለም፡፡ ለዚህም አንዱ ምክንያት ሊሆን የሚችለዉ ለሁሉም ተማሪ የመማር ልምምድ እኩል የሚስማማ አለመሆን ነዉ፡፡*

*እንደ ብዙ ምሁራን አተያይ አንዳንድ ተማሪዎች ገለጻዊ ዘዴ ከነ ምሳሌያዊ አቀራረብ ይበልጥ የሚስማማቸዉ ሲሆን፣አንዳዶች ግን ቃላዊ ዘዴ ይበልጥ ይስማማቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ገለጻዊ ዘዴ የሁሉም ተማሪ የመማር ልምድ መሠረት ያደረገ አይደለም ለማለት ያስደፍራል፡፡ በተጨማሪም ገለጻዊ ዘዴ ብቻዉን የተፈለገዉን የሰዋሰዊ ጽንሰ ሃሰብ ቅርጻዊ ስርዓቱን በተለይም አግባቡን በተጨባጭ የሚያሳይ አይደለም፡፡ በመመሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ቀርበዉ ከሚገኙት የሰዋሰዉ ትምህርት ገለጻ አንጻር ለማስተማር የቀረበዉ ማስታወሻና ገለጻዊ ስልቱ መልካም ነዉ የሚያሳኝ ነዉ፡፡*

*ከዚሁ ጋር ተዛማጅነት ያለዉ ጥያቄ ለመምህራን በቃለ መጠየቅ፣ለተማሪዎች በጽሁፍ መጠየቅ ቀርቧል፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ጥያቄዎች ለገለጻ ወይም ለማስታወሻ ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት ሰጥተዋል ብለዉ ይስማማሉ? የሚል ቃለ መጠይቅ ቀረቦላቸዉ የሚከተለዉን ምላሽ ሰጥተዋል*

*መምህር1. በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት ገለጻዎች ወይም ማስታወሻዎች በጥሩ መንገድ የቀረቡ ናቸዉ፡፡*

*መምህር2. ማስታሻዉ ወይም ገለጻዉ ተማሪዎች ሊረዱት በሚችሉበት ሁኔታ የቀረበ ነዉ፡፡*

*መምህር3. የቀረበዉ ማስታወሻ ወይም ገለጻ ከሌሎች ይዘቶች አንጻር በተመጣጠነ መልክ ትኩረት ተሰጥቶበታል፡፡*

*መምህር4. ጥያቄዎቹ ለገለጻዎቹ ወይም ለማስታሻ ተመጣጣኝ ትኩረት ሰጥቶ ነዉ ያገኘሁት በማለት አስረድተዋል፡፡*

አራቱም መምህራን በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ጥያቄዎች ለገለጻ ወይም ለማስታወሻ ከሌሎች ይዘቶች አንጻር ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት እንደተሰጠዉ አስረድተዋል፡፡ ከመምህራን በተጨማሪ ለዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆነዉ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ የሚማሩ ለ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ይኸዉ ጥያቄ በጽሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸዉ የሚከተለዉን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 8. በመማሪያ መጽሐፉ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ጥያቄዎች ለገለጻ ወይም ለማስተዋሻ ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት ሰጥተዋል ብለው ይስማማሉ? ለሚለዉ የሰጡት መልስ :-**

| የጥያቄዉ ቁጥር | ተጠያቂ | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ተማሪዎች | | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን ያስቸግረኛል | ፈጽሞ አልስማማም | አልስማማም |
| | | በቁጥር | 43 | 28 | 10 | 6 | 13 |
| | | በመቶኛ | 43% | 28% | 10% | 6% | 13% |

ከቀረበዉ ሠንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለዉ መጠይቁን ሞልተዉ ከመለሱ 100 ተማሪዎች መካከል 43(43%) በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ በማለት መልስ ሲሰጡ 28(28%) ደግሞ እስማማለሁ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ለመወሰን ያስቸግረኛል 10(10%)፣ 6(6%) ፈጽሞ አልስማማም ብለዉ የመለሱ ሲሆን አልስማማም ያሉት ደግሞ 13(13%) ናቸዉ፡፡ በአጠቃላይ

አዉንታዊ ምላሽ የሰጡት ተማሪዎች 71(71%) ሲሆኑ አሉታዊ ምላሽ የሰጡት ደግሞ29(29%) ናቸዉ።

ከሰነድ ፍተሸዉ ዉጤት፣ከመምህራን የቃለ መጠይቅ ምላሽና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ አብዛኛዉ ምላሽ የሚያሳየዉ በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ጥያቄዎች ለገለፃ ወይም ለማስታወሻ ትኩረት መስጠታቸዉን ነዉ።

### 4.4.3.3. ከተመጣጣኝነት አንጻር የተደራጁ

የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲቀርቡ ወይም ሲደራጁ ከቋንቋዉ የክሂል ዘርፎች፣የሰዋሰዉ፣ የቃላትና የስነ ጽሁፍ ይዘቶች ተመጣጥነዉ መቅረብ አለበት። የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ የሚኖራቸዉ ስርጭት ከታላሚዉ ቋንቋ ልዩ ልዩ የሰዋሰዉ ክፍሎች ሚዛናዊ በሆነ መልክ መቅረብ አለበት። በዚህም መሰረት ይዘቶቹ ደረጃዉን በጠበቀ ሁኔታ ከቋንቋዉ የድምጽ ስርአት፣ የምዕላድና የቃል ክፍል፣የአገባብና የፍቺ ስርዓት የተዉጣጡ እንዲሆኑ ይጠበቃል። (harmer, 1987,18)::

በዚህ መሰረት በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የሚቀርበዉ የሰዋሰዉ ትምህርት ተማሪዎች የቋንቋዉን ስርአት ትርጉም ባለዉ መንገድ ጠንቅቀዉ በማወቅ በትክክል መገልገል ማስቻል አለበት።

### 4.4.3.4 ከተገቢነት አንጻር የተደራጁ

Harmer(1987,19) ተገቢነትን አስመልክቶ የሚሰጡት ገለፃ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ለቋንቋዉ ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ አንጻር ነዉ። በዚህ መሰረት የአንድ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቅርጾች፣ ፍቺና አጠቃቀም ለማስተማር የሚያስችሉ ወይም ተገቢ መሆን እንዳለባቸዉ የሚያሳይ ነዉ በማለት ግልጸዋል።

በዚህ ጽንሰ ሀሳብ መሰረት ጥናቱ ባተኮረበት የአማርኛ ቋንቋ ማማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት በአራቱም የሰዋሰዉ ይዘቶች አደረጃጀት ማለትም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ዉጤት ተኮር እና በሂደት ተኮር አቀራረቡ የቀረቡትን መልመጃዎች በሠነድ ፍተሸዉ ላይ በግልጽ ለማስቀመጥ እንደተሞከረዉ ሁሉንም የሰዋሰዉ ይዘቶች በተገቢ መልክ አካቶ ማቅረቡ ተጠቁሟል ነገር ግን በአብዛኛዉ ይዘቶቹ የሚያመዝኑት በአገባብና በቋንቋዉ ቅርፃዊ ስረዓት ላይ ነዉ።

በመማሪያ  መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ለደረጃዉ የሚመጥንና ተገቢ ስለመሆኑ ለመምህራን በቃለ መጠቅ፣ለተማሪዎች ደግሞ በፅሑፍ መጠይቅ የቀረበ ሲሆን ቃለ መጠይቁ የቀረበላቸዉ አራት መምህራን እንደሚከተለዉ መልስ ሰጥተዋል

*መምህር1. በመማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰወሰዉ ይዘቶች ለደረጃዉ ተማሪ የሚመጥንና ተገቢ ነዉ።*

*መምህር2. ከመረሃ ትምህርቱም አንጻር ሲታይ ተገቢ ነዉ ብል አልተሳሳትኩም።*

*መምህር3. በመማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የቀረቡት ተመጣጣኝና ተገቢ ናቸዉ።*

*መምህር4. ደረጃዉን የጠበቀ ይዘት ነዉ የቀረበዉ በማት አስረድተዋል።*

ከላይ የቀረቡት አራቱ መምህራን *በመረሀ ትምህርቱም ሆነ በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ይዘቶች ተማሪዉን የሚመጥንና ተገቢ ነዉ* በማት አስረድተዋል።

ቀጥሎ ደግሞ ተዛማጅነት ያለዉን የጽሑፍ መጠይቅ ለተማሪዎች በማቅረብ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 9. **በመማሪያመጽሐፍዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ለደረጀዉ የሚመጥንና ተገቢ መሆኑን ይስማማሉ? ተብሎ ለቀረበዉ የጽሑፍ መጠይቅ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ**

| የጥያቄዉ ቁጥር | ተጠያቂ | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ተማሪዎች | | በከፍተኛ ደረጃ እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን ያስቸግረኛል | ፈጽሞ አልስማማም | አልስማማም |
| | | በቁጥር | 27 | 38 | 10 | 12 | 13 |
| | | በመቶኛ | 27% | 38% | 10% | 12% | 13% |

ከቀረበዉ ሠንጠረዥ ለማየት እንደሚቻለዉ የጽሑፍ መይቁን ከሞሉት 100 ተማሪዎች መካክል 65(65%) አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን አሉታዊ ምላሽ የሰጡት ተማሪዎች ደግሞ 35/35% ናቸዉ።

ከሰነድ ፍተሻዉ ዉጤት፣ ከመምህራን የቃለ መጠይቅ ምላሽና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ የተገኘዉ ዉጤት እንደሚያመለክተዉ በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት ይዘቶች ለደረጃዉ መጣኝና ተገቢነትን ያረጋግጣል፡፡

### 4.4.4. ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ሠንጠረዥ 10. **መምህራን የሰዋሰዉ ይዘቶችን በየዕለቱ በክፍል ዉስጥ አተገባበራቸዉ ምን እንደሚመስል ለማወቅ የተደረገ የምልከታ ዉጤት ትንተና፡፡**

| ተ.ቁ | የምልከታ መከታተያ ነጥቦች | ድግግሞሽ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 2 | የዕለቱን ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ከቀደመዉ እዉቀት በክለሳ ስለ መጀመሩ | 2 (25%) | 4 (50%) | 2 (25%) | - | - |
| 3 | የዕለቱን የሰዋሰዉ ትምህርት ለማስተማር የሚያስችል ዕለታዊና አመታዊ ዕቅድ አዘጋጅቶ ከመግባት አንፃር | 3 (37.5%) | 3 (37.5%) | 2 (25%) | - | - |
| 4 | የዕለቱን ትምህርት በተመለከተ በቂ ዝግጅት ስለመደረጉ | 4 (50%) | 3 (37.5%) | 1 (12.5%) | - | - |
| 5 | የዕለቱ ትምህርት የሰዋሰዉ ክፍሎች ላይ ያለዉ ትኩረት ምን እንደሚመስል | 2 (25%) | 2 (25%) | 2 (25%) | 2 (25%) | |
| 6 | የዕለቱን ትምህርት ሲያስተምሩ በቋንቋ ቅርጻዊ ስረአትና ፍቺ ተመጣጣኝ ትኩረት ስለመደረጉ | - | - | 3 (37.5%) | 5 (62.5%) | - |
| 9 | በሰዋሰዉ ትምህርት ዙሪያ የተማሪዎችን የቀደመ ዕዉቀት ለመመዘን የቀረቡ ጥያቄዎች ስለመኖራቸዉ | - | 4 (50%) | 3 (37.5%) | 1 (12.5%) | - |
| 11 | ሰዋሰዋዊ ምሳሌዎችን እያቀረቡ ከማለማመድ ወይም ከማሰራት አንጻር ሲታይ | 3 (37.5%) | 4 (50%) | 1 (12.5%) | - | - |
| 13 | ተማሪዎች የሰዋሰዉን ህግ በሂደት እንዲያቁ ስለመደረጉ | - | 3 (37.5%) | 3 (37.5%) | 2 (25%) | - |
| 16 | የሰዋሰዉ ትምህርት ሲያስተምሩ የቀረበዉን ይዘት ከተማሪዉ ማህበራዊ ህይወት ጋር አዛምዶና ተጨባጭ አድረጎ ከማስተማር አንፃር | 4 (50%) | 2 (25%) | 2 (25%) | - | - |
| 19 | የቀረበዉን የሰዋሰዉ ትምህርት ከገለጻዊ ስልት አንጻር የማቅረብና የማብራራት ሁኔታ ምን እንደሚመስል | 6 (75%) | 2 (25%) | - | - | - |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 20 | ከሌሎች ክፍሎች አንፃር ለሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ትኩረት ስለመስጠቱ | - | - | 3 (37.5%) | 5 (62.5%) | - |
| 24 | ተማሪዎች የዕለቱን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማወቅና ትመህርቱን ለማጠናከር የቀረቡ ጥያቀዎች ስለመኖራቸዉ | 3 (37.5%) | 2 (25%) | 3 (37.5%) | - | - |
| 26 | የቤትና የክፍል ስራለተማሪዎች አዘወትሮ የመስጠትና ክትትል ከማድረግ አኳያ | 2 (25%) | 3 (37.5%) | 2 (25%) | 1 (12.5%) | - |
| 28 | በክፍል ዉስጥ የሚቀርበዉ ምሳሌ የተማሪዉን አቅም ያገናዘበና የሚመጥን ከመሆንአንፃር | - | 3 (37.5%) | 3 (37.5%) | 2 (25%) | - |
| 30 | ተማሪዎች የሰዋሰዉን ትምህርት ተግባቦታዊ አገልግሎት ላይ እንዲያዉሉ አድርጎ ማስተማር ስለመቻሉ | - | - | 2 (25%) | 6 (75%) | - |

ከሰንጠረዡ ለመረዳት እንደሚቻለዉ በተራ ቁጥር ሁለት "2" ላይ የእለቱን ትምህርት ከመጀመር አስቀድሞ የቅድመ እዉቀት በክለሳ መልክ መጀመሩን በተመለከተ ለቀረበዉ የምልከታ መከታተያ ነጥብ በጣም ከፍተኛ 2 (25%) ክፍተኛ 4 (50%) መካከላኛ 2 (25%) የሆነ ዉጤት ሊገኝ ችሏል፡፡ በተራ ቁጥር "3" ላይ የእለቱን የሰዋሰዉ ትምህርት ለማስተማር የሚያስችል እለታዊና አመታዊ እቅድ አዘጋጅተዉ መግባታቸዉን በተመለከተ የምልከታ መከተታያ ነጥብ የቀረበ ሲሆን በጣም ከፍተኛ 3 (37.5%) ከፍተኛ 3 (37.5%) መካከለኛ 2 (25%) ነዉ፡፡ በተራ ቁጥር "4" የዕለቱን ትምህርት በተመለከተ በቂ ዝግጅት ስለመደረጉ በቀረበዉ የምልከታ መከታተያ ነጥብ በጣም ከፍተኛ 4 (50%) ከፍተኛ 3 (37.5%) መካከለኛ 1 (12.5%) እንደሆነ የምልከታዉ ዉጤት ያሳያል፡፡ በተራ ቁጥር "5" ላይ የእለቱ ትመህርት የሰዋሰዉ ክፍሎች ላይ ያለዉ ትኩረት ምን እንደሚመስል በቀረበዉ የምልከታ መከታተያ ነጥብ በጣም ከፍተኛ 2(25%) ከፍተኛ 2(25%) መካከለኛ 2(25%) ዝቅተኛ 2 (25%) መሆኑን የምልከታ ዉጤቱ የሳያል፡፡

በተራ ቁጥር "6" የእለቱን ትምህርት ሲያስተምሩ በቋንቋ ቅርፃዊ ስርአትና ፍቺ ተመጣጣኝ ትኩረት ስለመደረጉ በተመለከተ በቀረበዉ የምልከታ መከታተያ ነጥብ መካከለኛ 3(37.5%) ዝቅተኛ 5( 62.5%) መሆኑን የጥናቱ ዉጤት ያሳያል፡፡ በተራ ቁጥር "9" ላይ በሰዋሰዉ ትምህርት ዙሪያ የተማሪዎችን የቀደመ እዉቀት ለመመዘን የቀረቡ ጥያቄዎችን በተመላከተ ለቀረበዉ የምልከታ መከታተያ ነጥብ ከፍተኛ 4 (50%) መካከለኛ 3 (37.5%) ዝቅተኛ 1(12.5%) ነዉ፡፡ በተራ ቁጥር "11" ላይ ሰዋሰዋዊ ምሳሌዎችን እያቀረቡ ከማለማመድ ወይም

ከማሰራት አንጻር በቀረበዉ የምልከታ መከታተያ ነጥብ በጣም ከፍተኛ 3 (37.5%) ከፍተኛ 4 (50%) መካከለኛ 1 (12.5%) መሆኑን ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ በተራ ቁጥር "16" ላይ በክፍል ዉስጥ የሰዋሰዉ ትምህርት ሲያስተምሩ የቀረበዉ ይዘት ከተማሪዉ ማህበራዊ ህይወት ጋር አዛምዶና ተጨባጭ አድረጎ መልእክት ከማስተላለፍ ወይም ከመስተማር አኳያ ለቀረበዉ የምልከታ መከታተያ ነጥብ በጣም ከፍተኛ 4 (50%) ከፍተኛ 2 (25%) መካከለኛ 2 (25%) እንደሆነ የምልከታ ዉጤት ያሳያል፡፡ በተራ ቁጥር "24" ተማሪዎች የእለቱን ትምህርት ምን ያህል እደተገነዘቡ ለማወቅና ትምህርቱን ለማጠናከር የቀረቡ ጥያቄዎች ስለመኖራቸዉ ለመፈተሽ በተደረገዉ ምልከታ በጣም ከፍተኛ 3 (37.5%) ከፍተኛ 2 (25%) መካከለኛ 3 ( 37.5%) መሆኑን ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ በተራ ቁጥር "26" ላይ የቤትና የክፍል ስራ ለተማሪዎች አዝወትሮ የመስጠትና ክትትል ከማድረግ አኳያ ለቀረበዉ የምልከታ መከታተያ ነጥብ በጣም ከፍተኛ 2 (25%) ከፍተኛ 3 (37.5%) መካከለኛ 2 (25%) ዝቅተኛ 1 (12.5%) መሆኑን ዉጤቱ ያመለክታል፡፡ በተራ "30" ላይ ተማሪዎች የሰዋሰዉን ትምህርት ተግባቦታዊ አግልግሎት ላይ እንዲያዉሉ ከማስቻል አንጻር ለቀረበዉ ምልከታ መከታተያ ነጥብ መካከለኛ 2 (25%) ዝቅተኛ 6  (75%) መሆኑ ከዉጤቱ ታዉቋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት የምልከታ መከታተያ ነጥቦች ለመረዳት እንደተቻለዉ መምህራኑ የሰዋሰዉ ትምህርት ሲያስተምሩ የእለቱን ትምህርት በክለሳ መልክ መጀመርና የእለቱንም ትምህርት ለማስተማር እንዲያመች እለታዊና አመታዊ አወቅድ አዘጋጅተዉ መግባታቸዉንና በቂ ዝግጁትም እዳደረጉ በተደረገዉ ምልከታ ለማየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም መምህራኑ ሲያስተምሩ ለሰዋሰዋዊ ትምህርት ይዘት መሰረት ባደረገ መልክ ሰዋሰዋዊ መሳሌዎችን ከማሰራትና ከማለመመድ፣ከተማሪዉ ማህበራዊ ህይወት ጋር አዛምዶና ተጨባጭ አድርጎ ከማስተማር አንጻር፣ ተማሪዎች የእለቱን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማወቅና ትምህርቱን ከማጠናከር አኳያ እና የቤትና የክፍል ስራ ከሰዋሰዉ ትምህርት አንጻር መስጠትና ክትትል ከማድረግ አንፃር ጥሩ አፈፃፀም ለማየት ተችሏል ነገር ግን በተከታታይ ምልከታ እንደታየዉ መጠነኛ ክፍተቶች እንዳሉ የምልከታዉ ዉጤት ያሳያል፡፡ የእለቱን ትምህርት ሲያስተምሩ በቋንቋዉ ቅርጻዊ ስረአትና ፍቺ ተመጣጣኝ ትኩረት ከመስጠት አንጻር ዝቅተኛ ነዉ፡፡ መምህራኑ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘትን ከእቅዳቸዉ አንጻር ያስተምሩ እንጂ ተማሪዎች የሰዋዉን ትምህርት ተግባቦታዊ አገልግሎት ላይ እንዲያዉሉ አድርጎ ለማስተማር አለመቻሉ የተደረገዉ ምልከታ አመልክቷል፡፡

ስለዚህ ይህ ምልከታ የተደረገዉ በአራቱም ትምህርት ቤት ዉስጥ ሆኖ አራቱም መምህራን በሚያስተምሩበት ክፍለ ጊዜ ለ8 ተከታታይ ጊዜያት በ30 መከታተያ ነጥቦች ላይ ምልከታ ተደርጎ ዉጤቱም ከላይ በተመለከተዉ ሁኔታ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ11 **የክፍለ ጊዜዉን ትምህርት መመህራን በምን መልክ እደሚያቀርቡት ለማወቅ የተደረገ ምልከታ የተገኙ ምላሾች ትንተና**

| ተ.ቁ | የምልከታ መከታተያ ነጥቦች | ድግግሞሽ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 1 | የሰዋሰዉ ትምህርት የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር ተዘጋጅቶ የቀረበ ይዘት | - | - | 4 (50%) | 4 (50%) | - |
| 7 | ተማሪዎች ስለተማሩት የሰዋሰዉ ትምህርት በራሳቸዉ አባባል ለጓደኞቻቸዉ እንዲገልጹ የማነሳሳት ጉዳይ | - | - | 5 (62.5%) | 3 (37.5%) | - |
| 8 | መምህራን የሰዋሰዉ ይዘቶችን ሲያስተምሩ ተማሪዎችን ለትምህርቱ የማነሳሳትና የማነቃቃት ሁኔታ | - | 4 (50%) | 4 (50%) | - | - |
| 10 | የሰዋሰዉ ይዘቶች ለማስተማር በመማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ ከቀረቡት ጥያቄዎች ሌላ ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ይዘቶችን ከማቅረብ አንጻር | - | - | 2 (25%) | 6 (75%) | |
| 12 | ለተማሪዎች የሚሰጠዉ የሰዋሰዉ መልመጃዎች በቡድንና በግል የሚሰሩና የተማሪዎችን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ ያለዉ አስተዋጽኦ | - | 5 (62.5%) | 3 (37.5%) | - | - |
| 14 | ተማሪዎችን በቤትና በክፍል ስራ የሰሩትን በክፍል ዉስጥ እንዲያቀርቡና እንዲወያዩ ከማድረግ አንጻር ሲታይ | - | 3 (37.5%) | 3 (37.5%) | 2 (25%) | - |
| 15 | የቀረበዉን መልመጃ በምሳሌዎች አስደግፎ በግልጽ ከማቅረብና ከተማሪዎች አእምሮ ከማስረጽ አንፃር | 3 (37.5%) | 2 (25%) | 3 (37.5%) | - | - |
| 17 | ተማሪዎች በመማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት አድርገዉ በራሳቸዉ እዲሰሩ የተሰጣቸዉ ጊዜና የማበረታታት ሁኔታ | 3 (37.5%) | 5 (62.5%) | - | - | - |
| 18 | የቀረቡትን መልመጃዎች በግልጽ የማስረዳት እና እዉቀትን ከማስጨበጥ አንጻር ሲታይ | 4 (50%) | 4 (50%) | - | - | - |
| 21 | የቋንቋ ሰዋሰዉዊ ቅርጾችን መምህራን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ጉዳይ በመሄድ ከማይታወቅ ወደ ሚታወቅ የማቅረቡ ሁኔታ | - | 3 (37.5%) | 3 (37.5%) | 2 (25%) | - |
| 22 | የሰዋሰዉ ትምህርት ለማስተማር አስፈላጊ የሆኑ | - | - | 3 | 5 | - |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን መጠቀማቸዉ | | | (37.5%) | (62.5%) | |
| 23 | ተማሪዎች በሰዋሰዉ ትምህርት የጠለቀ እዉቀት እንዲኖራቸዉ ስለማበረታታት | - | 4 (50%) | 2 (25%) | 2 (25%) | - |
| 25 | ተማሪዎች በሰዋሰዉ ትምህርት ዉስጥ የተካተቱትን ይዘቶች ቅርጻዊ ስረአቱንና ፍቺዉን ለይተዉ እንዲያዉቁ ከማስተማር አኳያ ያለዉ ጥረት | - | - | 3 (37.5%) | 5 (62.5%) | - |
| 27 | ትምህርቱን በጥልቀትና በስፋት ለማቅረብ ከመጻፉ ዉጭ ከሌሎች ማጣቀሻ መጽሐፍት አጋዥ ሀሳቦችን ጨምሮ የማስተማር ሁኔታ | - | - | 3 (37.5%) | 5 (62.5%) | - |

**የክፍለ ጊዜዉን ትምህርት መምህራን በምን መልኩ እንደሚተገብሩት ለማወቅ በተደረገዉ ምልከታ የተገኘ ምላሽ (ዉጤት) ትንተና**

ከላይ በቀረበዉ ሰንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለዉ በተራ ቁጥር "1" ላይ የሰዋሰዉ ትምህርት የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ከማዳበር አንፃር ተዘጋጅቶ የቀረበ ስለመሆኑ የቀረበ የምልከታ መከታተያ ነጥብ መካከለኛ4(50%) ዝቅተኛ 4(50%) መሆኑን በተደረገዉ ተከታታይ የምልከታ ዉጤት ለማየት ተችሏል። በተራ ቁጥር "7" ላይ ተማሪዎች ስለተማሩት የሰዋሰዉ ትምህርት በራሳቸዉ አባባል ለጓደኞቻቸዉ እንዲገልጹ የማነሳሳት ሁኔታን በተመለከተ በቀረበዉ የምልከታ መከተታያ ነጥብ መካከለኛ 5(62..5%) ዝቅተኛ 3(37.5%) መሆኑን የምልከታ ዉጤት ያሳያል። በተራ ቁጥር"10" ላይ የሰዋሰዉ ይዘቶችን ለማስተማር በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከቀረቡት ጥያቄዎች ሌላ ተጨማሪ ለማስተማርያነት የሚያገለግሉ ይዘቶችን ከማቅረብ አንጻር ለቀረበዉ የምልከታ መከታተያ ነጥብ መካከለኛ 2 (25%) ዝቅተኛ 6(75%) መሆኑን መረጃዉ ያሳያል። በተራ ቁጥር "4" ላይ ተማሪዎችን በቤትና በክፍል ስራ የሰሩትን በክፍል ዉስጥ እንዲያቀርቡና እንዲወያዩ ከማድረግ አንፃር ለቀረበዉ የምልከታ መከታተያ ነጥብ በጣም ከፍተኛ 3(37.5%) መካከለኛ3(37.5%) ዝቅተኛ 2(25%) መሆኑን የምልከታ ዉጤቱ ያሳያል። በተራ ቁጥር "21" የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ቅርፆችን መምህራን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ጉዳይ ከማይታወቅ ወደ ሚታወቅ የማቅረቡን ሁኔታ አስመልክቶ ለቀረበዉ የምልከታ መከታተያ ነጥብ ከፍተኛ3(37.5%) መካከለኛ3( 3.7.5%) ዝቅተኛ 2(25%) መሆኑን በምልከታ ዉጤት ለማየት ተችሏል። በተራ ቁጥር "27" ላይ ትምህርቱን በጥልቀትና በስፍት ለማቅረብ ከመጽሐፉ ዉጪ ከሌሎች ማጣቀሻ መጽሐፍት ሀሳቦችን አዳብሮ የማስተማር ሁኔታን

በተመለከተ ለቀረበዉ የምልከታ መከታተያ ነጥብ መካከለኛ 3(37.5%) ዝቅተኛ5(62.5%) መሆኑን በተለያዩ ጊዜያት በተደረገዉ ተከታታይ የምልከታ ዉጤት አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡትን የምልከታ መከታተያ ነጥቦች ዉጤት ለመመልከት እንደተቻለዉ የሰዋሰዉ ይዘቶችን ለማስተማር በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከቀረቡት ጥያቄዎች ሌላ ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ይዘቶችን ከማቅረብ አንጻር ዝቅተኛ እንደሆነ ከምልከታ ዉጤቱ ለማየት ተችሏል፡፡የሰዋሰዉ ትምህርት የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር ተዘጋጅቶ የቀረበ ይዘት በአማካይ ደረጃ ስታይ መካከለኛ መሆኑ ከዉጤቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የሰዋሰዉ ትምህርት ለመስተማር አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ መሣሪያዎችን የመጠቀማቸዉ ሁኔታ ዝቅተኛ እንደሆን ከዉጤቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በሰዋሰዉ ትምህርት ዉስጥ የተካተቱትን ይዘቶች ቅርጻዊ ሥርዓቱንና ፍቺዉን ለይተዉ እንዲያዉቁ ከማስተማር አኳያ ያለዉ ጥረት ዝቅተኛ መሆኑን ከተደረገዉ የምልከታ ዉጤት ለመረዳት ተችሏል፡፡ተማሪዎች ስለተማሩት የሰዋሰዉ ትምህርት በራሳቸዉ አባባል ለጓደኞቻቸዉ እንዲገለጹ የማነሳሳት ጉደይ አነስተኛ እንደሆነ በተከታታይ ምልከታ ዉጤት ለማየት ተችሏል፡፡ በምልከታዉ ላይ ለማየት እንደተሞከረዉ አልፎ አልፎ ዉስን የአተገባበር ክፍትት ቢኖርም የመማር ማስተማሩ የክፍል ዉስጥ አተገባበር ጥሩና ጠንካራ ጎን እንዳለዉ በተደረገዉ ጥናት ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአራቱም ክፍል ላይ ለ8 ተከታታይ ዙር በተደረገዉ የምልከታ ዉጤት ከሰነድ ፍተሸ ዉጤት፣ ከቃለ መጠይቅና ከጽሁፍ መጠይቅ ከተገኘዉ ዉጤት ጋር ተመሳሳይነትና ተደጋጋሬነት ያለዉ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

### 4.4.5 የውጤት ማብራሪያ

- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ከውጤት ተኮር ወደ ሂደት ተኮር መደራጀታቸውን ጥናቱ ፈትሿል፡፡
- በተደረገው የሰነድ ፍተሻ በተተኳሪው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች ምሳሌውን ብቻ ተከትለው በመስራት የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ሥርዓት በቀላሉ ይረዱታል ማለት አይደለም፡፡ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው መልመጃዎች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ስልት ተከትለው የቀረቡ ይሁኑ እንጂ ምሳሌዎችን ብቻ መሠረት አድርገው የሚሰሩት

መልመጃዎች ሁሉም ተማሪዎች በተመጣጣኝ ሁኔታ ትክክለኛ የሆነውን የቋንቋ ህግ በራሳቸው ለማወቅ ሊከብዳቸው ይችላል፡፡

- መስተዋድድ አንድን አረፍተ ነገር እንዲያሰር አድርጎ ከሌላ አረፍተ ነገር ጋር እንዲጠጋ የሚያደርግ ነው፡፡ የሚለው ገለፃ ለተማሪው በሆነ መንገድ አልቀረበም፡፡ ምክንያቱም "እንዲጠጋ" ተብሎ የቀረበው ገለፃ እንዲጠጋ ብሎ ከማለት ሁለት አረፍተ ነገሮች እንዲገናኙ ያደርጋል ተብሎ ቢቀርብ የተሻለ ነበር፡፡
- በ7ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ ላይ በተደረገው የሰነድ ፍተሻ መሠረት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ተማሪዎች የቀረበውን ገለፃ መሠረት አድርገው ህጉን እየተከተሉ በተገቢው መንገድ በመልመጃዎችና ምሳሌዎች በመታገዝ ስርዓቱን ተገንዝበው እንዲተገብሩ የሚያደርጉ አቀራረቦች ስለሆኑ ተማሪው በራሱ ጥረት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር እንዲሄድና በሂደትም በራሱ እንዲተማመን የሚያደርግ ስልት በመሆኑ ጠንካራ ጎን ታይቶበታል፡፡
- በተተኳሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ከሌሎች አቀራረቦች የበለጠ በስፋትና በብዛት ገለፃዎችንና ምሳሌዎችን በማቅረብ በተገቢ መልኩ ቀርቦ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ከጠቅላላ እውቀት ወደ ዝርዝር ወይም ከከባድ ወደ ቀላል በሚሄድ አቀራረብ የራሳቸውን ጥረት አክለውና በምሳሌውም ተደግፈው ወደ ተግባር እንዲሄዱ ያደርጋቸዋል፡፡
- በውጤት ተኮር የይዘት አቀራረብ መሠረት የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ስርአት በመከተል የሚቀርቡ የተለያዩ የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ይዘቶችን ተማሪዎች በተናጥል እንዲተነትኑ መደረጉ አቅም ስለሚሆናቸውና የበለጠ እንዲነሳሱ ስለሚያደርጋቸው አቀራረቡ ተወዳጅና ጥንካሬ እንዲኖረው አድርጎታል፡፡ ምክንያቱም በርዕሰ ጉዳዩ ወይም አንድ አረፍተ ነገር በውስጡ ብዙ ዘርፎችን መያዙንና ተማሪው ደግሞ እያንዳንዱን የሰዋሰው ክፍሎች በቀላሉ እንዲረዳ ማስቻሉ በመልመጃዎች ማሳያነት በተደረገው የሰነድ ፍተሻ ለማየት ተችሏል፡፡
- በውጤት ተኮር አቀራረብ ስር የቀረቡት መልመጃዎች ከሌሎች አቀራረቦች የበለጠ ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡ እነዚህም የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ሥርዓት ጠብቀው በትክክል ሰዋሰዋዊ ህጉን መተግበር ላይ ትኩረት ያደረጉ በመሆናቸው በውጤት ላይ አነጣጥረው የቀረቡ መሆናቸው በሰነድ ፍተሻው ታይቷል፡፡

- የሠነድ ፍተሻው እንደሚያሳየው በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ በሂደት ተኮር አቀራረብ ስር የቀረቡት የሰዋሰው ይዘቶች በቁጥር በጣም ዝቅተኛ ሆነው ታይቷል፡፡
- የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትን ስንመለከት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ይልቅ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ተደራጅቶ የቀረበ ሲሆን ከውጤት ተኮርና ከሂደት ተኮር አንፃር ደግሞ ከሂደት ተኮር ይልቅ ውጤት ተኮር አቀራረብ የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች በስፋት ቀርበው እንደሚገኙ ለማየት ተችሏል፡፡
- ከላይ በንፅፅር የቀረቡትን የሰዋሰው ይዘቶች ብንመለከት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ስልት በውስጡ ይዘቶች ወይም ገለፃዎች በቁጥር 5፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ የሰዋሰው ይዘቶች በቁጥር 10፣ ውጤት ተኮር የአቀራረብ ስልት የቀረቡ የሰዋሰው ይዘቶች ብዛት በቁጥር 14 ሲሆኑ፣ በሂደት ተኮር አቀራረብ ስልት ደግሞ በቁጥር 1 ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- የይዘቶችን ተከታታይነት በተመለከተ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር የተጣጣመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን በዚህ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ይዘቶች ተከታታይነት ጥሩ ሆኖ የድግግሞሽ መጠን ዝቅተኛ ሆኖ ታይቷል፡፡
- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች ወይም ይዘቶች ከተለጣጣቂነት አንፃር በአብዛኛው ተመጣጣኝ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም ለተማሪዎች አረፍተ ነገሮችን ከአገልግሎታቸውና ከሰዋሰዋዊ ቅርፃቸው መመስረት እንዲችሉ ለማስተማር የቀረቡት ጥያቄዎች በቂና ተመጣጣኝ አይደሉም፡፡ በመሆኑም ተመጣጣኝ ባለመሆናቸው አደረጃጀታቸው ተለጣጣቂነት የላቸውም ለማለት ያስችላል፡፡
- የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ያካታተቸው የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች በሙሉ ለደረጃው በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የድግግሞሽ መጠናቸው ቢያንስም አብዛኞቹ እየተደጋገሙ ጥቂቶቹም ሳይደጋገሙ ቀርበዋል፡፡ ከዚህም አኳያ መጽሐፉና መርሃ ትምህርቱ ጥብቅ ትስስር እንዳላቸው ጥናቱ ፈትሿል፡፡
- በዚሁ በተተኳሪ መጽሐፍ ውስጥ ትኩረት የተሰጣቸው የቋንቋ ወይም የሰዋሰው ክፍሎች ስነአገባብና ስነምዕላድ ሲሆኑ ሎሎች ማለትም ስነድምፅ አልተካተቱበትም፡፡ ስለፍቺውም ቢሆን ፍቺውን በግልፅ አለማሳየቱ ከቀረበው የድግግሞሽ መጠን ተመጣጣኝ ያለመሆኑን በሰነድ ፍተሻው ታይቷል፡፡

- በሰነድ ፍተሻው እንደታየው በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ትኩረት የቋንቋውን ቅርፃዊ ሥርዓት በመከተል እንዲሠራ ነው እንጂ "የቋንቋ ቅርፃዊ ሥርዓትና ፍቺ" ለመግለፅ ተብራርቶ አልቀረበም፡፡ ከዚህ አንፃር ከመልመጃዎቹ በተገኘው መረጃ መሠረት በቅርፃዊ ስርዓት የተሰጠው ትኩረት ከፍተኛ ሲሆን ለፍቺ የተሰጠው ትኩረት በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡
- ከሠነድ ፍተሻው፣ከመምህራን ቃለ መጠይቅና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ የተገኘው ውጤት የሚጠቁሙት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኘው የቋንቋ ቅርፃዊ ስርዓትና ፍቺ ተመጣጣኝ ትኩረት አለመሰጠቱን ያረጋግጣል፡፡
- የሰዋሰው መልመጃዎች ይዘቱ/ግብአቱ/ ከጥልቅ ባህሪይ ወደ ዝርዝር ባህርይ ቀርቧል ብለው ይስማማሉ? ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ ከሠነድ ፍተሻው፣የተገኘው ውጤትና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት ተቀራራቢነት ሲኖረው ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኘው ውጤት ተደጋጋፊ አልሆነም፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ይዘቱ ከጥልቅ ወደ ዝርዝር ባህርይ የመደራጀት ሁኔታ አነስተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡
- ከሰነድ ፍተሻው፣ ከመምህራን ቃለ መጠይቅና ለተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ መልክ "በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ምሳሌዎች እንዲታወቅ የተፈለገውን የሰዋሰው ጉዳይ በግልፅ ያቀርባሉ ብለው ያምናሉ"? ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ ከአንዲት መምህርት በሰተቀር ሁሉም መምህራን ተማሪዎቹ ምሳሌውን ተከትለው መሥራት ከቻሉ በውስጡ ያለው የሰዋሰው ጉዳይ ግልፅ ነው ሲሉ የጽሁፍ መጠይቅ የቀረበላቸው ተማሪዎች 79% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ስለዚህ መረጃው ምሣሌዎቹ እንዲተዋወቅ የተፈለገውን የሰዋሰው ጉዳይ በግልፅ መቅረቡን ያሳያል፡፡
- በሰነድ ፍተሻው፣ በመምህራን ቃለ መጠይቅና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ በተገኘው ውጤት መሠረት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋሰው ጥያቄዎች በምሣሌዎቹ ብቻ ሊሠሩ እንደሚችሉ አዎንታዊ ምላሽ ተሰጥቶበታል፡፡
- "በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋሰው ይዘቶች ለገለፃ ወይም ለማስታወሻ ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት ሰጥተዋል ብለው ይስማማሉ"? ለሚለው ጥያቄ ለመምህራን በቃለ መጠይቅ ለደረጃው ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ ቀርቦ አራቱም መምህራን ከሌሎች አንፃር ሲታይ ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት እንደተሰጠው ሲያስረዱ ከተማሪዎች ደግሞ 71% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

- ስለዚህ ከሰነድ ፍተሻው ውጤት፣ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ ምላሽና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ አብዛኛው ምላሽ የሚያሳየው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋሰው ጥያቄዎች ለገለፃ ወይም ለማስታወሻ ትኩረት መስጠታቸውን ነው፡፡
- በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ለደረጃው የሚመጥኑና ተገቢ ስለመሆናቸው ለመምህራን በቃለ መጠይቅ ለተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ ቀርቦ አራቱም መምህራን በመርሃ ትምህርቱም ሆነ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋሰው ይዘቶች ተማሪውን የሚመጥንና ተገቢ ነው በማለት ሲያስረዱ በተመሳሳይ ሁኔታ “በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ለደረጃው የሚመጥንና ተገቢ መሆኑን ይስማማሉ”? ተብሎ ለቀረበው ለፅሁፍ መጠይቅ 65% ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከሠነድ ፍተሻው ውጤት፣ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ ምላሽና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው  በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ለደረጃው መጣኝና ተገቢነት ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡
- የምልከታ መከታተያ ነጥቦች በተለያዩ ጊዜያት በአራቱም ክፍሎች ማለትም በአራቱም ትምህርት ቤት በሚያስተምሩበት ክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታ መሠረት 30 የመከታተያ ነጥቦችን በመጠቀም በጣም ከፍተኛ ነጥብ ካላቸው ተግባራት መካከል የዕለቱን ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ከቀደመው እውቀት በክለሣ ስለመጀመሩ፣ የዕለቱን ትምህርት ለማስተማር የሚያስችል አመታዊ ዕቅድ አዘጋጅቶ ከመግባት አንፃር፣ ሌሎች በሰንጠረዡ ውስጥ የተገለፁትን ጨምሮ በድግግሞሽ 12 ተግባራት በጣም ከፍተኛ ነጥብ እንዳላቸው ጥናቱ ለማየት ችሏል፡፡
- የክፍል ምልከታውን አስመልክቶ በሰንጠረዥ ውስጥ ለመግለፅ እንደተቻለው መምህራን የሰዋሰው ይዘቶችን ሲያስተምሩ ተማሪዎችን ለትምህርቱ ማነሳሳትና የማነቃቃት፣ ተማሪዎች በሰዋሰው ትምህርት የጠለቀ እውቀት እንዲኖራቸው ስለማበረታታት እና ሎሎችን ጨምሮ በተለያዩ ጊዜያት በድግግሞሽ የተገኘውን ውጤት በሰንጠረዥ ውስጥ ለመግለፅ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት ከፍተኛ ነጥብ ያላቸው ተግባራት 20 እንደሆኑ ይህ ጥናት ፈትሿል፡፡
- በተለያዩ ጊዜያት ለ8 ዙር በተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታ በተገኘው መረጃ መሠረት የሰዋሰው ይዘቶችን ለማስተማር በመማሪያ መጽሐፉ ከቀረቡት ጥያቄዎች ሌላ ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ይዘቶችን ከማቅረብ አንፃር፣ ትምህርቱን በጥልቀትና

በስፋት ለማቅረብ ከመጽሐፉ ውጭ ከሌሎች ማጣቀሻ መጽሀፍት አጋዥ ሀሳቦችን ጨምሮ የማስተማር ሁኔታ እና ሌሎች በሠንጠረዡ ውስጥ የተጠቀሱትን ተግባራት ጨምሮ መካከለኛ ነጥብ ያላቸው መሆናቸውን ጥናቱ በትኩረት ተመልክቷል፡፡ መጠናቸውም ከድግግሞሽ አንፃር በቁጥር 20 ተግባራት እንደሆኑ ለማየት ተችሏል፡፡

- በተደረገው ምልከታ መሠረት በሠንጠረዥ ውስጥ ተብራርቶ ከተገለፀው ገለፃ አንፃር ተማሪዎች የሰዋሰውን ትምህርት ተግባቦታዊ አገልግሎት ላይ እንዲያውሉ አድርጎ ማስተማር ስለመቻሉ፣ ተማሪዎች ሰለተማሩበት የሰዋሰው ትምህርት በራሳቸው አባባል ለጓደኞቻቸው እንዲገልፁ የማነሳሳት ጉዳይ እና ሌሎችን ጨምሮ ያላቸው ነጥብ ዝቅተኛ ሆኖ ታይቷል፡፡ ይህም በቁጥር ሲገለፅ 17 መሆኑን ጥናቱ መፈተሽ ችሏል፡፡

  ከፍ ብሎ ለማብራራት እንደተቻለው በምልከታ መከታተያ ተግባራቱ እንደ መለኪያ ጥናቱ የተጠቀመባቸው ነጥቦች በጣም ከፍተኛ፣ከፍተኛ፣መካከለኛ፣ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ሲሆኑ፣በጣም ዝቅተኛ የሚለው ነጥብ በመረጃነት አልተወሰደም፡፡ ሌሎቹ በቅደም ተከተል ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

ጥናቱ ይዞት የተነሳው ዋነኛ አላማ በ2009 ዓ/ም ተዘጋጅቶ ስራ ላይ የዋለው የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ተገቢነት እና የክፍል ውስጥ አተገባበር መፈተሽ ሲሆን ከዋናው አላማ ስር የሚከተሉትን ዝርዝር ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት አድርጓል፡፡

1. በተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ ይዘቶች የቀረቡበት መንገድ ምን ይመስላል?
2. በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተመርጠው የቀረቡት የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች የተደራጁበት መንገድ ምን ይመስላል?
3. የአደረጃጀቱ ጠንካራና ደካማ ጎን ምን ይመስላል?
4. በክፍል ውስጥ የመምህራን አተገባበር  ጠንካራና ደካማ ጎን ምንድን ነው?
5. የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶችን አስመልክቶ በማስተማሪያ መጽሐፍና ከመርሀ ትምህርቱ መካከል ያለው ትስስር ምን ይመስላል ? የሚሉትን ጥናቱ ፈትሿል፡፡

ከመጽሐፍትና ከመረጃ መስኮች የተሰበሰቡ ንድፍ ሀሣባዊ መረጃዎች ጥናቱን እዳር ለማድረስ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የጥናቱ ግብአት የሆኑትን መረጃዎች ለመሰብሰብ አራት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችን ማለትም የሠነድ ፍተሻ፣ቃለ መጠይቅ፣የጽሑፍ መጠይቅና የክፍል ውስጥ ምልክታ አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ በመቀጠልም በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ይዘቶች ተፈትሸዋል፡፡ በደረጃው አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ አራት መምህራን ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸዋል፡፡ በክፍል ደረጃው ለናሙና ለተመረጡ አንድ መቶ ተማሪዎች  የፅሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ በአራት ትምህርትቤቶች ስምንት ዙር የክፍል ውስጥ ምልከታ ተደርጓል፡፡ ከሰነድ ፍተሻው፣ከቃለ መጠይቅ፣ ከጽሁፍ መጠይቅና ከምልከታ የተገኘው መረጃ ከክለሳ ድርሳን በሰፈሩ ንድፈ ሀሳብዊ ጥቆማዎችን መሰረት በማድረግ አይነታዊ የአተናተን ዘዴን በመጠቀም በገላጭ ስልት ቀርቧል፡፡

በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች አደረጃጀት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ከውጤት ተኮር ወደ ሂደት ተኮር የቀረበ ነው፡፡ አራቱን ይዘቶች ማካተቱና ማስተማሩ የመጽሐፍን ጠንካራ ጎን ሲያመለክት ይዘቶቹን አመጣጥኖ ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ አለማቅረቡና በይዘቶቹ መካከል መበላለጥ መኖሩ ድክመቱን ያሳያል፡፡ በዚህ አቀራረብ ሂደት ዉስጥ በሰነድ ፍተሸዉ እንደታየዉ መረጃዉ የሚጠቁመዉ ዉጤት ተኮር አብላጫዉን ድርሻ እንዲያዘ ነዉ፡፡ ከይዘቶቹ አደረጃጀትና አቀራረብ አንፃር ተማሪዎች በቀረበዉ ገለጻና ምሳሌ መሰረት ህጉን እየተከተሉ ወደ ተግባር ቀይረዉ እንዲለማመዱ የተመቻቸ ነዉ፡፡ በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ይዘቶች አልፎ አልፎ ድግግሞሽ ቢኖርም የድግግሞሽ መጠኑ አነስተኛ መሆንና በአንድ ምዕራፍ ዉስጥ ብቻ የመደጋገም ሁኔታ ይታያል፡፡

የደረጃዉ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱት የሰዋሰዉ ይዘቶች አቀራረቡን በሠነድ ፍተሻዉ እንደተመለከትነዉ መልመጃዎቹ ከምሳሌ ወይም ከማስታወሻ ወደ ጥያቄ የቀረቡ፣ ከገለፃ ስልት ብቻ የቀረቡ፣ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ መልመጃዎች ምሳሌ ተሰጥቶ ምሳሌዉን እየተከተሉ መስራትና ስለ ሰዋሰዋዊ ቋንቋ ቅርጽ ማወቅና ካወቁ በኃላ ወደ ጥያቄ መግባትና በመተግበር ተማሪዉ በራሱ እንዲተማመን መደረጉ ከጠንካራ ጎን የሚመደብ ሆኖ ነገር ግን የተማረዎች ልምድ የተለያየ መሆኑ ከግምት ዉስጥ አልገባም፡፡

በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋሰዉ መልመጃዎች ትኩረት ያደረገዉ በአብዛኛዉ በስነአገባብ እና በቅርጻዊ ሥርዓት ላይ ሲሆን በመጠኑ ስነምዕላድን ያካተተ ይመስላል እንጂ በሌሎች የሰዋሰዉ ክፍሎች ማለትም ስነድምፅና ስነፍች አላካተተም፡፡ ነግር ግን በማስታወሻ ወይም በገለፃና በምሳሌ የስርጭት ሚዛኑን ጠብቆ ለማስተማር መቅረቡ ጥሩ ገጽታ እንዳለዉ ያሳያል፡፡ በተለይ ስነምዕላድን አስመልክቶ በግልፅ የቀረበ የሰዋሰዉ ጉዳይ አይታይም፡፡

በሰዋሰዉ አቀራረብ በዉጤት ተኮርና በሂደት ተኮር በሆኑ መንገዶች አንፃር የተደረገ የሠነድ ፍተሻ ሰዋሰዋዊ ይዘቶች በአብላጫዉ ዉጤት ተኮር አካሄድን የተከተሉ መሆናቸዉን ያሰያል፡፡ ለሂደት ተኮር ወይም ለፍቺና ለአጠቃቀም የተሰጠዉ ትኩረት በጣም አነስተኛ ነዉ፡፡ ምክንያቱም መልመጃዎቹ የቋንቋዉን ቅርጽ ብቻ የሚተነትኑ እንጂ ለቅርጹና ለአጠቃቀም(ለተግባቦት) ያልዋሉ ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡

በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች የተማሪዉን የመማር አቅም የገናዘበ፣ የክፍል ደረጃዉን የመጠነና ተገቢ ይዘቶች መቅረባቸዉ በሠነድ ፍተሸዉ፣ በቃል

መጠይቅና በጽሑፍ መጠይቁ ብሎም በክፍል ምልከታዉ መረጀዉ እንደሚጠቁመዉ የቀረበዉ የሰዋሰዉ ይዘት ደረጃዉን የሚመጥንና ተገቢ ሆኖ ታይቷል፡፡

በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከቀረቡት አጠቃላይ 7 ይዘቶች አደረጃጀት መሠረት ማለትም፡- የቃላት ጥናት፣ አንብቦ መረዳት፣ የቃላት ዕዉቀት፣ መጽሐፍ፣ አቀላጥፎ ማንበብ፣ ቃላዊ ክህሎች(ማዳመጥና መናገር) እና ሰዋሰዉ የሚሉት ሲሆኑ እነዚህን ይዘቶች ለማስተማር በእያንዳንዱ ምዕራፎች በሁሉም ክህሎች(ማዳመጥ፣ መናገር፣ማንበብና መጻፍ) የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች የማንበብና የመጻፍን ችሎታዎች በሚያዳብሩት መልክ ለተማሪዉም ሆነ ለመምህሩ ግልጽ በሆነ መንገድ መርሃ ትምህርቱን መሠረት አድርጎ መደራጀቱና መዘጋጀቱ ለመጽሐፉ ትልቅ አድናቆት የሚያሰጡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠዉ ከይዘቶቹ መካከል ለማንበብና አቀላጥፎ ለማንበብ ነዉ፡፡ ከሠነድ ፍተሻዉም ሆነ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘዉ ዉጤት የሚያመለክተዉ በየምዕራፉ ለሰዋሰዉ የተሰጠዉ ክፍለ ጊዜ አነስተኛ መሆኑን ነዉ፡፡ ይህም በአደረጃጀቱ ላይ መጠነኛ ድክመት ታይቶበታል፡፡

በመማሪያ መጽሐፍ ወስጥ በተለያየ ምዕራፍ ከቀረቡት አስራ ስምንት የሰዋሰዉ ይዘቶች ዉስጥ ስምንቱ በተለያየ መጠን ከሁለት እስከ አራት ተደጋግመዉ የቀረቡ ሲሆን አስሩ ደግሞ ምንም ሳይደጋገሙ አንድ ጊዜ ብቻ የቀረቡ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ናቸዉ፡፡ ስለዚህ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ይዘቶች ምንም ሳይደጋገሙ የቀረቡ መሆናቸዉን መረጃዉ ስለሚጠቁም የድግግሞሽ መጠን አነስተኛ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ከዚህ አንፃር በመማሪያ መጽሓፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች በየምዕራፍ በተለያዩ ክፍሎች ተደጋግሞ ያለመቅረብ ሁኔታ ሲታይ ከተከታታይነት አንፃር መጠነኛ ክፍተት እንዲያሳይ አድርጓል፡፡ ምንም እንኳን የድግግሞሽ መጠን ማነስ የይዘቱን ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ በቅደም ተከተል ባይጓዝም መርሃ ትምህርቱና መማሪያ መጽሐፍ ተጣጥመዉ የቀረቡ ስለሆነ አደረጃጀቱን ጠንካራ ያሰኘዋል፡

ለተከታታይ ስምንት ጊዜያት በአራት ትምህርትቤቶች ውስጥ የአራት መምህራን የክፍል ዉስጥ አተገባበር ምን እደሚመስል በተደረገዉ የምልከታ ዉጤት እንደሚያመለክተዉ መምህራኑ በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱትን የሰዋሰዉ ይዘቶችን ሲያስተምሩ የእለቱን ትምህርት ከመጀመራቸዉ በፊት የተማሪዎችን የቅድመ ሰዋሰዉዊ እዉቀታቸዉን ለመመዘን በጥያቄ መልክ በመከለስ ወደ እለቱ ትምህርት መሸጋገር መቻላቸዉ፣ ግልጽና ተማሪዎች በሚገባቸዉ

መንገድ የመተግበርና የማስተማር ስነ ዘዴያቸዉ ጥሩና ጠንካራ ጎን ያለዉ መሆኑን በተከታታይ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች ስለ ተማሩት የሰዋሰዉ ትምህርት በራሳቸዉ አባባል ለጓደኞቻቸዉ እንዲገልጹ የማነሳሳት፣ በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ከቀረቡት ሌላ ማጣቀሻዎችንና አስፈላጊና አጋዥ መርጃ መሳሪያዎችን አለመጠቀማቸዉ እንደ ደካማ ጎን ተመዝግቧል፡፡

በአጠቃላይ በተደረገዉ የሰነድ ፍተሸ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በጽሁፍ መጠይቅና በክፍል ዉስጥ ምልከታየተገኙት ዉጤቶች ተመሳሳይነትና ተደጋጋፊነት ያላቸዉ መሆኑን ከጥናቱ ዉጤት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

## 5.1. አስተያየት

በመማርያ መጽሐፍ ዉስጥ ለተካተቱ ይዘቶች አደረጃጀት ተገቢነት እና የአተገባበርን ድክመት ለማሻሻል ያስችላሉ ተብለዉ በአጥኚዋ የተገመቱ የመፍትሔ ሀሳቦች ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

1. በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋሰዉ ይዘቶች አቀረቀረብ መጠን ሚዛናዊ ቢሆን ወይም መበላለጥ ባይኖር፡፡
2. የይዘቶች መደጋገም አልፎ አልፎ ባይሆንና በየምዕራፉ ተከታታይነቱን ጠብቆ ከቀላል ወደ ከባድ የይዘቱን ጥልቀትና ስፍት እየጨመረ የድግግሞሽ ቁጥር ከፍ ቢል፡፡
3. ከሂደት ተኮር ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት አንጻር ለቋንቋ ሰዋሰዉዊ ቅርጽና ስረዓት ብቻ ትኩረት ባይሰጥና ለሰዋሰዋዊ ቅርጹና ለፍቺያዊ አጠቃቀም ጭምር ትኩረት ቢሰጥ፡፡
4. ከመማሪያ መጽሐፉ የይዘቶች አደረጃጀት አንፃር ለሰዋሰዉ የተሰጠዉ ትኩረት አነስተኛ ስለሆነ ለወደፊት መሻሻል ቢደረግ
5. መምህራን የሰዋሰዉ ትምህርት ለማስተማር አስፈላጊና አጋዥ የሆኑ መርጃ መሳሪያዎችን የመጠቀምና በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡትን ይዘቶች በስፊትና በጥልቀት ለማቅረብ ሌሎች ማጣቀሻ መጽሐፍት የመጠቀም ልምድ ቢኖር፡፡

# ዋቢዎች

ሰሚራ አሊ(2010)፡፡ “በደቡብ ክልል በ2009ዓ.ም ሥራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተከተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶቸ አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ” በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናልዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ አማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ኤም.ኤዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት(ያልታተመ)፡፡

ባየ ይማም (1987)፡፡ የአማርኛ ሰዋሰው ፣ አዲስ አበባ፣ ተ.መ.ማ.ድ.ተ.የግ.ማህበር፡፡

ተስፋዬ በቀለ (1993)፡፡ “በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለ8ኛ ክፍል አማርኛ ኢ.አፌ.ፊት ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምግማ” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት አማርኛን የማስተማር ዘዴ፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

እስሌማን አባይ(2003)፡፡ “በ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ፣ ከስነ ትምህርታዊ ሰዋሰዉ አንጻር” በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲተ የቋንዎች ጥናት ፋካሊቲ የአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት በተጋባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ማስተማር/ALTA/ ኤም.ኤ ድግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት(ያልታተመ)፡፡

ጌታሁን አማረ (1989)፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋሰው በቀላል አቀራረብ፣ አዲስ አበባ ፣አልፋ ማተሚያ ቤት፡፡

Batston,R.(1994). Grammer.oxfored:University press celce-murcia,Mand Hills,S.(1988).

Techniques and Resources in teaching grammr. Oxfored OUP Cook,V.(2001) second Language learning teaching(3rd). New York. Oxfored University press.

Celce-Murcia,M and Hills,S.(1988). Techniques and resources in teaching grammer.Oxfored OUP.

Coook,V, (2001),second language learning teaching (3rd). New York Oxfored University press.

Cunningsworth,A.(1984). Evaluating and selecting EFL Teachnig materials (5th print). Oxfored:henman.

Dawson,C(1984) teaching English as a foreign languge Edinburgh Nelson Harp.

Dubin,Fand E,olshtian.(1986).Cambridge:cambrige University press.

Ellis,R(2000)." The place of grammer instruction in the second/foreign language carriculum''

In Brown,k.led languge and linguistics. Encyclopidia,vol.9oxfored:Eisevier

Ltd.(pp28-54)

Grant,N(1987). Making the most of your text book London long man

Harmer,J.(1987).Teaching and learnig grammer.London:long man

Larsen-Freeman,D(1986).Techniques and principles in languguge teaching oxfored:oxfored

university press.

Larsen-freeman,D.(1991).Teachnig grammer. In celcemurcia;M.(ed) teaching English as

second or foreign languge Boston heinle and heinle publishers.

Leech,G,(1994) "studens grammer-teachers' grammer-learners in bygate,M Tonkyn A

and Evillams,E led, grammer and languge teaches New York: prentice Hall 17-30

Nunan,D.(1991). Languge teaching methodology: A text book for teachers oxfored:

International Book distbution Ltd

Pamer, F(1934). Grammer: London:penguin book

Tyler,R.W.(1949).Basic principles of curriculum and instructon Chigago: The University of

Chigago press.

Ur.P(1988). Grammer practice activities Cambridge: Cambridge University press.

# አባሪዎች

የሠነድ ፍተሻ የሚያተኩርባቸው ነጥቦች የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ 7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ዓይነቶች አደራረጀት ተገቢነት ላይ በመሆኑ የትንተናው ትኩረት በእያንዳንዱ ምዕራፍ እና ንዑስ ክፍል የቀረቡ የሰዋሰው ይዘቶች ትግበራ ላይ ነው። ትኩረቱም በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀታቸው ምን ይመስላል ማለትም ሰዋሰውን ለማስተማር ወይም አደረጃጀቱ (ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ውጤት ተኮር አቀራረብ፣ ህዴት ተኮር የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ፣ እና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ) የሚሉትን አቀራረቦች ወይም አደረጃጀቶችን የትግበራ ብልሃቶች ምን እና እንዴት ናቸው? የሚሉት ዋና ጉዳዮች ናቸው።

**የመማሪያ መጽሐፉ አጠቃላይ ዳራ**

ይህ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ለ7ኛ ክፍል ተማሪዎች እንደ አፍ መፍቻ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን አገልግሎት መስጠት የጀመረው በ2009ዓ.ም (የመጀመሪያ ዕትም) ነው። መጽሐፉ ወደ ዋናው የትምህርት ክፍሎች ከመግባቱ በፊት በመግቢያው ላይ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ የተስማማ መሆን፣ ቀጥሎ ለወላጆች ማስታወሻ፣ ስለ ስርኣተ ትምህርቱ መሰረታዊ መርሆች፣ በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር በጋራ መማር፣የመጽሐፉ ይዘቶች አደረጃጀት፣ትምህርቶች ይልና ከዚያ በመቀጠል፣የቃላት ጥናት፣ አንብበው መረዳት፣ ቃላት፣ መጻፍ፣ አቀላጥፎ ማንበብ፣ ቃላዊ ክህሎች፣ ማዳመጥና መናገር፣ ሰዋሰው ብሎ በማስተዋወቅ ይጀምራል።

ዋናውን የመጽሐፉን ትምህርታዊ አቀራረብ ስንመለከት ደግሞ አስር ምዕራፎች ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ምዕራፍ በሦስተኛ ሳምንታት እና በዘጠነኛ ቀናት ተከፋፍሎ ይገኛል።

በአጠቃላይ የመጽሐፉ የቋንቋ ትምህርት የዘቶች ሰባት ሲሆኑ እነሱም፡-የቃላት ጥናት፣ አንብቦ መረዳት፣ የቃላት እውቀት፣መጻፍ፣ አቀላጥፎ ማንበብ፣ቃላዊ ክፍሎች (ማዳመጥና መናገር) እና የቋንቋውን የተወሰኑ ክፍሎች የሚያሳይ ሰዋሰው ናቸው።ሌላው መጽሐፉ በመጨረሻ ሙዳዬ ቃላት፣ ዋቢ መጽሐፍትን ይዟል። በሌላ በኩል መጽሐፉ በአጠቃላይ ሁለት መቶ ሰላሳ ሰባት ገፆች አሉት።

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስ ሂውማኒቲስ ኮለጅ

## የቋንቋዎችእናስነ-ጽሑፍትምህርትክፍል

## ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

<u>በተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ</u>

<u>የመጠይቁ ዓላማ</u>፡- የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በደቡብ ክልልበ 2009 ዓ.ም ሥራ ላይ በዋለው የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የዋሰው ትምህርት ይዘቶችን ለመገምገም የሚረዱ መረጃዎችን ከተማሪዎች ለመሰብሰብ ነው፡፡ ጥናቱ የሚደርስበት ውጤት አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ለሚማሩ ለ7ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ሰዋሰው በማስተማር ተግባር ውስጥ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም በዚህ መጠይቅ ውስጥ የቀረቡትን ጥያዎች በጥሞና አንብባችሁ ትክክለኛውን መረጃ ትሰጡ ዘንድ በትህትና እንጠይቃለን፡፡ ውድ ጊዜዎንና ጉልበትዎን ሳይቆጥቡ ላደረጉት ቀና ትብብር አጥኚዋ አስቀድማ ምስጋና ታቀርባለች፡፡

**<u>ማሳሰቢያ</u>**

በመጠየቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም

መጠይቁ የሚሞላው በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ አማካይነት በ2009ዓ.ም የተዘጋጀውን የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የሚጠቀሙ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ይሆናል፡፡

**<u>የአዲስ ቃላት መግለጫ፡-</u>** ቃላቱ በመጠየቁ ውስጥ ተደጋግመው ሲያጋጥምዎት አስቀድመው ትርጉማቸውን ለመገንዘብ እንዲመክሩ በትህትና እንጠይቃለን፡፡

**<u>ሰዋሰው</u>፡-** የአማርኛ ቋንቋ ስርዓትን ለማመልከት የተጠቀመ ነው፡፡ ይህ ሲባል ድምፆች ተቀናጅተው ቃላትን፣ ቃላት ተቀናጅተው ሐረጋትን፣ ሐረጋት ተቀናጅተው አረፍተ ነገር የሚመሰርትበትን ሥርዓት አጠቃሎ ያመለክታል፡፡

**<u>የሰዋሰው ክፍል</u>፡-** በሰዋሰው መልመጃዎች ውስጥ ቅጥያ፣ ድርብ ቃላት፣ ነጠላና ድርብ አረፍተ ነገር፣ ገላጭ፣ አያያዥ ቃላት ወዘተ.. በመሳሰሉ ዓይነት የቀረቡትን የቋንቋ ክፍሎች ይመለከታል፡፡

## ክፍልአንድ

መመሪያ 1.ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በተሰጣቸው መልስ መስጫ ቦታ ላይ ትክክለኛውን መረጃ በመሙላት መልሱ፡፡

1. ፆታ------------- 2. ዕድሜ---------- 3. የክፍል ደረጃ-------

4. የሚማሩበት ትምህርት ቤት ስም ----------------------------

5. ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ከተማ ስም--------------ወረዳ------------ዞን-----------ክልል---------

6. እየተማሩበት ያሉ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ርዕስ------------------------------------------

## ክፍል ሁለት

### <u>በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የሰዋሰው ይዘቶች</u>

መመሪያ 2፡- ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በማንበብ ከዚያ ለእያንዳንዱ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ ነው ብለው ያመኑትን ሀሳብ የያዘውን ፊደል ይክበቡ፡፡ የተለየ ሐሳብ ካለዎት በተሰጠው ስፍራ ላይ በመሙላት ይመልሱ፡፡

### ጥያቄዎች

1. መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ሰዋሰው መልመጃዎች ለቋንቋ ቅርፃዊ ስርዓትና ፍች ተመጣጣኝ ትኩረት ሰጥቷል ብለው ይስማማሉ---

**ሀ.** በከፍተኛ ደረጃ እስማማሁ **ሐ.** ለመወሰን ያስቸግረኛል **ሠ.** አልስማማም

**ለ.** እስማማለሁ **መ.** ፈፅሞ አልስማማም **ረ.** ሌላ ሀሳብ ካለዎት ይግለጹ ------

2. የሰዋሰው መልመጃዎች ከይዘቱ ጥልቅ ባህርይ ወደ ዝርዝር ባህሪው ተደራጅተው ቀርበዋል ብለው ይስማማሉ---

**ሀ.** በከፍተኛ ደረጃ እስማማሁ **ሐ.** ለመወሰን ያስቸግረኛል **ሠ.** አልስማማም

**ለ.** እስማማለሁ **መ.** ፈፅሞ አልስማማም **ረ.** ሌላ ሀሳብ ካለዎት ይግለጹ ------

3. ምሳሌዎቹ ወይም መልመጃዎቹ እንዲታወቁ የተፈለገውን የሰዋሰው ጉዳይ በግልጽ ያቀርባሉ ብለው ይስማማሉ---

**ሀ.** በከፍተኛ ደረጃ እስማማሁ **ሐ.** ለመወሰን ያስቸግረኛል **ሠ.** አልስማማም

**ለ.** እስማማለሁ **መ.** ፈፅሞ አልስማማም **ረ.** ሌላ ሀሳብ ካለዎት ይግለጹ ------

4. የቀረቡት ጥያቄዎች በምሳሌዎቹ መሰረት ሊሰሩ ይችላሉ ብለው ያምናሉ---

**ሀ.** በከፍተኛ ደረጃ እስማማሁ **ሐ.** ለመወሰን ያስቸግረኛል **ሠ.** አልስማማም

**ለ.** እስማማለሁ **መ.** ፈፅሞ አልስማማም **ረ.** ሌላ ሀሳብ ካለዎት ይግለጹ ------

5. መልመጃዎቹ ለምሳሌና ለማስታወሻ (ለገለጻ) ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት ሰጥይተዋል ብለው ይስማማሉ----

**ሀ.** በከፍተኛ ደረጃ እስማማሁ **ሐ.** ለመወሰን ያስቸግረኛል **ሠ.** አልስማማም

**ለ.** እስማማለሁ **መ.** ፈፅሞ አልስማማም **ረ.** ሌላ ሀሳብ ካለዎት ይግለጹ ------

6. በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ የሰዋሰው ትምህርት ለመተግበርና ለማጎልበት የተማሪዎች ሚና የላቀ መሆኑን ይስማማሉ?

**ሀ.** በከፍተኛ ደረጃ እስማማሁ **ሐ.** ለመወሰን ያስቸግረኛል **ሠ.** አልስማማም

**ለ.** እስማማለሁ **መ.** ፈፅሞ አልስማማም **ረ.** ሌላ ሀሳብ ካለዎት ይግለጹ ------

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**ሶሻል ሳይንስ ሂውማኒቲስ ኮለጅ**

**የቋንቋዎች እና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል**

**ድህረ ምረቃ ፕሮግራም**

7ኛክፍልአማርኛቋንቋ ለሚያስተምሩ መምህራን የሚቀርቡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

ክፍል አንድ

የዚህ ቃለ መጠይቅ አላማ በደቡብ ክልል በ2009 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለዉ የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መመርያ መጽሐፍ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶቸች አደረጃጀት እና የክፍል ዉስጥ አተገባበር መፈተሽ ነዉ፡፡ እርሶም በመመርያ መጽሐፉ ተጠቅመዉ በማስተማር ሙያ ላይ ስለሆኑ ለዚህ ቃለ መጠይቅ ተመርጠዋል፡፡ ለቃለመጠይቁ ፈቃደኛ በመሆንዎ በቅድሚያ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

**ጥያቄ1**. በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ መልመጃዎች ለቋንቋ ቅርጻዊ ስረአትና ፍቺ ተመጣጣኝ ትኩረት ሰጥቷል ብለዉ ያስባሉ

**ጥያቄ2**. የሰዋሰው መልመጃዎች ይዘቱ(ግበአቱ) ከጥልቅ ባህርይ ወደ ዝርዝር ባህሪ ቀርቧል ብለው ይስማማሉ? በአጭሩ ያብራሩ፡፡

**ጥያቄ3**. ምሳሌዎች ወይም መልመጃዎቹ እንዲታወቁ የተፈለገውን የሰዋሰው ጉዳይ በግልጽ ያቀርባሉ ብለው ያምሉ? ሀሳብዎን በግልጽ የስቀምጡ፡፡

**ጥያቄ4**. የቀረቡትየሰዋሰውጥያቄዎችበምሳሌዎቹመሰረትሊሠሩይችላሉብለውይስማማሉ?

**ጥያቄ5**. የሰዋሰው ጥያቄዎች ወይም መልመጃዎች ለገለፃ ወይም ለማስታወሻ ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት ሰጥቷል ብለው ይስማማሉ? በግልጽ ያብራሩ፡፡

**ጥያቄ6**. በመማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ደረጃዉን የመጠነና አቀረራቡም ተገቢ ነዉ ይላሉ?

**ጥያቄ7**. በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የተቀረቡትን የሰዋሰዉ ይዞች ለማስተማር ያጋጠሞት ችግር አለ?ካለምንምንናቸው? ይዘርዝሩ፡፡

ቃለ መጠይቅ ለሚደረግላቸዉ መምህራን የተሰጠ መለያ ኮድ እና ዳራ

| ተ.ቁ | የት/ት ቤቱ ስም | የመምህራን መጠርያ ኮድ | ፆታ | ዕድሜ | የት/ት ደረጃ | የሰለጠኑ በት ትምህርት መስክ | አገልግሎት ዘመን | ቃለ መጠይቅ የተደረገበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ማሻ አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | መምህር 1 | ሴ | 58 | ዲግሪ | አማርኛ | 36 | 10/9/2013 |
| 2 | ወናኒ አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | መምህር 2 | ወ | 50 | ዲፕሎማ | አማርኛ | 27 | 11/9/1013 |
| 3 | አተሶ አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | መምህር 3 | ሴ | 25 | ዲፕሎማ | አማርኛ | 5 ዓመት | 12/9/2013 |
| 4 | በተስፋ መለስተኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | መምህር 4 | ሴ | 43 | ዲፕሎማ | አማርኛ | 20 ዓመት | 13/9/2013 |

**ጥያቄ1፡-**በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ መልመጃዎች ለቋንቋ ቅርጻዊ ሥርዓትና ፍች ተመጣጣኝ ትኩረት ሰጥቷል ብለዉ ያስባሉ?

**መልስ፡-**

**መምህር1.** *አልስማማም፡፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት ይዘቶች ትኩረት የሚያደርጉት በሰዋሰዋዊ ፍቺ ላይ ሳይሆን በቅርጻዊ ስረአት ላይ ብቻ ስለሆነ፡፡ የቃላት ፍቺ ቢኖርም በሰዋሰዉ ስር ሳይሆን ራሱን ችሎ በቃላት ጥናት ስር የቀረበ ነዉ፡፡*

**መምህር2.***ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በቀረበዉ እስማማለሁ፡፡ ሰዋሰዋዊ ፍቺ ላይ ባያተኩርም በአንብቦ መረዳት ዉስጥ የቃላትን ፍቺ በሰፊዉ ስለሚያስተምር ነዉ፡፡*

**መምህር3.** *አልስማማም፡፡ ምክንያቱም በመጽሐፍ ዉጥ የቀረበዉ የሰዋሰዉ ይዘት አነስተኛ ነዉ፡፡ በቂ ጊዜና የተመጣጠነ ትኩረት ለሁሉም ይዘቶች እኩል አልተሰጠም፡፡*

**መምህር4.** *ለቋንቋዉ ቅርጻዊ ስረአትና ፍቺ ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት አልተሰጠም፡፡ ትኩረቱ በቅርጻዊ ስረአት ላይ ነዉ፡፡ በተለይም በአረፍተ ነገር መዋቅር ላይ ነዉ፡፡*

**ጥያቄ2.** የሰዋሰዉ መልመጃዎች ይዘቱ(ግብአቱ) ከጥልቅ በህሪ ወደ ዝርዝር ባህሪ ቀርቧል ብለዉ ይሰማማሉ? በአጭሩ ያብራሩ፡፡

**መልስ፡-**

**መምህር1.** *ከጥልቅ ባርሂ ወደ ዝርዝር ባህሪ ቀርቧል፡፡ መጠኑ ቢያንስም በማስታወሻ ተደግፎ ቀርቧል በዚህ በኩል ጥሩ ነዉ፡፡*

**መምህር2.** *በቀረበዉ ሀሳብ እስማማለሁ፡፡ ከጥቅል ወደ ዝርዝር ባህሪ ቀርቦ ነዉ ያገኘሁት፡፡*

**መምህር3.** *የይዘቱ አቀራራብ ከሌላዉ ይዘት አንጻርተማጣጣኝ ባይሆንም በጥሩ ሁኔታ ቀርቧል፡፡*

**መምህር4.** *የሰዋሰዉ መልመጃዎች ከጥቅል ባህሪ ወደ ዝርዝር ባህሪ የቀረቡ ናቸዉ ነገር ግን አንዳንድ ቦታ ላይ ማስታወሻ ብቻ ሰጥቶ ቀጥታ ወደ መልመጃ ይገባል። ይህ ደግሞ ለተማሪዎች ሊከብድ ይችላል።*

***ጥያቄ3፡-***ምሳሌዎቹ እንዲታወቁ የተፈለገዉን የሰዋሰዉ ጉዳይ በግልጽ ያቀርባሉ ብለዉ ያምናሉ? ሀሳብዎን በግልጽ ያስቀምጡ።

***መልስ፡-***

**መምህር1.***ምሳሌዎችን ተከትለዉ በምሳሌዉ መሰረት መስራታቸዉ በዉስጡ ያለዉን የሰዋሰዉ ጉዳይ በግልፅ መረዳታቸዉን ያመለክታል። ሊታወቅ የተፈለገዉ የሰዋሰዉ ጉዳይ ግልጽ ነዉ።*

**መምህር2.** *ሁሉም የሚሰጡት የሰዋሰዉ መልመጃ ምሳሌዎችግልፅ ናቸዉ። ችግር የለባቸዉም።*

**መምህር3.** *በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት ምሳሌዎች ችግር የለባቸዉም ግልፅ ናቸዉ።*

**መምህር4.** *አንዳንድ ጊዜ ምሳሌ ብቻ የሰዋሰዉን ጉዳይ ግልፅ ላያደርገዉ ይችላል። ምሳና ገለጻ አንድ ላይ ክልተደጋገፉ ግልጽ ላይሆን ይችላል የሚል ሀሳብ ነዉ ያለኝ።*

**ጥያቄ4.** የቀረቡት የሰዋሰዉ መልመጃ በምሳሌዎቹ ብቻ ሊሰሩ ይችላሉ ብለዉ ይላሉ?

***መልስ፡-***

**መምህር1.** *አዎን የቀረቡት የሰዋሰዉ ጥያቄዎች በምሳሌዉ መሰረት ሊሰሩ ይችላሉ።*

**መምህር2.** *አዎን ምሳሌዎቹን ተከትሎ መስረት ስለሆነ ሊሰሩ ይችላሉ።*

**መምህር3.** *እንደ ተማሪዎቹ የልምድ ሁኔታ ልዩነት ምክንያት በምሳሌዎቹ ብቻ ሊሰሩም ላይሰሩም ይችላሉ።*

**መምህር4**. *በመማሪያ መጽሐፍ ዉስት የቀረቡት ጥያቀዎች በምሳሌዉ መሰሰረት ሊሰሩ ይችላሉ፡፡*

**ጥያቄ5**. በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ጥያቄዎች ወይም መልመጃዎች ለገለፃ ወይም ለማስታወሻ ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት ሰጥተዋል ብለዉ ይስማማሉ? ያብራሩ፡፡

**መልስ፡-**

**መምህር1**. *በመማረያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት ገለፃዎች ወይም ማስተወሻዎች በጥሩ መንገድ ጠቀረቡ ናቸዉ፡፡*

**መምህር2**. *ማስታሻ ዌም ገለጻ ተማሪዎች ሊረዱ በሚችሉበት ሁኔታ የቀረበ ነዉ፡፡*

**መምህር3**. *የቀረበዉ ማስታወሻ ወይ ገለጻ ከሌሎች ይዘቶች አንጻር በተመጣጠነ መልክ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡*

**መምህር4**.*ጥያቄዎች ወይም መልመጃዎቹ ለገለጻ ወይም ለማስታወሻ ተመጣጣኝ ትኩረት ሰጥቶ ነዉ ያገኘሁት፡፡*

**ጥያቄ6** በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች ለደረጃዉ የሚመጥንና ተገቢ ነዉ ይላሉ?

**መልስ፡-**

**መምህር1**. *መማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት ይዘቶች ለደረጃዉ ተማሪ የሚመጥንና ተገቢ ነዉ፡፡*

**መምህር2**. *ከመረሀ ትምህርቱም አንጻር ሲታይ ተመጣጣኝና ተገቢ ነዉ፡፡*

**መምህር3**. *በመማራያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረቡት ይዘቶች መጣኝና ተገቢ መሆናቸዉን ነዉ ያሁት፡፡*

**መምህር4**. *ደረጃዉን የጠበቀ ይዘት ነዉ በዉስጡ ያለዉ ወይም የቀረበዉ፡፡*

**ጥያቄ7.** በክፍል ዉስጥም ሆነ በክፍል ዉጪ የሰዋሰዉ ትምህርት ለመጎልበት የተማሪዎችን ተሳትፎ እንዴት ይገልጻሉ?

**መልስ:-**

**መምህር1.** *ተማሪዎች በአብዛኛዉ የከተማ ልጆች ስለሆኑ ተሳትፎአቸዉ በጣም ጥሩ ነዉ።*

**መምህር2.** *ተማሪዎቹ በከተማና በከተማ ዙሪያ ስለሚኖሩ ከክፍል ዉስጥም ሆነ ከክፍል ዉጪ ጥሩ ተግባቦታዊ ተሳትፎ ይታይባቸዋል።*

**መምህር3.** *እኔ በማስተምርበት ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በአብዛኛዉ የገጠር ልጆች ስለሆኑ ተሳትፎአቸዉ ዝቅተኛ ነዉ።*

**መምህር4.** *ሰዋሰዋዊ ተግባቦትን ለማጎልበት ያላቸዉ ተሳትፎ መካከለኛ ነዉ።*

**ጥያቄ8.** በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ የቀረበዉን የሰዋሰዉ ትምህርት ለማስተማር ያገጠሞት ችግር አለ? ካለ ምን ምን ናቸዉ?

**መልስ:-**

**መምህር1.** *የሰዋሰዉ ትምህርት ሳስተምር ያጋጠመኝ ችግር አለ። 1 በአንድ ምዕራፍ ዉስጥያለዉ የሰዋሰዉ ይዘቶች ማነስ 2 በመማሪያ መጽሐፍ ዉስጥ ሰፊዉን ቦታ የያዘዉ ሰዋሰዉ ሳይሆን ምንባብ ብቻ ነዉ።*

**መምህር2.** *አንድን የሰዋሰዉ መልመጃ ለማስተማር ሌላ አማራጭ ምሳሌዎችን ሳይሰጥ በአንድ ምሳሌ ብቻ አስሮ ማቅረቡ፣ ለሰዋሰዉ ትምህርተ መጎልበት መጣቀሻ መጽሐፍትን አለመገበዙና በየመዕራፉ የቀረቡት የሰዋሰዉ ትምህርት ይዘቶች በቂ አለመሆን ተማሪዎች በትምህርቱ ቀዝቀዝ እንዲሉ ማድረጉ ናቸዉ።*

**መምህር3.** *የተማሪዎች ተሳትፎ በሰዋሰዉ ትምህርት አነስተኛ መሆን፣ድግግሞሽ መኖሩና አሰልቺ መሆን፣ ለሰዋዉ የተሰጠዉ ጊዜ አነስተኛ መሆኑ ናቸዉ።*

**መምህር4.** *ተማሪዎች ለሌሎች የክሂል ይዘቶች የሚሰጡትን ያህል ለሰዋሰዉ ትምህርት ትኩረት አለመስጠት፣ የሰዋሰዉን ትምህርት ከሌሎች ይዘቶች በተለየ መልክ አክብዶ መመለከትና ተነሳሽነት ማጣት ናቸዉ።*